# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ረቡዕ | 83ኛ ዓመት ቁጥር 359 ነሐሴ 29 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10.00 | ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!



ፀደይ ባንክ (አ.ማ)
TSEDEY BANK (S.C)

የሁሉም ባንክ
Bank for all !

የብዙዎችን ተስፋ ያለመለመ!

በፋይናንስ አቅርቦት በተግባር የተፈተነ እንዲሁም ሰፊና ጽኑ መሰረት ያለው ባንክ በአነስተኛ የፋይናንስ አገልግሎት ዘርፍ በአገለገለባቸው 25 ዓመታት አለም አቀፍ ዕውቅናዎችን ሲያገኝ የቆየው አማራ ብድርና ቁጠባ ተቋም ወደ ፀደይ ባንክ ተሸጋግሮ የተሟላ አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል።

Tel: +251 115 58 12 70/011 551 73 48/011 558 99 98
P.O.Box: 9630
E-mail: mekonnenyelewemwessen@tsedeybank-sc.com
Web: www.tsedeybank.org.et
Addis Ababa, Ethiopia


# የአቪዬሽን ሕግና የተጓዦች ግንዛቤ


ነፃነት አለሙ


**ዜና ትንታኔ**

በቅርቡ ጃፓን በሚገኘው የኒው ቺቶስ አውሮፕላን ማረፊያ የፍተሻ ጣቢያ አካባቢ ከሚገኝ ሱቅ ሁለት መቀሶች ጠፉ። የእነዚህ መቀሶች ፍለጋም ሰዓታትን ፈጅቶ 36 በረራዎች እንዲሰረዙና 201 በረራዎች እንዲራዘሙ ምክንያት ሆነ። በመቶዎች የሚቆጠሩ መንገደኞች በድጋሚ ተፈትሸው ከሁለት ሰዓታት በኋላ በረራ ተጀመረ።

በመቀስ ምክንያት በተራዘሙና በተሰረዙ በረራዎች ምክንያት በርካቶች መንገላታታቸውን የገለፁ ቢሆንም መቀሶቹ ለሽብር ተግባር ውለው ሊደርስ የሚችለውን ጉዳት ተገንዝቦ አውሮፕላን ማረፊያው የወሰደው ርምጃ ለመንገደኞቹ ደኅንነት ቅድሚያ መስጠቱን ያሳያል ያሉ ዓለም


የአቪዬሽን ሕግና... ወደ ገጽ 11 ዞሯል










# የጥናትና ምርምር ውጤቶች ምን እየፈየዱ ነው?


ልጅዓለም ፍቅሬ


**ዜና ትንታኔ**

በኢትዮጵያ በከፍተኛ ትምህርት እንዲሁም ለጥናትና ምርምር ተቋማት በየዓመቱ በርካታ የምርምር ሥራዎች ይሠራሉ። ለዚህ ተብሎም በየዓመቱ በርካታ ገንዘብ ወጪ ይደረጋል።

ለዩኒቨርስቲዎች ብቻ በየዓመቱ ለጥናትና ምርምር ተብሎ ከሦስት ቢሊዮን ብር በላይ እንደሚበጀት የተለያዩ መረጃዎች ይጠቁማሉ። ነገር ግን ከሚሠሩት የጥናትና ምርምር ሥራዎች አብዛኞቹ በየተሠሩበት ተቋም ጠረጴዛ ከማሞቅ የዘለለ አንዳች የሚፈይዱ አይደሉም።

ዩኒቨርስቲዎች ተማሪን ከማሠልጠን ጎን ለጎን የጥናትና የምርምር ውጤቶቻቸው በሀገሪቱ ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ችግሮች ላይ ፈውስ መሆን ለምን አልቻሉም? ጥናትና ምርምር በሚሠሩ ተቋማት፣ በምሑራን እንዲሁም በፖሊሲ አውጪዎች መካከል የተቀናጀ የአሠራር ሥርዓት ባለመዘርጋቱ የተሠሩት ጥናቶች ወደ ተግባር እንዳይቀየሩ ከፍተኛ ተግዳሮት መሆኑን የዘርፉ ምሑራን ያብራራሉ።

በዩኒቨርስቲዎች የሚሠሩ ጥናቶች ተቀባያቸው ማነው? ለሚለው ጥያቄም እስከ ዛሬ መልስ ሳያገኝ ቆይቷል ይላሉ። በዚህም የተነሳ ከሚሠሩት ምርምሮች ውስጥ አብዛኛው ወደ ተግባር አይገቡም።

ሀሳባቸውን ለኢፕድ የሰጡት በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የልዩ ፍላጎትና አካቶ ትምህርት ክፍል


የጥናትና ምርምር... ወደ ገጽ 11 ዞሯል






# ጠንካራ የሥራ ባሕል የታየበት የሐዋሳ የኮሪደር ልማት


ሳሙኤል ወንደሰን


**ዜና ሐተታ**

ምቹ የእግረኛ መንገዶችን፣ የሞተር አልባ (ብስክሌት) መንገዶችን፣ አረንጓዴ ስፍራዎችን፣ የመንገድ ዳርቻ ማረፊያ መቀመጫዎችን፣ የሕዝብ መናፈሻዎችን፣ የዘመናዊ ከተማ ደረጃን የሚመጥኑ መብራቶችና ፋውንቴኖችን ባጠረ ጊዜ ለመገንባት የሚያስችል ሥራ በሐዋሳ ከተማ እየተከናወነ ይገኛል።

የኮሪደር ልማት ሥራው ቀን ከሌሊት እየተሠራ ነው፤ በዚህም ለበርካቶች የሥራ ዕድል ተፈጥሮላቸዋል። በሥራ ላይ ያገኘነው ወጣት ፍቃዱ ሹቴ የሴራሚክና የቴራዞ ባለሙያ ነው። በሙያው የሰባት ዓመታት ልምድ አለው። ያካበተው ልምድ በሐዋሳ ከተማ የኮሪደር ልማት ተቀጥሮ እንዲሠራ ዕድል ሰጥቶታል።

ወጣት ፍቃዱ የተወለደው በሲዳማ ክልል ይርጋለም አካባቢ ነው። በተለያዩ አካባቢዎች በኮንስትራክሽን ፕሮጀክቶች ውስጥ በረዳትነት ሲሠራ መቆየቱን


ጠንካራ የሥራ... ወደ ገጽ 11 ዞሯል





# በክልሉ በ149 ሺህ ሔክታር መሬት ላይ ሩዝ እየለማ ነው

## - ከመኸር ግብርና 169 ሚሊዮን ኩንታል ምርት ይጠበቃል

**ዳግማዊት አበበ**



አዲስ አበባ፡- በክልሉ በ149 ሺህ ሔክታር መሬት ላይ ሩዝ እየለማ መሆኑን የአማራ ክልል ግብርና ቢሮ አስታወቀ። በዘንድሮ የመኸር ወቅት በዘር ከተሸፈነው ከአምስት ሚሊዮን ሔክታር በላይ መሬት 169 ሚሊዮን ኩንታል ምርት ይጠበቃል።

የአማራ ክልል ግብርና ቢሮ ምክትል ቢሮ ኃላፊ አቶ ቃልኪዳን ሽፈራው ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በክልሉ በሚገኙ አምስት ዞኖች የተሻለ የሩዝ ምርት ለማምረት ታቅዷል።

ከመደበኛው ሰብሎች በተጨማሪ ሩዝ ምርት ላይ ጥሩ እንቅስቃሴ መኖሩን ጠቁመው፤ በዘንድሮ የመኸር ወቅት የ149 ሺህ ሔክታር መሬት በሩዝ መሸፈኑን ተናግረዋል።

በዘንድሮ የምርት ዘመን ክልሉ ልዩ እቅድ ይዞ ሩዝ ማምረት አቅም እያላቸው እስካሁን ግን የማምረት ልምምድ ያላደረጉ አካባቢዎች ላይ በትኩረት እየሠራ መሆኑን አስረድተዋል።

ከዚህ ቀደም ሩዝ በስፋት ይመረትባቸው ከነበሩ የደቡብ ጎንደር ዞን አካባቢዎች ባለፈ በማዕከላዊ ጎንደር ዞን እና በአዊ ብሔረሰብ አስተዳደር ምርቱን የማለማመድ ሥራ መሠራቱንም አንስተዋል።

የሩዝ ምርት የክልሉ የትኩረት አቅጣጫ ሆኗል ያሉት ምክትል ቢሮ ኃላፊው፤ የአማራ ክልል ግብርና ቢሮ ሩዝን በክላስተር ለማምረት የሚያስችል ሥራ ማከናወኑን ገልጸዋል።

በክልሉ ውኃ በብዛት በሚተኛበት ቦታ የሚመረት ሩዝ እንዳለ ሁሉ እንደማንኛውም ሰብል ውኃ በማይተኛበት ቦታ የሚመረት ሩዝ መኖሩንም ጠቁመዋል።

በ2015/16 ዓ.ም የምርት ዘመን በክልሉ ከ82 ሺህ ሔክታር በላይ መሬት በሩዝ ዘር በመሸፈን ከአራት ሚሊዮን ኩንታል በላይ የሩዝ ምርት መሠብሠብ እንደተቻለ አስታውሰው፤ በዘንድሮ የምርት ወቅት ደግሞ ከቀድሞው የተሻለ መጠን ያለው ምርት ለማግኘት መታቀዱን አመላክተዋል።

በተያያዘ በክልሉ በዘንድሮ የመኸር ወቅት በአጠቃላይ አምስት ነጥብ አንድ ሚሊዮን ሔክታር መሬት በተለያዩ የሰብል ዘሮች ለመሸፈን ታቅዶ እስካሁን ከ97 በመቶ በላይ ሥራውን ማሳካት ተችሏል ብለዋል።

በክልሉ በመኸር ከሚለማው መሬት 169 ሚሊዮን ኩንታል ምርት ይገኛል ተብሎ ይጠበቃል ያሉት አቶ ቃልኪዳን፤ ምርቶቹ የምግብ ዋስትናን ከማረጋገጥ ባለፈ ለግብርና ምርት ማቀነባበሪያ ኢንዱስትሪና ለውጭ ገበያ እንዲሆኑ ልየታ ተደርጎ በተለያዩ አካባቢዎች የዘር መዝራት ሥራ መከናወኑን አስረድተዋል።

እንደ ምክትል ቢሮ ኃላፊው ገለጻ፤ ከሩዝ ምርት ባለፈ ለውጭ ገበያ በሚቀርቡ ሰብሎች ማለትም ማሾ፣ ሰሊጥና ቦሎቄ ላይ በትኩረት እየተሠራ ነው።

በሁሉም አካባቢዎች ያለው የሰብል አያያዝ ጥሩ ደረጃ ላይ እንደሚገኝ ጠቁመው፤ የግብዓት አቅርቦት በጊዜ መሰራጨቱ የተሻለ አፈጻጸም እንዲኖር ማስቻሉን ተናግረዋል።

በክልሉ ያለው የዝናብ ስርጭት ለግብርና ሥራው አመቺ መሆኑን የተናገሩት አቶ ቃልኪዳን፤ የማሳ ዝግጅት ሥራውን ቀደም ብሎ መጀመሩ የግብርናው ሥራ በጥሩ ሁኔታ እንዲካሄድ አግዟል ሲሉ ገልጸዋል።

እያንዳንዱ ሰብል መዘራት ባለበት የጊዜ ሰሌዳ እየተዘራ መሆኑን ያነሱት ምክትል ቢሮ ኃላፊው፤ በክልሉ ባሉ ሁሉም አካባቢዎች የመኸር ወቅት የግብርና ሥራው በተሻለ መልኩ እየተከናወነ ይገኛል ብለዋል።

የዘንድሮ ክረምት ዝናብ ከበድ ያለ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ለተባይ መፈጠር ምቹ አለመሆኑን ጠቁመው፤ ይሁንና በየዓመቱ የሚከሰቱ መደበኛ ተባዮች መኖራቸውን አስረድተዋል።

በተለይም ቢጫ ዋግን ለመቆጣጠር የአሰሳ ሥራ እየተሠራ እንደሚገኝ ተናግረው፤ እስካሁን ባለው መረጃ አስጊ የሆነ የአረምም ሆነ የተባይ ወረርሽኝ አለመከሰቱን አስታውቀዋል።

# ኅብረተሰቡ ሕጋዊ የንግድ ሥርዓትን ተከትሎ የተረጋጋ ግብይት እንዲፈፅም ጥሪ ቀረበ

## - በመዲናዋ ለመጪው በዓል በቂ ግብዓት ተሟልቷል

**ማሕሌት ብዙነህ**

አዲስ አበባ፡- ኅብረተሰቡ ለ2017 የዘመን መለወጫ በዓል ተፈላጊ የሆኑ ምርቶች ላይ ሕጋዊ የንግድ ሥርዓትን ብቻ በመከተል የተረጋጋ ግብይት ሊፈፅም እንደሚገባ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ንግድ ቢሮ ጥሪ አቀረበ። በመዲናዋ ለመጪው በዓል በቂ ግብዓት ስለመሟላቱም ተመላክቷል።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ንግድ ቢሮ አዲስ ዓመትን በማስመልከት በምርት አቅርቦት እና ቁጥጥር ላይ እየተከናወኑ ያሉ ተግባራትን በተመለከተ ትናንትና መግለጫ ሰጥቷል።

የቢሮው ኃላፊ ወይዘሮ ሀቢባ ሲራጅ እንደገለፁት፤ ለዘመን መለወጫ በዓል አስፈላጊ ምርቶች ላይ ምንም ዓይነት የዋጋ ጭማሪ እንዳይኖር ገበያውን የማረጋጋትና የቁጥጥር ሥራ እየተሠራ ይገኛል።

በመሆኑም ኅብረተሰቡ በቂ የበዓል ግብዓት መቅረቡን በመገንዘብ ሕጋዊ የንግድ ሥርዓትን በመከተል የተረጋጋ ግብይት ሊፈፅም ይገባል ሲሉ ጥሪ አቅርበዋል።

ለበዓል ግብዓት የሚሆኑት ምርቶችም በተመጣጣኝ ዋጋ መቅረባቸውን አብራርተዋል።

ለበዓሉ በመዲናዋ በቂ የምርት አቅርቦት ከመፈጠሩም በላይ ቢሮው ሕገወጥ የንግድ እንቅስቃሴዎችን ለመከላከል የሚያስችሉ ተግባራትን አቅዶ እያከናወነ እንደሚገኝ ገልጸዋል።

በዚህም የሽንኩርት፣ የእንቁላል፣ የዘይት፣ የምግብ ዱቄት፣ የቁም እንሰሳት፣ የቅቤና የጤፍ ምርቶችን ጨምሮ ለበዓሉ አስፈላጊ የሆኑ ሌሎች የግብርና፣ የእንስሳት እንዲሁም የኢንዱስትሪ ግብዓቶች በተመጣጣኝ ዋጋ እየቀረቡ መሆኑን አስታውቀዋል።



ወይዘሮ ሀቢባ ሲራጅ

በከተማዋ በሚገኙ የገበያ ማዕከላት እንዲሁም ከነሐሴ 27 እስከ ጳጉሜን 5 ቀን 2016 ዓ.ም በሚቆዩ ባዛሮች እንዲሁም ለ10 ቀናት በከተማዋ በሚገኙ በ193 የእሁድ ገበያዎች ምርቶቹ በስፋት እየቀረቡ መሆኑን ጠቅሰዋል።

ቢሮው ከአዲስ አበባ የንግድ ሥራዎች ድርጅትና ከኅብረት ሥራ ኮሚሽን፣ ከማኅበራት፣ ከአርሶ አደሮች እንዲሁም ከአቅራቢ ድርጅቶች ጋር በመቀናጀት የምርት አቅርቦት እጥረት እንዳይኖር እየሠራ መሆኑም ኃላፊዋ ገልጸዋል።

በተጨማሪም ከበዓሉ ጋር በተያያዘ በሸቀጦች ዋጋ ላይ ያለአግባብ ጭማሪ በሚያደርጉ እንዲሁም ምርትን በመደበቅና በማሸሽ ሰው ሠራሽ የምርት እጥረት እንዲከሰት የሚደረጉ ነጋዴዎች ላይ በተቋቋመው ግብረ ኃይል አማካኝነት ርምጃ ይወሰዳል ብለዋል።

በመሆኑንም ማኅበረሰቡ የንግድ ሥርዓትን ብቻ በመከተል ምርቶቹን በተመጣጣኝ ዋጋ በመሸመት እንዲሁም ሕገወጥ ነጋዴዎችን በመጠቆም የተሳለጠ ግብይት ማከናወን እንደሚችል ወይዘሮ ሀቢባ ጠቅሰዋል።

# ኮርፖሬሽኑ ሴራሚክና የፕላስቲክ ውጤቶችን ሊያመርት ነው

**መስከረም ሰይፉ**

አዲስ አበባ፡- በ2017 ዓ.ም ለሀገር ውስጥ ፍጆታ የሚውሉ ሴራሚክ፣ የተለያዩ ፕላስቲክ ውጤቶችንና የኮንስትራክሽን ግብዓቶችን እንደሚያመርት የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ሥራዎች ኮርፖሬሽን አስታወቀ።

የኮርፖሬሽኑ ዋና ሥራ አስኪያጅ ዮናስ አያሌው (ኢ/ር) እንደገለጹት፤ በ2016 በጀት ዓመት ኮርፖሬሽኑ ለራሱ ፍጆታ የሚውሉ ግብዓቶችን አምርቶ ሲጠቀም ቆይቷል።

በ2017 ዓ.ም አቅሙን በማሳደግ እንዲሁም ከሀገር ውስጥና ከውጭ ካሉ ኢንቨስተሮች ጋር ሼር ካምፓኒዎችን በመክፈት ሴራሚክ፣ የፕላስቲክ ውጤቶችን እና የተለያዩ የኮንስትራክሽን እቃዎችን በማምረት በተመጣጣኝ ዋጋ ለገበያ ማቅረብ እንደሚጀምር አመላክተዋል።

ምርቶቹ ከውጭ የሚመጡ የኮንስትራክሽን ግብዓቶችን በሀገር ውስጥ የመተካትና ገበያውን የማረጋጋት ሚና እንደሚኖራቸው አስረድተዋል።

የኮንስትራክሽን ግብዓቶች ፍላጎት በየጊዜው እየጨመረ በመሆኑ በራስ አቅም ማምረት አስፈላጊ ነው ያሉት የኮርፖሬሽኑ ዋና ሥራ አስኪያጅ፤ ተቋሙ የኮንስትራክሽን ግብዓት እጥረትን ለመቀነስ የሚችል የኢንዱስትሪ ዞን አቋቁሞ ለራሱ የሚውሉ ግብዓቶችን ሲያመርት መቆየቱን አስታውሰዋል።

ተቋሙ የኮንስትራክሽን ግብዓት የማምረት አቅሙ 60 በመቶ ለማሳደግ አቅዶ እየተንቀሳቀሰ መሆኑን ጠቁመዋል።

የኢትዮጵያ የግንባታዎች ፕሮጀክት በአብዛኛው የሚሠሩት በውጪ ሀገራት ድርጅቶች መሆኑን አንስተው፤ በቀጣይ ይሄንን ለማስቀረትና የሀገር ውስጥ ፕሮጀክቶችን ከመገንባት ባለፈ ተቋሙ ዓለም አቀፍ ፕሮጀክቶችን ጭምር ለመሥራት በሂደት ላይ መሆኑን ተናግረዋል።



ዮናስ አያሌው (ኢ/ር)

ኮርፖሬሽኑ በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪና በአፍሪካ ሁነኛ ተቋም ለማድረግ አቅም መፍጠር የሚችል ሥራዎችን እየሠራ መሆኑን ገልጸው፤ በ2016 በጀት ዓመት በአራት የአፍሪካ ሀገራት ቅርንጫፎች መክፈቱንና በቀጣይ አምስት ዓመታትም በአምስት ሀገራት ቅርንጫፉን ለማስፋት አቅዶ እየተንቀሳቀሰ መሆኑን ገልጸዋል።

በተጨማሪም ኮርፖሬሽኑ የተገጣጠሙ ቤቶች የመገንባትና ለገበያ የማቅረብ ፍላጎት እንዳለው አመላክተው፤ የተገጣጠሙ ቤቶችን ይዘት ከአራት ፎቅ ወደ ዘጠኝና 12 ፎቅ ለማሳደግ እየሠራ ይገኛል ብለዋል።

ከዚህ ቀደም ተገጣጣሚ ቤቶች ሲሠሩ ግንባታው የሚካሄደው ሳይት ላይ እንደነበር ገልጸው፤ ኮርፖሬሽኑ በአሁኑ ሰዓት ቤቶችን አስቀድሞ ገጣጥሞ የማስቀመጥ (የፕሪፋብ) አሠራር መጀመሩን አስታውቀዋል።

በአዲሱ አሠራር መሠረት አሁን ገበያ ላይ ካሉ ሪልስቴቶች በግማሽ የሚቀንስ ዋጋ ያላቸውን ቤቶች ለገበያ ለማቅረብ የሚያስችለውን ጥናት ማጠናቀቁን ገልጸዋል።



# ሆስፒታሉን የምርምርና የትምህርት ልህቀት ማዕከል ለማድረግ እየተሠራ ነው

**ዳግማዊት አበበ**

አዲስ አበባ፡- የቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም ሕክምና ኮሌጅ በሕክምና አገልግሎት አሰጣጥ፣ በምርምርና በትምህርት የልህቀት ማዕከል ለማድረግ በትኩረት እየሠራ መሆኑን አስታወቀ።

የቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም የሕክምና ኮሌጅ ዋና ሥራ አስኪያጅ ሲሳይ ስርጉ (ዶ/ር) በተለይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ተቋሙን በሕክምና አገልግሎት አሰጣጥ፣ በምርምርና በትምህርት የልህቀት ማዕከል ለማድረግ የተጀመረውን ጥረት ከግብ ለማድረስ የተለያዩ ሥራዎች እየተሠሩ ነው።

ለኅብረተሰቡ የሚቀርበውን የጤና አገልግሎት ጥራትን ለማሻሻል እና የሆስፒታሉን የአስተዳደር ልህቀትን እውን ለማድረግ የተለያዩ ግንባታዎችን እንዲሁም የማሻሻያ ሥራዎች እየተከናወኑ ይገኛል ብለዋል።

ቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ለአንጀት፣ ለጉበት፣ ለካንሰር እና ለልብ ሕክምና ማዕከላት የሚያገለግሉ የሦስት አዳዲስ ሕንፃዎችን ግንባታ በማጠናቀቅ ላይ መሆኑን ዶክተር ሲሳይ ገልጸዋል።

ማዕከላቱ በሆስፒታሉ የሚሰጡ አገልግሎቶችን ለማስፋትና ጥራት ለመጨመር እንዲሁም የሕክምና አገልግሎት መስጫ ቦታ ጥበት እንዳይከሰት የሚረዱ መሆናቸውን አንስተዋል።

ዋና ሥራ አስኪያጁ እንዳመለከቱት፤ ማዕከላቱ ሙሉ በሙሉ ሲጠናቀቁ በአጠቃላይ 110 የሕክምና አልጋዎች ሲኖራቸው በከፍተኛ ቴክኖሎጂ እንዲደራጁ ይደረጋል።

ሆስፒታሉ ከማዕከላቱ ግንባታ ባለፈ የጤና አጠባበቅ አገልግሎቱ ላይ ልዩ ልዩ ማሻሻያዎች ማድረጉን ጠቁመው፤ በተቋሙ ቀዶ ጥገና ተሠርቶ ሌላ ታካሚ ለማስገባት የሚወስደውን ጊዜ ከ30 ደቂቃ ወደ 15 ደቂቃ ማውረድ መቻሉን ገልጸዋል። ይህም በርካታ ታካሚዎችን ለማስተናገድና የተገልጋይን እርካታ ለማሳደግ አግዟል ብለዋል።

በተጨማሪ በሆስፒታል ተመላልሰው የሕክምና አገልግሎት የሚያገኙ ሰዎች በአካል ከመምጣት ይልቅ በቤታቸው ሆነው በነፃ የስልክ ጥሪ የሕክምና ውጤታቸውንም ማግኘት እና ቀጠሮ ማስያዝ እንዲችሉ ተደርጓል ሲሉ አስታውቀዋል።

ሆስፒታሉ 13 የላብራቶሪ አገልግሎት ፈቃድ ስላለው የእውቅና ሥርዓት ውስጥ እንዲገባ ለማስቻል በቀጣይ ይሠራል ብለዋል።

ለታካሚዎች ጥራት ያለው የጤና አገልግሎት ለመስጠት የተለያዩ ተግባራትን ሲያከናወኑ መቆየታቸውን አስታውሰው፤ ከስፔሻሊስቶች፣ ከአገልግሎት መስጫ ቦታዎች ጥበትና ከቴክኖሎጂ እድገት ጋር ተያይዞ ውስንነቶች ነበሩ፤ ግንባታ ላይ ያሉት ሦስቱ ሕንፃዎች በ2017 ዓ.ም ለአገልግሎት ሲበቁ ለችግሮቹ ምላሽ ይገኛል ተብሎ እንደሚጠበቅ ጠቁመዋል።

የቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም ሕክምና ኮሌጅ በአጠቃላይ አራት ሺህ 350 ሠራተኞች አሉት፣ ከዚህ መካከል 300ዎቹ የሕክምና ስፔሻሊስቶች ናቸው።

# በትግራይ እና በአማራ የምክክር ሥራዎች ከተከናወኑ ሀገራዊ ምክክር ጉባኤ በመጪው ጥር ወር ይካሄዳል

## - የሲዳማ ክልል የአጀንዳ ማሰባሰብ የምክክር ምዕራፍ ተጠናቀቀ

**መዓዛ ማሞ**

ሐዋሳ፡-በትግራይ እና በአማራ ክልሎች የምክክር ሥራዎች ከተከናወኑ ዋናው ሀገራዊ ምክክር ጉባኤ በመጪው ጥር ወር እንደሚከናወን ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን ገለጸ። በሲዳማ ክልል ለሰባት ተከታታይ ቀናት ሲደረግ የቆየው የአጀንዳ ማሰባሰብ የምክክር ምዕራፍ ትናንት ተጠናቋል።

የሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን ዋና ኮሚሽነር መስፍን አርዓያ (ፕ/ር) በሲዳማ ክልል የአጀንዳ ማሰባሰብ የምክክር መድረክ ማጠቃለያ ላይ ተገኝተው ባደረጉት ንግግር እንደገለጹት፤ በትግራይና በአማራ ክልሎች የሚከናወኑ ክልላዊ የምክክር ሥራዎች ከተሠሩ ዋናው ሀገራዊ ምክክር ጉባኤ በቀጣዩ ዓመት በጥር ወር ይካሄዳል።

በአሁኑ ጊዜ ኮሚሽኑ በክልሎች የአጀንዳ ማሰባሰብ የምክክር ምዕራፍ እያከናወነ መሆኑን ጠቁመው፤ ከተሰበሰቡ አጀንዳዎች ወሳኞቹ ተመርጠው በዋናው ሀገራዊ ምክክር ጉባኤ ምክክር እንደሚደረግባቸው አመላክተዋል።

ምክክሩ አሸናፊ እና ተሸናፊ የሚኖርበት አይደለም ያሉት ዋና ኮሚሽነሩ፤ በምክክር ያሉትን ችግሮች በመፍታት ሁሉም አሸናፊ የሚሆንበት መሆኑን ገልጸዋል።

በምክክሩ ሕዝቦች በሁሉም አጀንዳዎች ላይ መፍትሔ የሚፈልጉበት መሆኑን ጠቁመው፤ መፍትሔ በማይገኝባቸው ላይ ሕዝቡ እንዲወስን የሚደረግበት የምክክር ሂደት እንደሚሆንም ገልጸዋል።

ትልልቅ ተቋማት ሀሳባቸውን በተደራጀ መልኩ ለኮሚሽኑ እያቀረቡ መሆኑን የተናገሩት ዋና ኮሚሽነሩ፤ ማንኛውም የውይይት አጀንዳ ያለው ወገን ያለውን አጀንዳ ለኮሚሽኑ ማቅረብ እንደሚችል ተናግረዋል።



ኮሚሽኑ በሲዳማ ክልል የተሰበሰቡ አጀንዳዎችን ተረክቧል

በሲዳማ ክልል ለሰባት ተከታታይ ቀናት ሲደረግ የቆየው የአጀንዳ ማሰባሰብ የምክክር መድረክ ውጤታማ እንደነበረ ገልጸው፤ ለሂደቱ መሳካት አስተዋፅዖ ያደረጉ አካላትን አመስግነዋል።

የሲዳማ ክልል የባለድርሻ አካላት ወኪሎች የክልሉን አጀንዳዎች ለኮሚሽኑ አስረክበዋል። በአጀንዳ ማሰባሰብ የምክክር መድረክ ማጠቃለያ መርሐ ግብሩ ከአምስቱ ባለድርሻ አካላት የተመረጡ 25 የባለድርሻ አካላት ወኪሎች የሲዳማ የክልልን አጀንዳዎችን አደራጅተው ለኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን አስረክበዋል።

በሲዳማ ክልል በተከናወነው አጀንዳ የማሰባሰብ የምክክር መድረክ ከ900 በላይ የሚሆኑ ከሲዳማ ክልል ከሚገኙ 45 ወረዳዎች የተመረጡ የማኅበረሰብ ወኪሎች፣ በክልሉ የሚገኙ የፖለቲካ ፓርቲዎች፣ ሦስቱ የመንግሥት አካላት ተወካዮች፣ የተለያዩ ተቋማትና ማኅበራት ተወካዮች እና የታዋቂና ተፅዕኖ ፈጣሪ ግለሰቦች ተወካዮች ተሳትፈዋል።

# ሠላምና ትብብርን የሚያጎለብቱት በዓላት

**ታደሠ ብናልፈው**

ሃይማኖታዊ ሥርዓትና በሕዝባዊ ትዕይንቶች ደምቀው የሚከበሩ በዓላት ሠላምን የሚሰብኩ፤ ጥላቻን የሚጠየፉ፤ መነቃቀፍ፣ መጠላለፍ፣ መገዳደልን ለሰው ልጅ ይቅርና ለዱር ፍጥረታት የማይመኙ፤ የአንድነት፤ የእኩልነት፤ የፍትሕ ቅኝትና ዜማ፤ ውዳሴና በረከቶች ናቸው።

ኢትዮጵያ ሳቢ የበዓላት የአከባበር ሥርዓት፣ ጣፋጭ የበዓል ማድመቂያ ዜማዎች፤ የተጣላን አስታርቆ፣ የተበተነውን ሰብስቦ፣ የተቸገረውን መጽውቶ፤ ሀገር የሚያፀናና ትውልድን የሚያሻግር ትውፊት ያላቸው የበርካታ በዓላት ባለቤት ነች። በጋራ በዓላት እንዳሉ ሁሉ የሙስሊምን በዓል ኦርቶዶክሱ አድምቆ፤ የኦርቶዶክስ በዓላትን ወንድም ሙስሊሙ አጅቦ፤ በኢሬቻንም ደምቆና በጋራነት የሚያከበር ማኅበረሰብ መኖሩ ለኢትዮጵያውያን አዲስ አይደለም።

በዓላትን ለማክበር ደግሞ ሠላም ወሳኝ ነው። ከሌሎ ሀገርም፤ ሕዝብም፤ ሃይማኖትም የለምና ወንድማማችነት፣ ለሠላም ዘብ መቆምና መተባበር አስፈላጊ መሆኑ አያጠያይቅም።

የኢትዮጵያ የአደባባይ የሃይማኖትና ሕዝባዊ በዓላት ዓለም የሚታደምባቸው፤ ከመሆን አልፈው ነፃነታቸውንና ሠላማቸውን እንደዓይን ብሌን በማየት ሊያውኳቸው የሚሞክሩ ተግባራትን፤ ዝርፊያዎችን፤ ንጥቂያዎችን፤ ማታለሎችን በመከላከል ማሳተፉ የሁልጊዜም የቤት ሥራ ነው።

የጀሞ ደብረ ሠላም መድኃኒዓለም ቤተክርስቲያን አስተዳዳሪ አባ መላከብርሃን ሙላት ከበቤ በሰጡት አስተያየት፤ ኢትዮጵያ ስለሠላም የሚሰብኩ፤ የሰው ልጅ እኩል በመሆኑ ማንም የበላይ ማንም የበታች አለመሆኑን የሚያስተምሩ፤ ሠላምን የሚያውጁ ሃይማኖታዊና ሕዝባዊ በዓላት ያሏት ትልቅ ሀገር ናት ይላሉ። በመሆኑም ታሪካቸው የሆኑ ሃይማኖታዊና ሕዝባዊ በዓላትን በሠላም ማከበር ተገቢ መሆኑን ያነሳሉ።

በዓላት አስተምህሮአቸው አንድነት፤ ይቅርባይነት፤ መከባበር፤ ፍቅርና መዋደድ ነው፤ በቀጣይ የሚከበሩ በዓላትን ይዘታቸውን፤ ትውፊታቸውን ጠብቀን፤ አስተምህሮታቸውን አክብረን ማሳለፍ አለብን ሲሉ ይናገራሉ።

ከትውልድ ወደ ትውልድ እየተከበሩ የመጡ በዓላት ናቸው፤ ዛሬም እንደ ትናንቱ በሠላም እንዲከበሩ ማኅበረሰቡ ትልቁን ድርሻ መወጣት እንዳለበት ያስረዳሉ። በበዓላት ጊዜ የሚፈጠሩ ግጭቶች በዓል አከባሪውን ብቻ ሳይሆን ሁሉንም የሚጎዱ በመሆናቸው በ2017 ዓ.ም የምናከብራቸው በዓላትን ሠላማቸው የተጠበቀ ማድረግ ይገባል ሲሉ ምክራቸውን ለግሰዋል።

በሀገሪቱ የተከሰቱ የሠላም መደፍረሶች ሕዝቡ ስለሠላም አስፈላጊነት የሚረዳበትን መንገድ ላይ በአግባቡ ባለመሠራቱ የመጣ ነው የሚሉት አባ መላከብርሃን፤ በሀገሪቱ ከማዕዘን እስከ ማዕዘን ፍፁም የሆነ ሠላም ለማምጣት ከልብ መሥራት የሚጠይቅ በመሆኑ፤ በሠላም ዙሪያ ውጤት ለማምጣት ከልብ መሠራት እንዳለበት ያስረዳሉ።

በ2017 ዓ.ም የሚከበሩ በዓላት ትውፊታቸውን በጠበቀ መልኩ በሠላም እንዲከበሩ የሁሉም ማኅበረሰብ ኃላፊነት ነው፤ የሃይማኖት አባቶች ሠላምን ማስተማር፤ ወጣቱም የሃይማኖት አባቶችን በማክበርና መልዕክታቸውን በመስማት ሠላምን ማስከበር እንዳለበት ይጠቁማሉ።

የሀገር ሽማግሌዎች፤ ወላጆች ልጆችን ማስተማርና ሥነምግባር እንዲኖራቸው ማረቅ አለባቸው ያሉት የሃይማኖት አባቱ፤ እርስ በእርስ እየተረዳዱ ችግሮችን የማለፍ ጥበብን አጠናክሮ መቀጠል እንደሚገባም ነው የሚገልጹት።

የሃይማኖት አባት የሆኑት ሀጂ ተሻለ ኪሮ በበኩላቸው፤ የኢትዮጵያ የሃይማኖትና ሕዝባዊ በዓላት ሠላም የሚያውጁ፤ ስለ በአብሮነትና ለኅብረ ብሔራዊነት አንድነት የተመቹ ናቸው ይላሉ።

ሠላም ለሀገር ኢኮኖሚያዊ፤ ፖለቲካዊ፤ ማኅበራዊ እድገት የሚጫወተው ሚና ትልቅ ነው፤ እኔና ለእኔ ብቻ የሚለው ሃሳብ ሀገር ያጠፋል፤ በመሆኑም የጋራ ተጠቃሚነትን በማጎልበት እኛነትን ማጎልበት ለሰላም ወሳኝ ድርሻ አለው ሲሉ ያስረዳሉ።

ልማትን ለማስቀጠል፤ በዓላቶችን በአንድነት፤ በፍቅር ማክበር አስፈላጊ መሆኑን ጠቁመው፤ በኢትዮጵያ በሚገኙ ቤተ-እምነቶችና ብሔር ብሔርሰቦች በዓላትን እንደየባሕልና ወጋቸው ተሰባስበው በጋራ ሊያሳልፉ እንደሚገባም መልዕክታቸውን ያስተላልፋሉ።

በዓላት በአንድ ማዕድ የሚያቋርሱ፤ በደስታና በመከራ ጊዜ በአብሮነት ለመቆም መነሻ የሆኑ የአንድነት ጌጦች ናቸው ያሉት የሃይማኖት አባቱ፤ በዓላት ዛሬም ነገም ትውፊታቸው ተጠብቆ እንዲከበሩ ማድረግ የሁልጊዜም የቤት ሥራ ነው ሲሉ ሃሳባቸውን ሰጥተዋል።

በ2017 ዓ.ም የሚከበሩ ሃይማኖታዊና የብሔር ብሔረሰቦች በዓላት ሠላማቸው በተጠበቀ መንገድ እንዲከበሩ ወጣቱ በብሔር፤ በቋንቋ፤ ሳይለያይ በአንድነት መቆም አለበት ሲሉ አስረድተዋል።

ከትውልድ ወደ ትውልድ እየተሻገረ የመጣውን አንድነት መጎልበት እንዳለበት አንስተው፤ በዓላት ሲከበሩ የአንዱን ሠላም አንዱ የሚጠብቅበትን አካሄድ ማጠናከር፤ የኢኮኖሚ አቅም ያነሳቸውን የመደገፉ ልምድ ማሳደግ አስፈላጊ መሆኑን ያመላክታሉ።

ሳቁንን ደስታውን በጋራ በማድረግ በቀጣይ የሚከበሩ በዓላትን የፍቅር ማድረግ እንደሚገባም አባታዊ ምክራቸውን ለግሰዋል።

በቀጣይ የሚከበሩ የአደባባይ በዓላትንም ትውፊታቸው ሳይሸረሸር፤ ይዘታቸው በተጠበቀ መልኩ እንዲከበሩ፤ የሃይማኖት አባቶች ከፖለቲካና ከፅንፈኝነት ነፃ ሆነው ዜጎችን ላይ የሠላም አዋጅ ማወጅና በሠላም የማስከበር ኃላፊነት እንዳለባቸው አስረድተዋል።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ይቅርና ዓለም ለማክበር በጉጉት የሚናፍቃቸው ሃይማኖታዊ የአደባባይ በዓላት ላይ ረብሻ የሚያነሳ ሰው በእምነት የጎደለ ነው፤ ሁሉም እንደየሚከተለው ሃይማኖት እምነቱን አጥብቆ ሠላምን መከተል ይገባል ሲሉ ተናግረዋል።

በ2017 ዓ.ም የምናከብራቸው በዓላት በሠላም እንዲከበሩ ወጣቱ ትልቅ ኃላፊነት አለበት፤ ሁሉም ማኅበረሰብ በእኔነት ስሜት ሠላምን ማስከበር ይገባዋል ይላሉ።

በኢትዮጵያ የሚከበሩ በዓላት የአንድነትና የፍቅር ተምሳሌቶች ናቸው ያሉት ደግሞ የፊንፊኔ ቱሌማ አባ ገዳዎች ሰብሳቢ ሰቦቃ ለታ ናቸው።

ዘመን መለወጫ፤ መስቀል፤ ኢሬቻ፤ ኢድአልፈጥር፤ ጥምቀትና ሌሎችም ሃይማኖታዊና ሕዝባዊ በዓላት ሠላምን የሚያስተምሩ፤ አንድነትን የሚያፀኑ፤ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ እድገትን የሚያስመዘግቡ መሆናቸውን ያስረዳሉ።

በዓላት ፍቅርና ሰላምን በማስተማር አንድነትን አፅንተዋል፤ አንዱ ለአንዱ በችግርና በደስታ እንዲቆም ጠንካራ ባሕል ገንብተዋል። ባሕላቸውንና ትውፊታቸውን ለማስቀጠል ትውልዱ መሥራት እንደሚገባ ይጠቁማሉ።

ሠላም ካለ ሀገር፤ እምነት፤ እድገት፤ ባሕል አለ፤ ሠላም ለሁሉም ነገር መፍቻ ቁልፍ ነው፤ ወጣቶች በቀጣይ በሚከበሩ በዓላት ላይ ሠላም የማስከበር ሥራ መሥራት አለባቸው ይላሉ።

በ2017 ዓ.ም የሚከበሩ በዓላት ልክ እንደወትሮው ሠላምን የሚያውጁ፤ በዩኒስኮ የተመዘገቡ፤ የአንድነት፤ የፍቅር፤ የመከባበር፤ የአብሮነት መገለጫችን በመሆናቸው በሠላም እንዲከበሩ ሁሉም መሥራት እንዳለበት መልዕክታቸውን ያስተላልፋሉ።

ከአዲስ አበባ ምግብና መድኃኒት ባለሥልጣን
ጋር በመተባበር በየ 15 ቀኑ የሚታተም

# በዓለም አቀፍ ተወዳዳሪ ለመሆን የተሰጠ ሥልጠና

ስሜነህ ደስታ

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ምግብ መድኃኒት ባለሥልጣን ከኢትዮጵያ ምግብና መድኃኒት ባለሥልጣን ጋር በመተባበር ከማዕከል እስከ ቅርንጫፍ ለሚገኙ ለዘርፉ የቁጥጥር ባለሙያዎች እና አመራሮች በምግብ ፣ መድኃኒት እንዲሁም ተቋማት ጥራትና ደህንነት ቁጥጥር ዙሪያ ከሐምሌ 30 ጀምሮ በሶስት ተከታታይ ዙር በአዳማ ከተማ ሲሰጥ የቆየው የአቅም ግንባታ ሥልጠና ነሐሴ 18 ቀን 2016 ዓ.ም. ተጠናቋል፡፡

ከባለሥልጣኑ ማህበራዊ ድረ ገጽ በተገኘው መረጃ በማጠቃለያ ፕሮግራሙም ላይ ሰልጣኞች እንዳሉት « የተሰጠው ሙያዊ ሥልጠና ከሪፎርሙ በኋላ በተቀናጀ ሁኔታ የተሰጠ ሥልጠና ስለሆነ፣ በተሰጠን ሥልጠና ጥሩ ባለሙያ በመሆን የከተማችንን ገፅታ ለመገንባት መሥራት ይገባናል» ብለዋል፡፡ በሥልጠናውም ሳይንሳዊ ዕውቀት ማግኘታቸውንና ዕውቀትና ሙያቸውን ለማሻሻል እንደሚያግዛቸው ገልጸዋል።

የባለሥልጣን መሥሪያ ቤቱ ዋና ሥራ አስኪያጅ ወ/ሮ ሙሉእመቤት ታደሰ በበኩላቸው በጥቂት ባለሙያዎች ተቋሙ በብልሹ አሠራር የሚነሳ መሆኑን አውስተው፣ ከዚህ ችግር እንዴት መውጣትና መታገል እንደሚገባ ማጤን እንደሚያስፈልግ ጠቅሰዋል፡፡ መሰል የአቅም ግንባታ ሥልጠናዎች ተጠናክረው እንደሚቀጥሉ አሳስበዋል፡፡ በተቋሙ ራዕይ ላይ አንድ መሆንና የአመለካከት ለውጥ ማምጣት እንደሚገባና ተቋሙን ለመቀየር የሁሉም ኃላፊነት መሆኑን በመገንዘብ ያላሰለሰ ጥረት ማድረግ እንደሚያስፈልግ መልዕክት አስተላልፈዋል።

ይህን ስልጠና በተመለከተ በአዲስ አበባ ምግብና መድኃኒት ባለስልጣን ተቆጣጣሪ ባለሙያ፣ ሥልጣናውን በማስተባበርና በማሰልጠን የተሳተፉትን አቶ ሞላ ታደለን አነጋግረናቸዋል፡፡ የሰጡት ምላሽም እንደሚከተለው አቅርቧል፡፡

አቶ ሞላ በቅድሚያ ስለስልጠናው አስፈላጊነት ሲያስረዱ፣ ከተማዋ የምትፈልገው የተሻለ የአገልግሎት አሰጣጥን ለማጠናከርና የአመራሩንና የባለሙያውን አቅም ለመገንባት ስልጠና ቁልፍ እና ወሳኝ ጉዳይ መሆኑን ይናገራሉ፡፡ ወቅቱ የ2017 በጀት ዓመት የዝግጅት ምዕራፍ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ አመራር እና ባለሙያውን ማብቃትና ማዘጋጀት፣ ለተግባር ምዕራፉ በእጅጉ ጠቃሚ መሆኑ ስለታመነበት ስልጠናው መሰጠቱን ያስረዳሉ፡፡ አቅም ከመገንባት ባሻገርም እንደ ከተማም፣ እንደ ሀገርም ሆነ እንደ ዓለም አቀፍ ያለንን ተወዳዳሪነት ለማሳደግ ለተቆጣጣሪ ባለሙያዎችና አመራሮች ስልጠና መስጠት አስፈላጊ መሆኑንም አጽንኦት ሰጥተው ይገልጻሉ።

ለዚህም ምክንያት ሲያስቀምጡ አንድ ቁጥጥር የሚያደርግ ተቋም ሊያሟላቸው ከሚገቡ ዓለም አቀፍ ስታንዳርዶች አንዱ ከአቅም ግንባታ አኳያ ባለሙያዎች በየጊዜው ወቅቱን ያማከለ ግንዛቤና ዕውቀት እንዲኖራቸው ስልጠናዎች መውሰዳቸው ነው በማለት ያስረዳሉ፡፡ ይህ በሚሆንበት ጊዜ በዚያች ሀገር የሚመረት ምርትና አገልግሎት የተሻለ ጥራትና ደህንነቱ የተጠበቀ ይሆናል የሚል እሳቤ አለ፡፡ ይህ ሲሆን በገበያ ደረጃ ተወዳዳሪነት ያድጋል፤ ምርቶችም ተፈላጊ ይሆናሉ፡፡

ለአብነት ሲጠቅሱም በሀገር ውስጥ የምናመርታቸው ምርቶች በዓለም ገበያ ላይ ተወዳድረው ገበያ እንዲያገኙና ተቀባይነት እንዲኖራቸው ‹‹ማቹሪቲ ሌቭል 3›› በሚል የዓለም ጤና ድርጅት ያስቀመጣቸው ስታንደርዶች አሉ። በአፍሪካ አህጉር ተቆጣጣሪ አካላትን በመመዘን ስታንዳርዱን አሟልተው ‹‹ማቹሪቲ ሌቭል 3›› ደረጃ የደረሱ ሀገራት ስድስት ብቻ ናቸው፡፡

ኢትዮጵያ ከስድስቱ ሀገራት ውስጥ የለችበትም። በሀገር ደረጃ የተያዘው ግብ በአጭር ጊዜ ውስጥ ስታንዳርዱን በማሟላት ወደ ‹‹ማቹሪቲ ሌቪል 3›› ለመድረስ ነው፡፡ ኢትዮጵያ ማቹሪቲ ሌቪል 3 ደረጃ ከደረሰች በሀገር ውስጥ የሚመረተው ክትባት ፣ የምግብ ምርቶች እንዲሁም ሌሎች ምርቶች በዓለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነት እንዲኖራቸው ያስችላል፡፡

እንደ እሳቸው አገላለጽ በማቹሪቲ ሌቪል 3 ስታንደርድ ውስጥ ከሚጠየቁ ጥያቄዎች አንዱ ከአቅም ግንባታ አንጻር የቁጥጥር ባለሙያዎች በሙያቸው በንድፈ ሃሳብ ደረጃ ምን ያህል ዕውቀትና ግንዛቤ አላቸው? በየጊዜው ስልጠናዎች ይወስዳሉ ወይ? ሰልጣኞች ምን ያህል አቅም እንደገነቡ ይለካሉ ወይ? ወዘተ. የሚሉት ናቸው። ስለሆነም ለቁጥጥር ባለሙያዎችና አመራሮች ስልጠናው መሰጠቱ ወሳኝ ነው፡፡

ሥልጠናው በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ምግብና መድኃኒት ባለሥልጣን በኩል በሶስት ዙር በሚሰጥበት ወቅት በፌዴራል ምግብና መድኃኒት ባለሥልጣን አስተባባሪነትና የበጀት ድጋፍ ተደርጎለታል፡፡ ተሳታፊዎቹ ደግሞ ከአዲስ አበባ ምግብና መድኃኒት ባለሥልጣን የተመረጡ ሶስት መቶ የሚሆኑ ከማዕከል እስከ ቅርንጫፍ የሚገኙ በቁጥጥርና በብቃት አሰጣጥ (ማረጋገጥ) ላይ የሚሠሩ አመራሮችና ባለሙያዎች ናቸው። እንደ አቶ ሞላ ገለጻ ሥልጠናው በሶስት ዙር ማድረግ ያስፈለገበት ዋናው ምክንያት ባለሥልጣኑ የሚያከናውናቸው የቁጥጥር ሥራዎች እንዳይስተጓጎሉ እንዲሁም የሥራ ስምሪቱን ጤናማ ለማድረግ በማሰብ ነው፡፡

ሥልጠናው ሲሰጥ በሁለት ቡድን የተዋቀረ ነው፡፡ አንደኛው የምግብ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ የመድኃኒትና የተቋማት በሚል የተከፈለ ነው። በእያንዳንዱ ቡድን ከ45 እስከ 50 ሰልጣኞች ተሳትፈውበታል፡፡ በሁለቱም ቡድኖች የተሰጡት ይዘቶች ተመሳሳይ ሲሆኑ ለየት የሚሉት ነገሮች ማሳያዎቹ ናቸው ይላሉ አቶ ሞላ፡፡

በሥልጠናው የተካተቱት ይዘቶቹ ሰባት ዓይነት ናቸው፡፡ እነሱም የመጀመሪያው የቁጥጥር መርሆዎችና ዘዴዎች ዘርዘር ብለው የቀረቡበት ሲሆን መርሆዎቹና ዘዴዎቹ ምን እንደሆኑ ከቀረበ በኋላ በባለሥልጣኑ መሥሪያ ቤት እንዴት ተግባራዊ እንደሚሆኑ ማብራሪያ ተሰጥቶበታል፡፡ ሁለተኛው ጥራትን ማስተዳደርና ማስጠበቅ በተመለከተ ነው፡፡ በዚህ ሥልጠና ባለሥልጣኑ የምርቶችና የአገልግሎቶች ጥራትን እንዴት ማረጋገጥ እንዳለበት እንዲሁም ጉድለቶች ሲገኙ እንዴት መስተካከል እንደሚገባቸው የታየበት ነው፡፡

ሶስተኛው የአዋጅ 1112/2011 መሠረታዊ ይዘቶችንና አፈጻጸማቸው በተመለከተ ነው፡፡ የአዋጁን መሠረታዊ ይዘቶች ተግባራዊ ከማድረግ አኳያ ምን ተግዳሮቶች እንዳሉ፤ ምን መልካም አጋጣሚዎች እንዳሉ ግንዛቤ የተሰጠበት ነው፡፡ አራተኛው ስጋትን መሠረት ያደረገ የቁጥጥር ሥነ ዘዴ(ስልት) የሚል ይዘት ያለው ሲሆን በዚህም መሠረታዊ መርሆዎቹን በተመለከተ ግንዛቤ እንዲሰርጽ ተደርጓል፡፡

ከአራቱ በማስከተል በአምስተኛነት የገበያ ቅኝት በተመለከተም ሥልጠና ተሰጥቷል፡፡ በዚህም አንድ ምርት በሚመረትበት ቦታ ብቻ ቁጥጥር ማድረግ በቂ ስላልሆነ፣ ተመርቶ ወደ ማህበረሰቡ በሚከፋፈልበትም ወቅት የጥራት እንዲሁም የደህንነት ጉድለት ሊያጋጥመው ይችላል፡፡ ስለሆነም በቁጥጥር ባለሙያ ተገቢ የሆነ የገበያ ቅኝት ለማድረግ ምን ላይ ትኩረት ማድረግ እንደሚገባ ፣ እንዴት ነው ቅኝት የሚደረገው ፣ ቅኝቱ የሚሰጠው ጥቅም ፣ ወዘተ. በሚሉ ርዕሰ ጉዳዮች ዙሪያ ግንዛቤ ተሰጥቷል።

ስድስተኛው የባለሙያዎች የሥነ ምግባር መርሆዎች ምን መምሰል እንደሚገባቸው የተሰጠው ሥልጠና ነው፡፡ በዚህም እንደ ሲቪል ሠራተኛ፣ እንደ ተቋም እና እንደ ቁጥጥር ባለሙያ መከተል ስለሚገባው ሥነ ምግባር የተነሳበትና ግንዛቤ የተሰጠበት ነው፡፡ በሰባተኛነት ደግሞ የትምባሆ ሕግና ቁጥጥር በተመለከተ የተሰጠ ሥልጠና ነው። በዚህ ሥልጠና በከፍተኛ ደረጃ በማህበረሰቡ ዘንድ የጤናም የአካልም ጉድለት እያስከተለ ስላለው ስለአደገኛው ትምባሆ ምርት ባህሪ ግንዛቤ ተሰጥቷል፡፡

በተጨማሪም የትምባሆ ምርትን በተመለከተ ዓለም አቀፍ ሕጎችና የሀገሪቱ ሕጎች ምን ይላሉ የሚሉትን እውቀት በመስጠት ለቁጥጥሩ አጋዥ በሚሆን መልኩ ሥልጠና እንደተሰጠ አቶ ሞላ ዘርዘር አድርገው ነግረውናል፡፡

የሥልጠናው አስተባባሪና አሰልጣኝ እንደሚሉት በንድፈ ሃሳብ ደረጃ ሥልጠና በሚሰጥበት ወቅት ሰልጣኞች የነበራቸው ተሳትፎ ከፍተኛ እንደነበረ አንስተዋል፡፡ ለዚህ ደግሞ እንደዋነኛነት የሚነሳው ሥልጠናው ለሙያቸው በቀጥታ የሚያግዝ ከመሆኑ በተጨማሪ በሥራው ላይ ያሉ ሰዎች ተሞክሯቸውን የሚያቀርቡበት ስለነበረ መሆኑን ገልጸዋል፡፡ በቡድን የተደረጉ ውይይቶች ከፍተኛ ግንዛቤ ለማግኘት የረዱ ከመሆናቸው በተጨማሪ ተሳትፎ ለማድረግም አግዘዋል፡፡

በመጨረሻም በቡድን የተደረጉ ውይይቶች ሪፖርት በጋራ መድረክ እየቀረቡ የሰልጣኞች ተሳትፎ እንዲኖር መደረጉን አስረድተዋል፡፡ በዚህም በስልጠናው ሰልጣኞች ከፍተኛ ልምድ የወሰዱበት፣ እርስ በእርስ ለመማማር የቻሉበት ከመሆኑ በተጨማሪ ከስህተት ለመታረምና ለመማር የነበረ ፍላጎት ከፍተኛ እንደነበረ ታይቷል ብለዋል፡፡

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ምግብና መድኃኒት ባለሥልጣን የቁጥጥር ባለሙያና የሥልጠናው አስተባባሪና አሰልጣኝ አቶ ሞላ በሥልጠናው ዙሪያ ባስተላለፉት መልዕክት እንዳሉት አንድ ባለሙያ ስለሚሠራው ሥራ በንድፈ ሃሳብ ደረጃ ብቁ ሆኖ መረጃ ሊኖረው ያስፈልገዋል። ከዚህ አንጻር በባለሥልጣኑ የሰለጠኑት የቁጥጥርና የብቃት ማረጋገጥ ባለሙያዎችና አመራሮች በሰለጠኑት አግባብ ላልሰለጠኑት የሥራ ባልደረቦቻቸው መረጃዎችን ማጋራት ይጠበቅባቸዋል፤ እንዲሁም ተሞክሮ ሊሆን በሚችል መልኩ በተግባር ማስተላለፍ ይገባቸዋል ብለዋል፡፡

ባለሙያዎቹም በጋራ በመረዳዳት ባገኙት ዕውቀት በመታገዝ የከተማዋን ነዋሪዎች የአገልግሎት ፍላጎት ልዩ ትኩረት ሰጥተው ተገቢ በሆነ አግባብ እንዲያገለግሉ አሳስበዋል፡፡ ብዙ ጊዜ ሳይርቅ ያልሰለጠኑት ባለሙያዎች ከሰለጠኑ ባለሙያዎች ከሚያገኙት መረጃ በተጨማሪ እንደ ሥራ ባልደረቦቻቸው ስልጠና የሚያገኙበት ሁኔታ እንዲመቻች ሃሳብ በመስጠት መልዕክታቸውን አጠናቀዋል፡፡



የሥልጠናው ተካፋዮች በከፊል ፤



አቶ ሞላ ታደለ ሥልጠና ሲሰጡ፣

# ርዕሰ አንቀፅ

## ኢትዮጵያውያን ለብሔራዊ ክብራቸው ያላቸው የሁሌ ዝግጁነት ጠላቶቻቸው እንደሚያስቡት አይደለም!

ኢትዮጵያውያን ረጅም ዘመን በሚቆጠረው የሀገረ መንግሥት ምሥረታ ታሪካቸው የማንንም ሀገር ብሔራዊ ጥቅም የሚጎዳደር ተግባር ፈጽመው አያውቁም። በነዚህ ጊዜያት ውስጥ በማንም ሀገር ላይ ጦር ሰብቀው የተንቀሳቀሱበት ጊዜ የለም። ይህ ከትልቁ ታሪካቸው ሰፊውን ምዕራፍ የሚሸፍን፤ ከማኅበረሰባዊ ማንነታቸው የሚቀዳ እውነታቸው ነው።

ስለ ሀገር ነፃነት፣ ፍትሐዊነት ያላቸው ቀናዒነት መሠረታዊ መገለጫቸው ነው፤ እንግዳን ተቀብሎ እግር አጥቦ እና አልጋ ለቆ ማስተናገድ በዘመናት መካከል የነበረ የማንነታቸው አንድ አካል ነው። ለጎረቤት ትልቅ ክብር መስጠት፤ ደስታን ሆነ ኃዘንን ተጋርቶ አብሮ ማሳለፍ ዛሬም ዋነኛ ማኅበረሰባዊ እሴታቸው ነው።

በዘመናት መካከል ብዙ ዋጋ በመክፈል ነፃነታቸውን አስጠብቀው ዘመናትን ያስቆጠሩ ሕዝቦች ናቸው። የነፃነት ተጋድሏቸው በቅኝ ግዛት ቀንበር ውስጥ ለነበሩ የአፍሪካ እና የላቲን አሜሪካ ሕዝቦች የአልገዛም ባይነትንና የነፃነት መነቃቃት መፍጠር የቻለ፤ እስከዛሬም የነፃነት ሰንደቅ ሆኖ ከፍ ብሎ የሚውለበለብ ነው፡፡

ከራሳቸው አልፈው ለፍትሕ እና ለነፃነት ለሚደረጉ ትግሎች አቅም በመሆን በግዞት ውስጥ ለነበሩ ሕዝቦች አሁናዊ ነፃነት ብዙ ዋጋ የከፈሉ ናቸው፤ ዛሬም ለነፃነት እና ለፍትሕ ካላቸው ቀናዒነት አኳያ ተመሳሳይ ዋጋ ለመክፈል ወደኋላ የሚሉ አይደሉም፤ በዚህም ዓለም አቀፋዊ አንቱታን ያተረፉ ናቸው።

ይህ ማኅበረሰባዊ ማንነታቸው በዚህም ትውልድ ማኅበረሰባዊ ስሪት ውስጥ ከፍ ያለ ስፍራ አለው፤ በተለያዩ ዓለም አቀፍ የሠላም ማስከበር ተልዕኮዎች ላይ ያለን ሀገራዊ ተሳትፎ፤ ከዛም ባለፈ፤ በጎረቤት ሀገሮች የሚፈጠሩ የሠላም እጦቶችን፤ ለመከላከል እየከፈሉ ያሉት የሕይወት መስዋዕትነት የዚህ ማኅበረሰባዊ ማንነታቸው ሌላው መገለጫ ነው።

ከሁሉም በላይ ስለሀገራቸው ካላቸው ቀናዒነት አኳያ፤ የሀገርን ሕልውና አደጋ ላይ የሚጥል ስጋት ሲፈጠር ልዩነታቸውን ጥለው አንድ ሆነው የነፃነታቸው ምልክት ስለሆነው ሰንደቅ ዓላማቸው መስዋዕት ለመሆን ያላቸው መነቃቃት በየዘመኑ የታየና አሁንም ከያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ውስጣዊ ማንነት ጋር በማይበጠስ ገመድ የተገመደ ነው።

ለኢትዮጵውያን የሀገር ጉዳይ የብዙ ትውልዶች የተሰናሰለ የመስዋዕትነት የታሪክ ትርክት ነው፤ በዛሬ ላይ ብቻ የሚሰላ ሳይሆን በብዙ ትናንቶች የተከፈሉ የሕይወት መስዋዕትነት እና ከመስዋዕትነቱ በስተጀርባ ያሉ የነፃነት እና የፍትሕ ማኅበረሰባዊ መሻቶች ድምር ውጤት ነው።

ይህም ሆኖ ግን ጠላቶቻችን እንደ ሀገር በውስጣዊ ችግሮቻችን የተከፋፈልን፤ ይህም ለብሔራዊ ሽንፈት እና መንበርከክ ክፍተት ይሆናል ብለው ባሰቡ ቁጥር፤ እንደ ሀገር ክብራችንን ሊያረክሱ፤ የነፃነት ትርክታችንን ለማጠልሸት ሲንቀሳቀሱ ማየት የተለመደ ነው። በዚህ ከታሪካችን ያለመማር የተዛባ ስሌት ለውርደትና ለከፋ ጥፋት የተዳረጉ ጠላቶቻችን ጥቂት አይደሉም።

ዛሬም ከዚህ ህያው ከሆነው ታሪካችን እና ብሔራዊ ማንነታችን መማር ያልቻሉ፤ በየዘመኑ እጆቻቸውን ከጥፋት መመለስ ያልቻሉ ጠላቶቻችን ዛሬም እንደሀገር ብሔራዊ ጥቅማችንን በሚነካ፤ ከዛም ባለፈ እንደሀገር በብዙ የሕይወት መስዋዕትነት የደመቀውን የትናንት የነፃነት ታሪካችንን ለማቆሸሽ መንቀሳቀስ ከጀመሩ ውለው አድረዋል።

እነዚህ ኃይሎች አንድም ከትናንት የሽንፈት ታሪካቸው መማር ባለመቻላቸው ተመሳሳይ ስህተት ለመፈጸም መነሳሳታቸው ፤ ከዛም ባለፈ አሁናዊውን ዓለም እና የሚገዛበትን ማኅበራዊ፤ ፖለቲካዊ እና ኢኮኖሚያዊ አስተሳሰብ ማስተዋል አለመቻላቸው በራሳቸው ላይ የሚፈጥሩት ችግር ከትናንት የከበደ እንደሚሆን ይታመናል።

ዘመኑ የሚገዛበት ማኅበራዊ፣ ፖለቲካዊ እና ኢኮኖሚያዊ አስተሳሰብ ፍትሐዊነት እና ከዚህ የሚመነጭ ሰጥቶ የመቀበል የጋራ ተጠቃሚነት ነው። በዘመነ ግሎባላይዜሽን/ዓለም ወደ አንድ መንደርነት እየተለወጠች ባለችበት አሁናዊ እውነታ/ከዚህ ውጪ መሆን በራስ ላይ አደጋ ከመጋበዝ ባለፈ ቆሞ ቀር የሚያደርግ ነው። ይህ ደግሞ ኪሳራው ምን ያህል እንደሚሆን መገመት አይከብድም።

በተለይም በዚህ ወቅት እንደ መንደር ጎረምሳ ብሔራዊ ጥቅሞችን ለማስጠበቅ ፉከራ እና ቀረርቶ ማብዛት፤ ከዚያም ባለፈ አካባቢያዊ ሠላምና መረጋጋትን ወደ ሁከትና ብጥብጥ ለመለወጥ ያዙኝ ልቀቁኝ ማለት፣ የገዛ ሀገርንና ሕዝብን ላልተገባ ብሔራዊ ውርደት እና ውርደቱ ለሚፈጥረው አንገት መድፋት መዳረግ ነው።

ኢትዮጵያውያን በየትኛውም ሁኔታ ውስጥ ቢሆኑ፤ በብዙ መስዋዕትነት ዛሬ ላይ ያደረሷትን ሀገራቸውን ሆነ ቀና ብሎ የሚያስኬዳቸውን ነፃነታቸውን እና ብሔራዊ ክብራቸውን ለማስጠበቅ ያላቸው የሁሌ ዝግጁነት ጠላቶቻችን እንደሚያስቡት አይደለም። ይህ አይነቱ ስሌት ለብዙዎች የውርደት፤ ለኢትዮጵያውያን ደግሞ የተጨማሪ ክብር ምንጭ ሆኗል።

የብዙ ባንዳዎች ዲስኩር እና የባንዳነት ተግባር ኢትዮጵያውያን ስለሀገራቸው እና ስለነፃነታቸው ያላቸውን ቀናዒነት የሚሸረሽረው አይደለም፤ በቀደሙት ዘመናት የነፃነት ተጋድሏቸው ወቅትም የብዙ ባንዳዎች ዲስኩር ፈትኗቸው እንደነበር አይካድም፤ ችግሩ ሁሌም የሚከተላቸው የጠላቶቻቸው ከንቱ የተስፋ ስንቅ ነው።

**አዲስ ዘመን**

ኢፕድ

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ**
ወርቁ ማሩ
Email:- workumaru2@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70

# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## በሀገር ላይ የተቃጡ ሴራዎችን ለመመከት በአንድነት ልንቆም ይገባል

ልዑል አበበ

ኢትዮጵያ የባሕር በር ለማግኘት ከሶማሊላንድ ጋር የመግባቢያ ስምምነት ከተፈራረመች ወዲህ የሶማሊያ መንግሥት ባለሥልጣናት ኢትዮጵያን በሚጎዳ ተግባር ላይ ተጠምደው ይገኛሉ፡፡ ይህን ተግባር ወደ ጠላትነት ከፍ አድርገውም በቅርቡ የግብፅን ጦር በራቸውን ከፍተው ተቀብለዋል፡፡ ከኢትዮጵያ ጋር ያላቸውን ልዩነት ማስፋትም የዘወትር ሥራቸው አድርገውታል፡፡ ብዙ ዋጋ እየከፈለች ከለላ ስታደርግላቸው የኖረችውን ኢትዮጵያን በመካድ ሩጫም ተጠምደዋል፡፡ የዚያድ ባሬን ስህተት ለመድገምም እየተጣደፉ ይገኛሉ፡፡

የኢትዮጵያ ሠላም አስከባሪ ኃይል ከሶማሊያ እንዲወጣ ከባድ ሴራ መጠንሰስ ከጀመረ ከራርሟል፡፡ ፕሬዚዳንት ሼህ ሐሰን ሞሐመድ በተደጋጋሚ ከካይሮ እስከ አሥመራ ብሎም እስከ ሪያድ ምልልስ ማብዛታቸው የማታ የማታ እውነቱን አደባባይ ይዞት ወጥቷል፡፡ መንግሥታቸው ለዓመታት ለሠላሙ መከበር ዋጋ ሲከፍል የኖረውን የኢትዮጵያ ሠራዊት እንደ ወራሪ ኃይል ለመክሰስ አቅም ሆኗቸዋል፡፡

ኢትዮጵያ ከ2006 ጀምሮ በሶማሊያ ያሰማራችው ሠላም አስከባሪ ኃይል ከፍተኛ መስዋዕትነት ከፍሏል፡፡ ሞቃዲሾን አስለቅቆ ጊዜያዊ መንግሥቱ በእግሩ እንዲቆም አስችሏል፡፡ እስከ ደቡባዊቷ ባይደዋ ከተማ ድረስ ዘልቆም የአሸባሪውን ቡድን አባላት በመደምሰስ ለሶማሊያ መንግሥትና ሕዝብ እፎይታን ሰጥቷል፡፡ ኢትዮጵያ ይህን ሁሉ ስትከውን ዓለም እጁን አጣጥፎ ዳር ቆሞ ነበር ሲመለከት የቆየው፡፡

ኢትዮጵያ ለሶማሊያ ሠላምና መረጋጋት በርካታ ጦር፣ ገንዘብና ቁስ ብትሰዋም በተቃራኒው ወራሪ አድርገው ጥላሸት ለመቀባት ሌትተቀን ሲለፉ ማየት አሳፋሪ ነው፡፡ የኢትዮጵያ ጦር በብዙ ግፊትና ጫና 2008 ላይ ሶማሊያን ለቆ ወጣ፣ በ2007 የአፍሪካ ኅብረት በሶማሊያ አሚሶም የተባለ የሠላም አስከባሪ ኃይል አሰማርቶ ነበር፡፡ ሆኖም የአሚሶም አቅም ውስን ስለነበር አልሸባብን እንዳይጠናከር ማድረግ አልተቻለውም፡፡

በኢትዮጵያ ጦር መስዋዕትነት ተዳክሞ የቆየው አልሸባብ ዳግም ማንሰራራት የጀመረው ያኔ ነበር፡፡ በሶማሊያ የተመሠረተው ጊዜያዊ የሽግግር አስተዳደር ጨርሶ ሳይጠፋ ማቆየት ቢቻልም የአልሸባብን ተደጋጋሚ የሽብር ጥቃት መግታት ከባድ ሆኖበት ነበር፡፡ ከጅቡቲ፣ ቡሩንዲ፣ ሴራሊዮን፣ ኬንያና ከዑጋንዳ የተውጣጣ ሃያ ሁለት ሺ የአፍሪካ ኅብረት ሠላም አስከባሪ ጦር በተሠማራባቸው ከ2010 ጀምሮ በዘለቁት ዓመታት የአልሸባብ ጥቃት አይሎ ታይቷል፡፡ በዚህ የተነሳ እንደ አሜሪካ ባሉ ሀገራት ይሁንታና በራሱ በሶማሊያ መንግሥት ፍላጎት ኢትዮጵያ ከ2013 ጀምሮ የሠላም አስከባሪ ኃይሏን ዳግም አዝምታለች ፡፡

የኢትዮጵያ ጦር በተናጠል ወደ ሶማሊያ መሠማራቱ በፍጥነት የሀገሪቱ ፀጥታ ላይ መሻሻል እንዲታይ አድርጓል። በ2014 መጀመሪያ ኢትዮጵያ ሶማሊያ ውስጥ ያዘመተችው ሠራዊት በአሚሶም ተልዕኮ ስር እንዲካተት ፈቀደች፡፡ ከዚህ ጎን ለጎንም ከሶማሊያ መንግሥት ጋር በተናጠል ባካሄደችው ስምምነት ተጨማሪ ሠራዊት አዝምታለች፡፡

በ2022 ተልዕኮው በተጠናቀቀው አሚሶም ስርም ሆነ በተናጠልና በአፍሪካ ኅብረት የሽግግር ሠላም አስከባሪ ተልዕኮ (አትሚስ) ስር ኢትዮጵያ በሶማሊያ ሠላም የማስፈኑን ሥራ ቀጥላበታለች፡፡ የአትሚስ ተልዕኮ በ2024 መጨረሻ ሲጠናቀቅ በሌላ ሠላም አስከባሪ ኃይል እንደሚተካ ይጠበቃል፡፡

ይህ ሊሆን በተቃረበበት በዚህ ወቅት ግን ፕሬዚዳንት ሐሰን ሼህ ሞሐመድ ከግብፅ ጋር በኢትዮጵያ ላይ ሴራ ሸረቡ። ሰውየው የበትረ መንግሥታቸውንና ቤተመንግሥታቸው (ቪላ ሶማሊያ) ዘብ የሆነውን የኢትዮጵያ ሠራዊት ወራሪ ኃይል አድርገው በመሳል በፖለቲካ ሴራ መጠመዳቸውን በመጀመሪያው ዙር የሥልጣን ዘመናቸው ደጋግመው አሳይተዋል፡፡ 2017 ላይ ግን በመሐመድ አብዱላሂ መሐመድ (ፋርማጆ) ተተኩ፡፡

ፋርማጆ የሶማሊያም ሆነ የአፍሪካ ቀንድ ቀንደኛ ጠላት እንደ አልሸባብ አይነት የሽብር ቡድን መሆኑ ቀድሞ ገብቷቸዋል፡፡ ለዚህም ነው ከአጋር አካላት ጋር ተባብረው አልሸባብ ላይ ጠንካራ ዘመቻ የከፈቱት፡፡ አልሸባብ በፋርማጆ የሥልጣን ዘመን በከፍተኛ ደረጃ ተዳክሞ ታይቷል፡፡ አልፎ አልፎ ጥቃት ቢፈፅምም የያዘው አካባቢ ተመናምኖ ውስን ቦታ ላይ ተገድቦ ነበር፡፡ በፋርማጆ ዘመን ፀረ አልሸባብ

> **ሼህ ሐሰን ከጎረቤት ሀገሮች እስከ ሩቅ ምስራቅ ጉብኝት ሲያደርጉ ግን ወደ ኢትዮጵያ ስመምጣት ስድስት ወራት እንደፈጀባቸው መረሳት የለበትም፡፡ ከኢትዮጵያ ታሪካዊ ጠላቶች ጋር ከማበር በተጨማሪ የዚያድ ባሬ የታላቋ ሶማሊያ ሕልም አቀንቃኝነታቸውም ኢትዮጵያን በበጎ ዓይን እንዳይመለከቷት ያደረገ ምክንያት መሆኑን መጠርጠር አይከፋም**

ዘመቻው የተሳካ ቢሆንም ሼህ ሐሰን ዳግም ወደ ሥልጣን መጥተዋል፡፡

ሼህ ሐሰን ከጎረቤት ሀገሮች እስከ ሩቅ ምስራቅ ጉብኝት ሲያደርጉ ግን ወደ ኢትዮጵያ ለመምጣት ስድስት ወራት እንደፈጀባቸው መረሳት የለበትም፡፡ ከኢትዮጵያ ታሪካዊ ጠላቶች ጋር ከማበር በተጨማሪ የዚያድ ባሬ የታላቋ ሶማሊያ ሕልም አቀንቃኝነታቸውም ኢትዮጵያን በበጎ ዓይን እንዳይመለከቷት ያደረገ ምክንያት መሆኑን መጠርጠር አይከፋም፡፡

ኢትዮጵያ ይህን ሁሉ ዓመት ለሶማሊያ ዋጋ ስትከፍል የት እንደነበሩ የማይታወቁ ኃይሎች ዛሬ ድንገት መጥተው «ሞታችንን ከሶማሊያ ጋር ያድርገው» ማለታቸው ሌላ መዘዝ ይዞ እንደሚመጣ የተረዱት አይመስልም። ኢትዮጵያ ያን ሁሉ መስዋዕትነት የከፈለችው ለሶማሊያ ሕዝብና ለቀጣናው መረጋጋት ነው፡፡

ሶማሊያ እንድትረጋጋና ጠንካራ መንግሥት እንዲኖራት ኢትዮጵያ ብዙ ለፍታለች፡፡ ከአልሸባብ ጋር ከመዋጋት አንስቶ የሶማሊያን ወታደሮች እስከ ማሠልጠንና ማስታጠቅ ጥረት አድርጋለች፡፡ ዛሬ ላይ ግን ኢትዮጵያን ከአልሸባብ በባሰ ጠላት አድርገው ፈርጀዋታል፡፡

የቀድሞው የአሜሪካ ፕሬዚዳንት ባራክ ኦባማ ኢትዮጵያን በጎበኙበት ወቅት «የኢትዮጵያ ሠራዊት ጠንካራና ጀግና ተዋጊ ነው» ሲሉ የሠላም አስከባሪ ኃይሉ በሶማሊያ ያሳየውን ስኬታማ ሥራ ለዓለም መስክረዋል፡፡

ይህን ታሪክ ዛሬ ገልብጠው ለመፃፍ የተነሱት የሶማሊያ መንግሥት ባለሥልጣናት ኢትዮጵያን የወረራ ስጋት ቀለበት ውስጥ ለመክተት እየተጣደፉ ነው፡፡ በጎረቤት፣ ወዳጅና የክፉ ቀን ደራሽ በሆነችው ኢትዮጵያ ላይ ይህን አይነት ቁማር መሥራት የትም እንደማያደርስ ግን ከታሪክ አልተማሩም፡፡

ኢትዮጵያ ለሶማሊያ የከፈለችውን ውለታ ወደ ጎን በመተው የሠላም አስከባሪ ኃይሏና መከላከያ ሠራዊቷን ስምና ዝና የማጠልሸት ሰፊ ዘመቻ ተከፍቷል፡፡ የተፈጠሩ አለመግባባቶችን በዲፕሎማሲ ጥረት በቱርኪዬ አማካኝነት ለመፍታት ጥረት እየተደረገ መሆኑ እየታወቀ ከቀጣናው ውጪ የሆኑ አካላትን ወደ አካባቢው ጦር እንዲያስገባ መጋበዝ ጠብአጫሪነት ነው፡፡

ይህን ኢትዮጵያን ጫና ውስጥ የመክተት ዘመቻ ኢትዮጵያ በዝምታ እንደማትመለከተው በውጪ ጉዳይ ሚኒስትር በኩል ከሳምንት በፊት የወጣው ጠንካራ መግለጫ ሊበረታታ የሚገባው ነው፡፡ ኢትዮጵያውያንም ይህን ሴራ ተረድተው በአንድነት ሊቆሙና ሊሰባሰቡ ይገባል፡፡

ኢትዮጵያውያን ለሶማሊያ ሠላምና አንድነት ሞተናል። ኢትዮጵያውያን ለሶማሊያ ያላቸውን ክብር ከማንም በላይ አሳይተዋል፡፡ በሶማሊያ የግዛት አንድነት ላይም የኢትዮጵያ መንግሥት ጥያቄ የለውም፡፡ የኢትዮጵያ ጥያቄ አንድና አንድ ነው፡፡ የባሕር በር ጥያቄ፡፡ ኢትዮጵያ በቀይ ባሕር የራሷ ወደብ እንዲኖራት ጥረት ማድረጓ ታሪክም ሆነ ዓለም አቀፍ ሕግ የሚደግፈው ነው፡፡ ይህም ተገቢነት ያለው ጥያቄ በሠላማዊ መንገድና በንግግር የጋራ ተጠቃሚነትን መሠረት ባደረገ መንገድ መፍታት ከዘመኑ ጋር መራመድ ነው ፡፡

# «ለርዳታ እጁን ዘርግቶ ርዳታ የሚወስድ አካል፣ ሞራል ኖሮት ከሌላው ጋር እኩል መቆምና መገዳደር አይችልም»

- አምባሳደር ሽፈራው ተክለማርያም(ዶ/ር)፣
የኢትዮጵያ አደጋ ስጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን ኮሚሽነር፣

ወንድወሰን ሽመልስ

**አመሠራረቱ፣ በሰብዓዊነት መርህ ተቃኝቶ፤ ለሰው ልጆች ችግር መፍትሔን፣ በመከራዎቻቸውም ወቅት ደርሶ መደገፍና እንባ ማበስን ማዕከል አድርጎ ነው፡፡ ምንም እንኳን በሚጠበቀው ልክ ሰርቷል ባይባልም፣ ላለፉት ሃምሳ ዓመታት አንድም ዜጎች ለችግር እንዳይዳረጉ ቀድሞ በማስገንዘብ፤ ሁለትም፣ ዜጎች አደጋ በገጠማቸው ጊዜ አፋጣኝ ምላሽና ድጋፍን በማድረስ፤ ሦስትም፣ ዜጎች ከችግሮቻቸው ባሻገር ሆነው እንዲገለጡ የመልሶ ማቋቋምን ተግባር ለመከወን ሲጥር ኖሯል፤ የኢትዮጵያ አደጋ ስጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን፡፡**

**ዛሬም እነዚህን ሦስት ተግባራት ሚዛን አስጠብቆ ለማስኬድ የሚገዳደረው መልከ ብዙ ፈተና ያለበት ቢሆንም፤ በፈተና አዙሪት ውስጥ ሆኖ ችግር ከማውራት ይልቅ፤ የችግሮቹን ምንጭ ለይቶ ለመፍትሔዎቻቸው መሥራትን እንደ አቅጣጫ ይዞ በመንቀሳቀስ፣ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን ተረጂነትን ታሪክ እንዲያደርጉ የሚያስችል የትግበራ መንገድ ስለመጀመሩ ይነገራል፡፡ በተለይ ሰብዓዊ ድጋፍን በራስ አቅም መከወንን ግቡ አድርጎ፤ በኢትዮጵያ ምድር የምግብ ዋስትናን ከማረጋገጥ ባሻገር የምግብ ሉዓላዊነትን የማረጋገጥ ዓላማን ይዞ እየሰራ ስለመሆኑም ይገለጻል፡፡**

**ታዲያ የዚህ መልካም ሕልምና ዓላማ ትልምን ከማሳካት አኳያ፤ እንደ ተቋም፣ እንደ ሀገር፣ እንደ ሕዝብና መንግሥት እሳቤውን ገዝቶ የድርሻን ከመወጣት አንጻር ምን አቅምና እድል አለ፤ ምንስ ፈታኝ ሁኔታዎችና የመፍትሔ አቅጣጫዎች ተለይተዋል፤ የሚሉ ጉዳዮችን በማንሳት፣ ከኢትዮጵያ አደጋ ስጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን ኮሚሽነር አምባሳደር ዶክተር ሽፈራው ተክለማርያም ጋር ያደረግነውን ቆይታ እንደሚከተለው አቅርበነዋል፡፡**

**አዲስ ዘመን፡- የአደጋ ስጋት ሥራ አመራር ምንድን ነው? በማንስ ይከወናል?**


**አምባሳደር ዶክተር ሽፈራው፡-** የአደጋ ስጋት ሥራ አመራር በሀገር ደረጃ ሲታይ የሰብዓዊ መብትን፣ ማህበራዊ ፍትህን፣ ብሔራዊ ደህንነትንና ዘላቂ ሰላምን የሚያቅፍ ነው፡፡ የአንድ መንግሥት የመንግሥታዊ ቅቡልነትን የሚያመላክትም ነው፡፡ ምክንያቱም፣ ዜጎች መንግሥት አለኝ ብለው እንዲያስቡ ከሚያደርጋቸው ጉዳይ አንዱ፣ በሚቸገሩበት ወቅት የሚታደጋቸው መኖሩ ነው፡፡ ስለዚህ አንዱ የአደጋ ሥራ አመራር አንዱ መገለጫው ለሕዝቦች መድረስ ነው፡፡

ሁለተኛው፣ ሁለንተናዊ እይታን መጠየቁ ሲሆን፤ ይሄም በሚዛናዊነት በቅድመ አደጋ፣ በአደጋው ወቅትና ከአደጋ በኋላ የሚሰሩ ሥራዎችን ማካተቱ ነው፡፡ ሦስተኛው፣ ሥራው ሁሉንም የሚመለከት መሆኑ ሲሆን፤ ማህበረሰቡን፣ የግልም ይሁን የመንግሥት ተቋማትን፣ የአስተዳደር እርከኖችን በሙሉ ማካተቱ ነው፡፡

ስለዚህ የአደጋ ስጋት ሥራ አመራር ስንል፣ ሁሉንም የሚመለከት፣ የሁሉም ኃላፊነት ያለበት፣ የሁሉንም ምላሽ የሚጠይቅ ተግባር ማለት ነው፡፡ በመሆኑም የአደጋ ሥራ አመራር ሀገራዊ ገጽታ አለው፤ የደህንነት ገጽታ አለው፤ መላው ማህበረሰቡም መጫወት ያለበትን ሚናም የሚያካትት ነው፡፡

**አዲስ ዘመን፡- የአደጋ ስጋት ሥራ አመራር በሀገራችን ምን ገጽታ አለው?**

**አምባሳደር ዶክተር ሽፈራው፡-** በሀገራችን የአደጋ ሥራ አመራር ኮሚሽን ተቋቁሞ መሥራት ከጀመረ 50 ዓመታት እየሆነው ነው፡፡ በ50 ዓመታት የሥራ ታሪክም በጎ ነገሮች እንዳሉ ሆነው፤ ጥሩ ያልሆኑ ነገሮችም ተተክለዋል። ለምሳሌ፣ የሰብዓዊነት ሥራ ዓለም አቀፋዊ እይታና ዓለም አቀፋዊ ግንዛቤ ነው፡፡ ነገር ግን ሰብዓዊነት ከዛ እያለፈ እየሄደ፣ ሰዎች ሲቸገሩ ከመደገፍ ባለፈ፤ ተረጂነትን እንዲለማመዱ፣ የማይመለከታቸውም ጭምር በሰብዓዊነት ማዕቀፍ ውስጥ


ፎቶ፡- ሐዲስ አብርሃ

እንዲታዩ የሆነበት ሁኔታም አለ፡፡

ሥራው 1960ዎቹ ሲጀመር፣ በተለይም የተቸገሩ ወገኖችን በመደገፍ፣ በሕይወትና ሞት መካከል ያሉ ሚሊዮኖችን የመታደግ ሥራ ተሰርቷል፡፡ የቅድመ ማስጠንቀቂያው ሥርዓትም ቀላል የሚባል አይደለም። በዚህም በተለያየ መንገድ (ለምሳሌ፣ በሴፍቲኔት እና በድንገተኛ መንገድ) ሰዎች ሲታገዙ መጥተዋል፡፡ በዚህ በኩል ሲታይ፣ የአደጋ ስጋት ሥራ አመራር ሥርዓታችን በሰብዓዊነት ላይ ሰፊ ሥራ ሰርቷል ማለት ይቻላል፡፡

በተለይም ከቅድመ አደጋ፣ በአደጋ ወቅት እና ከአደጋ በኋላ ተግባራት አኳያ ሲመዘን፤ በአደጋ ወቅት የነበሩ የተለያዩ ችግሮችን በመቅረፍ በኩል የማይናቅ ድርሻ ነበረው። ይሁን እንጂ በሂደት በተለይም በሀገራችን በአጼው ሥርዓት የተፈጠረው ከፍ ያለ የሰብዓዊ ቀውስ ንጉሱ ከሥልጣናቸው እንዲወርዱ ምክንያት የሆነበት አጋጣሚም ተፈጥሮ ነበር፡፡ በወቅቱ የሰዎችም፣ የበርካታ እንስሳትም ሕይወት ጠፍቷል። ሌሎች የኑሮ መሠረቶችና መሠረተ ልማቶች ወድመዋል፡፡

በሂደት ሰብዓዊነት በሁለት ተከፈለ፡፡ አንደኛው፣ ሰዎች የእለት ድጋፍ አግኝተው ሕይወታቸውን መታደግ የሚያስችል አሠራር ሲሆን፤ ሁለተኛው፣ ከድጋፍ እንዲወጡ የአይበገሬነት ግንባታ ላይ መታገዝ አለበት የሚለው አስተሳሰብ ነው፡፡ ይሄ እሳቤም የሰብዓዊ አያያዝ የዛሬውን ችግር ከመቅረፍ ባሻገር ካሉ ተግባራት አኳያም የራሱን እድገት እያሳየ፤ ሰብዓዊነት ሥራውም ልማትን፣ ሰብዓዊነት እና ዘላቂ ሰላምን ባጣመረ መልኩ እንዲከናወን እያስቻለም መጥቷል፡፡

**አዲስ ዘመን፡- በኢትዮጵያ ያለው የሰብዓዊ ድጋፍ አሠራር ከደጋፊነት ባሻገር የተረጂነት እሳቤነት እያጎለበተ መምጣቱ ይነገራል፡፡ ይሄን የተረጂነት እሳቤና አካሄድ እንደ ሕዝብና ሀገር ተጽዕኖው እንዴት ይገለጻል?**

**አምባሳደር ዶክተር ሽፈራው፡-** የሰብዓዊ ድጋፍን ከ1960ዎቹ ጀምረን ስናይ፤ ሰብዓዊነት መልኩን እየቀየረ ሄዷል፡፡ ለምሳሌ፣ የ1965/66ቱ ማህበረሰብን ለመታደግ የተደረገ ሰብዓዊነት ነው፡፡ ይሄ ድጋፍም በሀገር ውስጥ አቅም ሳይሆን፣ በአጋር አካላት ላይ የተንጠለጠለ ነው፡፡ ይህ እየተቀየረ መሄድ ነበረበት፡፡

ሆኖም ርዳታው ሰዎች ባልተቸገሩበት ሁኔታም ሲደረግ ስለነበረ፤ ሰብዓዊነት በሂደት ወደ ተረጂነት ዞረ፡፡ ሊደገፍ የሚገባውና የማይገባው የማይለይበት ሁኔታም ተፈጠረ። ይባስ ብሎ የርዳታ ድጋፍ የሚባለው ለተለያዩ ፍላጎቶች የሚታደል፤ የዘመድ አዝማድ መጠቀሚያ ሆነ፡፡ ለአቋራጭ ባለሀብትነት አቅም፤ የተለያዩ ፍላጎቶችን ማሳኪያ እየሆነ ሄደ። እናም በሂደቱ ሰብዓዊነት ቅርጽ እያጣ በብልሽት ውስጥ ላሉ ሰዎች መጠቀሚያ እየሆነ ብዙ ጉዳቶችን አስከትሏል፡፡

በዚህም፣ የመጀመሪያው ጉዳት፤ ሰው በጥረትና በታታሪነት ሊወጣው የሚችለውን እለታዊ ችግር፣ የዘላቂ ችግር ባለቤት እንዲሆን አደረገው፡፡ በዘላቂነት ከችግር እንዲወጣ የነበረውን አስተሳሰብ በመዋጮ ምክንያት ያለውን ጥሪት እየሸጠ እዛው እንዲሆን በመደረጉ፣ በተረጂነት የመኖር ፍላጎት እየገነነ ሄደ፡፡

ከዚሁ ጋር አያይዘን የምናየው ሌላው ጉዳት፣ የሀገረን ሰላምና ልማትን ከማወክ ጀምሮ፤ የራሳችን የመንግሥት መዋቅር የምንላቸውም አካላት በዚህ ውስጥ እየሰመጡ እንዲሄዱ አድርጓል፡፡ ከዚህ ተነስቶም የተቸገረ የሚኖር ቢሆንም፤ ይሄን የተቸገረ ከማሳወቅ አኳያ ቁጥሮች እጅጉን ተጋንነው የሌለ የተረጂነት ቁጥር ይነገር ጀመረ፡፡

ይሄ ቁጥርን አጋንኖ የማቅረብ ችግር የተቸገረን ሰው ቁጥር በአስር አባዝቶ ማቅረብ ችግር የለውም በሚያስብል ደረጃ የሚገለጽ ነው፤ ምክንያቱም በሺህ ተባዝቶ ሲቀርብ ተስተውሏል፡፡ ለዚህ ምክንያትም የሌለና ያልተፈጠረ ነገር ተፈጥሯል፤ በጣም ብዙ ሰው ተጎድቷል፤ በጣም ብዙ ሰው ተርቧል፤ በጣም ብዙ ሰው ሞቷል ይባላል፡፡ እንደዚህ እየተባለ የሚሄደው ነገር ደግሞ፤ ተመልሶ ለራስ ጥቅምና ለግል ፍላጎት ማስኬጃ ይውላል፡፡ በተለያዩ ትስስሮችም በየእህል ወፍጮ ቤት፣ በየገበያውና ሱቆች ያለማንም ከልካይና ጠያቂ፤ አንዳንዴም ሕጋዊ በሚመስል መንገድ በጠራራ ፀሐይ የሚቸበቸብበት ሁኔታ አለ፡፡

ስለዚህ ጉዳቱ፣ እንደ ማህበረሰብ ታታሪነታችንንና ሥራ ፈጣሪነታችንን በጣም ጎድቷል፡፡ ካጋጠመን የትኛውም ዓይነት ተፈጥሯዊም ይሁን ሰው ሠራሽ ችግር የሚሰራው ድራማም እንዲቀጥል አድርጓል፡፡ እናም ይሄኛው ገጽታው በጣም የተበላሸ ነው፡፡ ሀገር ክብሯ፣ ነፃነቷና ሉዓላዊነቷ ላይ ትልቅ ደንቃራ ፈጥሯል፡፡ ይሄም በንድፈ ሃሳብ ደረጃ የሚነገር አይደለም፡፡

በዚህ መልኩ በአንድ ሀገር ላይ ዜጎች በራሳቸው መንገድ የራሳቸውን ችግር መቅረፍ እያቃታቸው ሲሄድ፤ በየትኛው መንገድ አግዛለሁ፣ እደግፋለሁ የሚል ሰው በራሱ እና በተለያዩ ምክንያት መምጣቱ አይቀርም፡፡ ያ እየበዛ እየበረከተ ሲሄድ፤ የአንድ ሀገር ግማሽ እና አንድ ሶስተኛ በሚባል ደረጃ እየሰፋ ሲሄድ የሚያመጣው ችግር ። ይሄም ያ ሀገር በራሱ ፖሊሲ፣ በራሱ ሕገ መንግሥታዊ ሥርዓት፣ በራሱ ሕግና ደንቦች ሊመራ አይችልም፡፡

ምክንያቱም ደገፍኩ የሚለው አካል፣ እኔ በምለው መንገድ መታዘዝ አለብህ፤ እኔ ያልኩህን መተግበር አለብህ፤ የምትወስነው ውሳኔ፣ የምትሄድበት መንገድ እና የምታወጣው ፖሊሲ እኔ በምለው መንገድ ብቻ ነው የሚሆነው በሚል ቁጥጥር ያደርጋል፡፡ ይሄ ሲሆን ደግሞ ሀገር እንደ ሥርዓተ መንግሥት ሕገ መንግሥት ያላት፤ ሕግ እና ሥርዓት ያላት ልትመስል ትችላለች፡፡ በተግባር ሲታይ ግን ከሁሉም የወጣች ትሆናለች፡፡

በአፍሪካ ሀገሮች የምናየው ይሄንኑ ነው፡፡ በአፍሪካ ሀገሮች መንግሥታቱ አሉ ይባላል፤ የሚመሩት ግን ከሌላኛው ካፒታል ነው፡፡ መንግሥታት ገንዘብ አላቸው ይባላል፤ የገንዘቡ መጠን፣ የገንዘቡ ዓይነትና የገንዘቡ ጥንካሬ የሚለካው ግን በሌላኛው ካፒታል ነው፡፡ ይሄ በተለይም በምዕራብ አፍሪካ ሀገራት በግልጽ የሚታይ ነው፡፡ ስለዚህ ተረጂነት ስር እየሰደደ ሲሄድ፤ የዜጎችን የመሥራትና የመፍጠር ትልቅ ችሎታና አቅማቸውን እያኮሰሰው ይሄዳል፡፡ ሀገርንም እንደ ሀገር ነፃነትና ክብሯን፤ የዜጎችንም ክብር እና ሉዓላዊነትን እያኮሰሰ የሚሄድ ነው። ስለዚህ ሰብዓዊነት መልኩን ትቶ ወደ ተረጂነት ከተቀየረ የዜጎችንም ይሁን የሀገርን ህልውና ክፉ ነገር ውስጥ በማስገባት፤ ወደ ማይመለስበት አዘቅት እንዲወርድ የማድረግ አቅሙ በጣም ትልቅ ነው፡፡

ይሄ ከውጭ አካል አንጻር ሲታይ፤ ለምሳሌ፣ በ1885/86 ምዕራባዊያኑ አፍሪካን ለመቀራመት ተስማምተውና የፖለቲካ ውሳኔ ወስነው ተንቀሳቀሱ፡፡ ይሄ ሀገራችንን ጨምሮ አፍሪካን የማንበርከክ እቅድ ነበር፡፡ የ1940ዎቹ (1944 አካባቢ) የብሪቴን ዉድ ስምምነትም፣ ዓለም በሙሉ በዶላር ይመራ፤ ገበያውም ቢሆን በዶላር እንዲገዛ ይደረግ የሚል ነበር፡፡

በተመሳሳይ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ቻርተር ጣፋጭ በሚመስል ሃሳብ፣ «ሪስፖንሲቢሊቲ ቱ ፕሮቴክት» የሚል ነገርን አሰፈረ፡፡ ይሄ ማለት ደግሞ ሀገሮች ያላቸው ሉዓላዊነት ኃላፊነት ነው እንጂ መብት አይደለም የሚል ነው። በዚህ ድፍረት በተሞላበት አሠራር፣ በአንድ ሀገር በሆነ መንገድ ሰብዓዊ መብት ቢጣስ እና እነሱ ደግሞ ተጥሷል ብለው መደምደሚያ ላይ ቢደርሱ የሌላ ሀገር ጣልቃ የሚገባበት (ለመከላከያውም ጭምር በጸጥታው ምክር ቤት እያስወሰነ) ሁኔታ አለ፡፡

በመሆኑም ዓለም አቀፋዊ ሁኔታውንም ስናይ፣ የኢኮኖሚ ሉዓላዊነት፣ የምግብም ሉዓላዊነት የሚባል ነገር እንዳይኖር በማድረግ ለማንበርከክ ከመጀመሪያውም የተዘጋጀ ዓለም ላይ ተረጂነት ሲጨመርበት፤ ተጋላጭነታችንን በጣም ከፍ ያደርገዋል፡፡

ስለዚህ ተረጂነት መነሻውም መድረሻውም ህልውናንም ነፃነትንም ሉዓላዊነትንም የሚያሳጣ፤ ዜጎችንም በማይጨበጥ ተስፋ ውስጥ አስገብቶ በዘላቂነት የሚወጡበት ነገር ላይ ሳይሆን፤ በማጥ ውስጥ እንዲሰነብቱ የሚያደርግ አደገኛ ልምምድ ነው፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ኮሚሽኑ አዲስ ፖሊሲ ቀርጾ ወደ ተግባር መግባቱ፣ በዘርፉ የሚታዩ ችግሮችን ከመፍታት እና የሰብዓዊ ድጋፍ ለሚገባቸው ብቻ እንዲሆን ከማድረግ አኳያ ምን እድልና አቅም ይፈጥርለታል? ምን የማስፈጸሚያ ስትራቴጂስ ተቀምጧል?**

**አምባሳደር ዶክተር ሽፈራው፡-** በ2016 ዓ.ም የካቲት አጋማሽ ላይ፣ የአደጋ ስጋት ሥራ አመራር ፖሊሲ በአዲስ መንገድ በአዲስ ሁኔታ ተቀርጾ በሚንስትሮች ምክር ቤት ጸድቋል፡፡ የአደጋ ስጋት ሥራ አመራር ፖሊሲ ለሁሉም ነገር አቅጣጫ የሚሰጥና በር የሚከፍት በመሆኑ በሴክተሩ ለምናካሂደው መሠረታዊ የለውጥ ሥራዎች አንዱና የመጀመሪያው አቅም ነው፡፡

ይህንን የአደጋ ስጋት ሥራ አመራር ፖሊሲ ተከትሎም፣ የሕግ ማዕቀፎች እና የአደረጃጀት ክለሳዎች ተፈጥረው እየተሰራ ነው፡፡ የዚህ አንዱ ነጥብ፣ የአደጋ ስጋት ሥራ አመራር

ወደ ገጽ 7 ዞሯል

# ተጠየቅ

# «ለርዳታ እጁን ዘርግቶ ርዳታ...

ከ6ኛ ገፅ የዞረ

ሥርዓታችን መንግሥት መር መሆን አለበት፤ ሁለተኛው፣ ሕዝቡ በየደረጃው እና በያለበት ቦታ ላይ ድርሻውን የሚወጣ ሊሆን ይገባል፤ ሶስተኛው፣ የላይኛው አካል ድጋፍ በሚያደርግበት ጊዜ የታችኛው አካል የሚገባውንና የሚችለውን እያደረገ መሆኑን በማረጋገጥ ሊሆን ይገባል፤ ከዚህ ሲያልፍና ሲቸገር ደግሞ የእወጃ ወይም ይፋ የማድረግ ሥርዓትን ተከትሎ የመደጋገፍ ሂደት ይኖራል የሚል ነው፡፡

በዚህ ሂደት ላይ ቅጽበታዊ አደጋዎች ካልሆኑ በስተቀር፣ ዘገምተኛ ለሚባሉ የትኛውም አደጋዎች ምላሽ ሙሉ በሙሉ በየአካባቢው ሊሸፈን ይገባል የሚል ሲሆን፤ ቅጽበታዊ አደጋ ከሆነ ግን (እንደ ጎርፍ፣ የመሬት መንሸራተትና እሳት በሚነሳበት ጊዜ) የፌዴራል መንግሥት በኮሚሽኑ በኩል 30 በመቶውን፣ ቀሪውን 70 በመቶ ደግሞ ክልሎች ይችላሉ የሚል ነው፡፡ ይሄ ሁሉ ማዕቀፍ ተረጂነት እና ልመናን የማይፈቀድ እንዲሆን፤ በሂደቱ ግን ሰብዓዊ ድጋፍ የሚፈልጉ ወገኖች ስለሚኖሩ ለእነዚህ በራሳችን አቅም ለመደገፍ ዝግጅት እንድናደርግ የሚል አካሄድ ነው፡፡

ለዚህም፣ የመጀመሪያው የሰብዓዊ ድጋፍ ግንባር ተብሎ የሚወሰደው ማህበረሰቡ ራሱ ነው፡፡ በማህበረሰቡ ውስጥ በየቀበሌው ብዙ አቅም አለ፡፡ እናም በሕዝባችን ውስጥ ያለውን አቅም በማደራጀትና በማደጋገፍ፤ የሚቸገረውን በመለየት እና የተለየውን ደግሞ በእለታዊነትም ይሁን በዘላቂነት ከችግር ለማውጣት ዝግጅት ማድረግ አለበት። ይህንን ለማድረግ ደግሞ ወረዳ፣ ዞን፣ ክልልና ፌዴራል መዘጋጀት አለበት የሚል ሃሳብ አለ፡፡

ይህንን ለመሥራት የስትራቴጂክ ምግብ ክምችት (መጠባበቂያ ክምችት የምንለው) መያዝ ያስፈልጋል፤ የመጠባበቂያ ፈንድ ማደራጀት ያስፈልጋል፤ በማህበረሰብ ደረጃ የመተጋገዣ ሥርዓት መዘርጋት ያስፈልጋል፡፡ ከዚያ አልፎ እነዚህ የሚያዙባቸውን የመጋዘንና ሌሎች የተለያዩ ሥራዎችን ጭምር ማስቀመጥ ያስፈልጋል፡፡ ስለዚህ ለአደራሹም፣ መጠባባቂያ ክምችቱም፣ ለዚያ የሚያስፈልጉ የገንዘብና መሰል ሀብትም በየደረጃው ይደራጃል በሚል እየተሄደ ነው፡፡

ከዚያ አልፈን ስንሄድ ግን መሥራት ያለብን ዋና ዋና ጉዳዮች አሉ፡፡ የመጀመሪያው፣ ተረጂነት አጥፊ ነው፤ ክፉ ልምምድ ነው፤ አመንምኔ ነው የሚለው ላይ የጋራ አረዳድ መፍጠር ነው፡፡ ከዚያ ሰፈር ካልመጣ እዚህ የሚሰራ ነገር የለም የሚል አስተሳሰብም ትክክል አይደለም፡፡ ምክንያቱም ይህች ሀገር ሀብታም ሀገር ናት፡፡

ለምሳሌ፣ ሰፊ የሚታረስ መሬት አለ፡፡ እስከዛሬ አርሰናል ተብሎ የሚባለውም የዚህን ግማሽም አይደርስም። በጣም በርካታ ወጣት ሃይል እና ሰፊ ጉልበት አለ፡፡ ዘርፈ ብዙ ፋይዳ ያላቸው ወንዞችም ብዙ ናቸው፡፡ ኢትዮጵያ መልከዓ ምድሯ የሰጣት ተደማሪ ፀጋ አላት፡፡ አንዱ ጋ ድርቅ ሆነ ብለን ስናስብ፣ ሌላ ቦታ ላይ ልምላሜ፤ አንደኛው ቦታ ላይ የሆነ ነገር ተፈጠረ ብለን ስናስብ፣ ሌላ ቦታ ላይ ደግሞ የተሻለ ነገር አለ፡፡

ስለዚህ በመጀመሪያ፣ እነዚህን ፀጋዎች ይዘን ከተረጂነት መውጣት አስፈላጊ ነው ብለን መግባባት ይገባል፡፡ እናም ተረጂነትን ወደ ምርታማነት በመቀየር፣ ከምግብ ዋስትና እሳቤ ወጥተን፣ የምግብ ሉዓላዊነት ወደሚለው አስተሳሰብ መሄድ አለብን፡፡ ምክንያቱም፣ የምግብ ዋስትና የምንለው በአብዛኛው ሰዎች በየትም መጣ በየት የምግብ ፍላጎታቸው የሚያሟላውን ነገር ማቅረብ ማለት ነው፡፡ ይህ ከውጭም ሊመጣ ይችላል፤ ከውስጥም፣ ከሰፈርም ሊመጣ ይችላል፡፡

የምግብ ሉዓላዊነት ስንል ግን፣ የምንመገበውን ነገር ማምረት ማለት ነው፡፡ የምንመገበው ነገር እንዴት ነው የተመረተው? ማን ነው ያመረተው? የት ነው የተመረተው? የሚለውን ሃሳብ በሙሉ በመያዝ፤ በዘላቂነት የምግብም ይሁን ሌሎች ጉዳዮችን በራሳችን ባለቤትነት ራሳችንን ማዕከል አድርጎ ምርቱንም፣ ግብይቱንም፣ ገበያውንም ራሳችን ተቆጣጥረን መምራትን የሚጠይቅ ነው፡፡ ለዚህ ነው ከክቡር ጠቅላይ ሚኒስቴራችን ዐቢይ አሕመድ(ዶ/ር)፣ "አሁን ጉዟችን ወደ ምግብ ሉዓላዊነት ነው፤" የሚሉት፡፡ ይሄ ደግሞ ከምግብ ዋስትና የሰፋ አቅምም፣ የሰፋ ተልዕኮም ያለው ስለሆነ፣ በዚህ ላይ መግባባት አለብን፡፡

ሁለተኛው ነጥብ፣ ማጥራት የሚል ነው፡፡ ማጥራት ማለት ቅድም እንዳነሳነው፣ ሳይገባቸው እዚህ ውስጥ የሚገኙ፤ በተለያየ ምክንያት ይህንን ሰብዓዊ ድጋፍ ለመጠቀም ያሰፈሰፉ፤ ወይም ጥቅም ላይ ያሉ በተለያየ መንገድ ከዚህ ውስጥ መውጣት አለባቸው፡፡ እዚህ ጋ ልብ ሊባል የሚገባው በተለያየ ምክንያት ሰብዓዊ ድጋፍ የሚያስፈልገው ሰው በየትኛውም ጊዜ ይኖራል፡፡ ይሄ ዓለም አቀፍ ልምድም ነው፡ ፡ ይሄ ደግሞ በአካላዊ፣ በአካባቢያዊ፣ ተፈጥሯዊ አልያም በእድሜ ምክንያት ሊሆን ይችላል። ሰዎች ሊፈናቀሉ ወይም በቅጽበታዊ አደጋዎችም ሊጠቁ ይችላሉ፡፡



እንዲህ ሲሆን ሰዎች ድጋፍ ይፈልጋሉ፡፡ ይህ ግን ድጋፍ ነው እንጂ ርዳታ አይደለም፡፡ ርዳታ የሚባለው ሰው ሊደገፍ ሳይገባው ዝም ብለህ ስትሰጥ ነው፡፡ በመሆኑም ሳይገባቸው በዚያ ውስጥ የተቀላቀሉ አካላት በሙሉ ተለይተው ሊታወቁ፤ በአንጻሩ መደገፍ ሲገባቸው የቀሩ ካሉም ለይቶ የማወቅና የማጥራት ሥራ በማከናወን ችግሮችን ማስተካካል ይገባል፡፡

ሦስተኛው ጉዳይ፣ ራሳችንን ማዘጋጀት ነው፡፡ ምክንያቱም ሌላው ዓለም የድጋፍ እጁን እያጠፈ ሂዷል፡፡ ፍላጎቱም ትኩረቱም ወደሌላኛው እየሄደ፤ ምናልባትም ሰብዓዊነትን ከመደገፍ ይልቅ ጦርነትን ማፋፈም የሚመስል ዝንባሌዎችም አሉ፡፡ ስለዚህ ይሄን እውነት ተገንዝበን ራሳችንን በራሳችን ለመደገፍ ልንዘጋጅ ይገባል፡፡

ለዚህ ደግሞ፣ አንዱ እና ትልቁ ማህበረሰቡ በራሱ የሚያደርገው መደጋገፍ ነው፡፡ ለዚያም መዘጋጀት ይፈልጋል፡፡ ከዚህ ባሻገር ስትራቴጂክ ክምችት በየደረጃው መያዝና መኖር አለበት፤ ገንዘብም መያዝ ይፈለጋል፡፡ ለዚህ መሰሉ ሥራ እንደ ሀገር ወደ ሁለት ሚሊዮን ሜትሪክ ቶን ያስፈልገናል ብለን አስልተናል፡፡ ከዚያ ውስጥ ወደ 500 ሺህ መጠባበቂያ፤ ወደ አንድ ነጥብ አምስት ሚሊዮን የሚሆነው ደግሞ የእለት ደራሽ ይሆናል፡፡

ከዚያ ባለፈ፣ የግዥ ሥርዓቱን ለማከናወን የፈንድ ሥርዓት ስለሚያስፈልግ፣ ፈንድ መያዝ አለብን፡፡ ይሄ በፌዴራልም በክልሎችም ሊያዝ የሚችል፤ የሚያስፈልገን ስትራቴጂክም እንበለው የእለት ደራሽም ይሁን፣ ለቅጽበታዊ አደጋዎች የሥራ ማስኬጃ ለመሳሰሉት ለማስቀመጥ እና ለመግዛት ነው፡፡ ለዚህ የሚሆኑ መጋዝኖች፣ ማሽነሪዎችን እና ግብዓቶችን ማዘጋጀት ያስፈልጋል፡፡

የድጋፍ ሂደቱም፣ የሚደገፈውን ለይቶ የመደገፍ፣ ሲደገፍም የምግብ፣ የሥነ ምግብ፣ የመጠለያ፣ የቤትና የአልባሳትን በመሳሰሉ ድጋፍ ፈላጊው የቸገረውን ነገር በሙሉ በሚሸፍን መንገድ ተዘጋጅቶ የመሸፈን ነው፡፡ ሆኖም አሁን እኛ እየሄድን ባለንበት አግባብ የሚሸፈነውንም በትክክል አንሸፍንም፤ የማይገባውም እዚያ ውስጥ ገብቶ እየዳከረ የሌላኛውን ድርሻ ይሻማል፡፡

በመሆኑም በማጥራትና በመዘጋጀት ሂደት፣ በተለያዩ ምክንያቶች የሚታገዘውና የሚደገፈው ሕዝብ እየጨመረ እንዳይሄድ ይህንን በደንብ አድርጎ ማስተዳደር፤ በድጋፍ ውስጥ ያሉ ዜጎችንም ከሌሎች ፕሮግራሞች ጋር እያቀናጁ ራሱን እንዲችል ማድረግና ከድጋፍ ማስወጣት ይፈልጋል። ለምሳሌ፣ ከሴማት ቱርፋት ፕሮግራሞች፣ ከክህሎት መር ሥራ እድል ፈጣሪ ፕሮግራሞች፤ ከኩታ ገጠም የእርሻ ሥርዓቶች ጋር እና ሌሎችም ጋር ማገናኘት ይቻላል፡፡ ሰው የመሥራት አቅም እስካለው ድረስም ሊሳተፍ ከሚችልበት አማራጭ ጋር ማቀናጀት ይቻላል፡፡

በዚህ መልኩ ከሰብዓዊ ድጋፍ ፈላጊነት ራስን መቻል ደረጃ ሲደርስ የማሸጋገር ሥራ ሊሰራ ይችላል፡፡ ማሸጋገር ሲባል፣ ለምሳሌ፣ ሰዎች ተፈናቅለዋል ብንል፤ እነዚህን የተፈናቀሉ ሰዎች በዘላቂ የልማት ፕሮግራሞች አማካኝነት ወይ ወደነበረበት እና ወደተነሳበት አካባቢ ሂዶ ምርቱንም እርሻውንም ደግፎ ወደ ሥራ እንዲገባ የማድረግ፤ ወይም እዚያው ባለበት ማህበረሰብ ውስጥ ኑሮውን እንዲመራ የማድረግ፤ ወይም ወደ ሌላ ቦታ ወስዶ ሕይወት እንዲጀምር የማድረግ ሥራዎችን የመሳሰሉት ሊሰሩ ይችላሉ፡፡

ስለዚህ የማቀናጀት እና የማሸጋገር ሥራዎች የድጋፍ ፈላጊን መጠን በራሱ ጊዜ እየቀነ እንዲሄድ የሚያደርግ ሲሆን፤ ይሄ ምናልባትም እንደ ሀገር ከድጋፍ ፈላጊነት ወደ ድጋፍ ሰጭነት የመሻገር ነገር እየፈጠረ ይሄዳል፡፡ ስለዚህ ከተረጂነት ወጥተን ወደ ምርታማነት፤ ከተረጂነት ወጥተን ወደ ምግብ ሉዓላዊነት እንሻገር ስንል፤ እጃችን ላይ ያለውን በዚህ መንገድ እያጠራን እንሂድ የሚል ነው፡፡

**አዲስ ዘመን፡- በዚህ ዙሪያ ያለውን ስሜት ለመገንዘብም ሆነ ይሄንን እሳቤ ለመዋቅሩም፣ ለሕዝቡም ከማሳወቅ አኳያ ምን ሰርታችኋል?**

**አምባሳደር ዶክተር ሽፈራው፡-** በዚህ ሂደት ላይ በተለያዩ ከተሞች ወደ 32 ሺህ ከሚጠጉ አመራሮች ጋር ውይይት ተደርጓል፡፡ ይህ ከአመራሮች ጋር የተደረገ ውይይት በከፍተኛ አመራሮች የተመራ ሲሆን፤ ክልሎችም በየራሳቸው ጊዜ በየደረጃው ወደ አስር ነጥብ ስድስት ሚሊዮን የሚደርስ ሕዝብ አወያይተዋል፡፡ ይህ ድጋፍ ተፈላጊ ነበር ወይስ አልነበረም በሚልም በድጋፍ ውስጥ ካሉ ሰዎች ጋር ጭምር ውይይት ተደርጓል፡፡ ሕዝቡ በአንድ ድምጽ ያነሳው፣ በየትኛውም መዋቅር እና መድረክ ላይ እኛ ድጋፍ ፈላጊ ነን እርዱን ብሎ የጠየቀበት አግባብ አለመኖሩን ነው፡፡

ይልቁንም ሕዝቡ የተናገረው፣ ከመጀመሪያውም የእናንተ የአመራሮቹ አባዜ ነው፤ ይህንን እኛ ፈልገን አይደለም ያመጣነው፤ ያመጣችሁትንም እናንተው ናችሁ የምትወስዱት የሚል ነው፡፡ እኛ ከእናንተ የምንፈልገው ግብዓት እንድትሰጡን ነው፡፡ ለመደገፋችሁ ርግጠኛ ከሆናችሁ፣ በእንስሳትም ይሁን፣ በእህልም ይሁን፣ በአትክልትም ይሁን፣ እኛ የሚያስፈልገንን እንድትደግፉን ነው፡፡ እናም ምርጥ ዘሩን፣ ማዳበሪያውን ማቅረብ ከቻላችሁ እኛ ሥራችንን መሥራት እንችላለን፡፡ የሚደገፍ እንኳን ቢኖር በራሳችን የመደጋገፍ እና አንዱ ለአንዱ የመድረስ ባሕላችንን ተጠቅምን እንደርሳለን የሚል ነው፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ከሕዝቡ ሃሳብና አስተያየት ምን ተምራችሁ፤ ምንስ የተለየ ነገር ለመሥራት አቀዳችሁ?**

**አምባሳደር ዶክተር ሽፈራው፡-** የሕዝቡ ሃሳብና አስተያየት የፌዴራሉም የክልሎችም የቤት ሥራ ተደርጎ የተሰጠ የሕዝብ መልዕክት ነው፡፡ ይሄን ለማሳካት የሚያስችል ፖሊሲ ተቀርጿል፡፡ አሁን ላይ የሕግ ሥራዎች እየተጠናቀቁ ነው፡፡ ይህንን ዝግጅት በምናደርግበት ሂደትም ወደማምረት ትግበራ ተገብቷል፡፡ ቀደም ብዬ የገለጽኩት ሁለት ሚሊዬን ሜትሪክ ቶን እህል ለዚሁ ዓላማ የማምረት ውጥን ተይዞ ወደሥራ መገባቱም የዚሁ አንድ አካል ነው፡፡

ክልሎችም እንደ ሀገር ለዘርፉ የሚያስፈልገንን ለማምረት ከ253 ሺህ ሄክታር በላይ መሬት በማረስ፤ የሁለት ሚሊዮን ሜትሪክ ቶን እህል ፍላጎትን ለመሸፈን መንገዱን ጀምረዋል። ሥራውን ዘግየት ብለን የጀመርን ቢሆንም፣ በአሁኑ ጊዜም ወደ አንድ መቶ ሺህ ሄክታር ተለይቶ ወደ እርሻም ተገብቷል። በሚቀጥሉት ወቅቶችም የተባለውን 253 ሺህ ሄክታር የመሸፈን አቅሙ አለ፡፡ የሚቻልም ነገር ነው፡፡

በዚህ ዓይነት መንገድ ስንሄድ ግን መከታተል ያለብን ነገር አለ፡፡ አንደኛው ተጠያቂነትን መፍጠር ሲሆን፤ በየደረጃው ለተሰጠው ኃላፊነት፣ ለተሰጠው ሥልጣን፣ ለሚያስተዳድረው የአስተዳደር እርከን ኃላፊነት እና ተጠያቂነት መኖሩ ማረጋገጥ አለበት፡፡ ምክንያቱም ለምርጫ ሲሆን ምረጡን የምንል፤ ሰዎች ችግር ውስጥ ሲገቡ የለንበትም የምንል፤ የመጣውን ሰብዓዊ ድጋፍ ደግሞ ላልተገባ አላማ የምናውል መሆን የለብንም፡፡ ይህ ክብረ ነክ ነው፡፡ ከዜግነትም በታች ነው፡፡ ሀገርን፣ ዜግነትንና ዜጋንም ጭምር መሆን የሚገባውን ቦታ የሚያሳጣ ነው፡፡ ኢትዮጵያዊነትንና ኢትዮጵያን የማይመጥን ነው፡፡ በዚህ ደረጃ ሰው እንዲሰራ ተጠየቂነት በቦታው ላይ መሆን አለበት፡፡

ይሄ ግን ቀላል ነገር ነው ተብሎ የሚወሰድ አይደለም። ለ50 እና 60 ዓመታት በሰው ሥጋ፣ ደም እና አጥንት ውስጥ የገባ ጉዳይ ነው፡፡ መድረክ ላይ ለመናገር በጣም ቀላል ቢሆንም፣ መሬት ላይ ለመሥራት ግን ምናልባትም ወገብ የሚያጎብጥ፤ የሚገዳደርና መልሶ እዚያው ማጥ ውስጥ የሚከትም ነው፡፡ ስለዚህ በዚህ ላይ ሚዲያዎች ሊያግዙን፤ ኃላፊነት ከተጠያቂነት ጋር እንዲሰፍን የሚያስችሉ ዘገባዎችን ማከናወን አለባቸው፡፡ ለዚህም ችግሩን ለማቃለል ማን እንዴት ተንቀሳቀሰ፣ ምንስ አደረገ፣ ምንስ አቃተው የሚሉ ግንዛቤን ፈጣሪ እና አቅጣጫ አመላካች አጀንዳዎችን ተከታታይ በሆነ መልኩ ማስረጽ ይጠበቅባቸዋል፡፡

ስለዚህ ሥራው ማን ምን አደረገልኝ ከሚል ወጥቶ፣ ማን ምን አደረገ በሚል ቅኝት እንዲመራ፤ የተጠያቂነት ሥርዓቱም ከላይ እስከ ታች ተጠናክሮ የሚሄደበትን ሁኔታ መፍጠር ትልቁ ጉዳይ ይሆናል፡፡ በመሆኑም በዚህ መልኩ መሥራት፣ ያሉንን አቅምና ልምዶች መጠቀም ከተቻለ በርግጥም ከተረጂነት ወደ ምርታማነት፤ ከምግብ ዋስትና ወደ ምግብ ሉዓላዊነት መሻገር ይቻላል፡፡

**አዲስ ዘመን፡- በልማታዊ ሴፍቲኔት መርሃ ግብር አማካኝነት ከ25 ዓመታት በላይ ተረጂነት እንዲሰርጽ ከተደረገበት አካሄድ ምን የተለየ ሥራ በመሥራት ተረጂነት እሳቤን ሽሮ የምግብ ሉዓላዊነት አጀንዳ እውን ማድረግ ይቻላል?**

**አምባሳደር ዶክተር ሽፈራው፡-** ከሰብዓዊ ድጋፍ፣ ራስን ወደ መቻል የሚለውን ስናነሳ፤ ዋናው ቁም ነገር ማምረት ነው። ምርት የማምረት ሥራ ደግሞ በራሳቸው በድጋፍ ፈላጊዎች ሊሰራ ይችላል፡፡ በአካባቢው መዋቅርም ሊሰራ ይችላል፡፡ ለዚህ ደግሞ ካሉት የልማት እንቅስቃሴዎች ጋር አስተሳስረን መፈጸም አለብን፡፡ ሰዎች በየጓሯቸውም ይሁን በጋራ፤ በግልም ይሁን በኩታ ገጠም፤ በሌማት ቱርፋትም ይሁን በክህሎት መር የሥራ እድል ፈጠራዎች፣ በተለያዩ ዘርፎች ላይ ሊሳተፉ ይችላሉ፡፡ ስለዚህ ሰዎች በዚህ ማዕቀፍ ስር እንዲቀናጁ በማድረግ ወደሌላኛው ከፍታ እንዲሸጋገሩ የማድረግ ሥራ በትኩረት መሰራት አለበት፡፡

በዚህ አግባብ ስንሰራና ዜጎችን ስናሸጋገር ምርታማነትን ስለምናሳድግ፣ የሚቀረው ሰብዓዊ ድጋፍ ፈላጊ ቁጥር በራሳችን አቅም የምንሸፍነው ይሆናል፡፡ ይህ ሲሆን የማንንም ርዳታ እና ድጋፍ አንፈልግም፡፡ አንፈልግም ብንል፣ የዓለም አቀፉ ድጋፍ እያሽቆለቆለ ሂዷል፡፡ ለምሳሌ፣ በረጂዎች ባለፉት ዓመታት ምናልባት 90 እና 80 በመቶ የሰብዓዊ ድጋፍ ፍላጎት ይሸፈን ነበር፡፡ ባለፈው ዓመት ወደ 33 በመቶ ወርዷል፤ አሁን ባለንበት ዓመት እስካሁን ከ18 በመቶ በታች ነው፡፡

ከፍላጎት አኳያ ብናይ፣ ባለፈው ዓመት አራት ቢሊዮን ዶላር ነበር የጠየቅነው፡፡ ያገኘነው ግን ወደ አንድ ነጥብ ሶስት ቢሊዮን ዶላር ነው፡፡ እናም የዓለም አቀፍ ድጋፉ እያሽቆለቆለ የሚሄድበት ፍጥነት በራሱ እጅግ በጣም የሚያስደነግጥ ነው፡፡ ስለዚህ ጥያቄው ሊኖር ከሚችለው ነገር አንጻር እስኪ ራሳችንን እንቻል የሚል ነው፡፡ ምክንያቱም ካናዳ ላይ ስንዴ እየዘነበ ወይም ሌላ ቦታ አንድ ነገር እየተፈጠረ እዚህ ያለውን ይታደግልኛል የሚባል ነገር የለም፡፡ አሁን የሚሆነው ነገር ሀገራት ኢትዮጵያን ጨምሮ ራስን መቻል እና ችግሩን መፍታት ነው፡፡ በተረጂነት እቀጥላለሁ ቢባልም እድሉ የለም፡፡

በጥቅሉ፣ ሰብዓዊ ድጋፍ ፍላጎትን በትክክለኛው እናስተዳድረው፣ የምግብ ሉዓላዊነትንም እናረጋግጥ ሲባል፤ ሰብዓዊ ድጋፍ ፈላጊውን ገፍተን እናስወጣው ማለት አይደለም፡፡ እንደዚህ የሚል ሃሳብም የለንም፡፡ ሰብዓዊ ድጋፍ ፍላጎቱም፤ ፈላጊውም ይኖራል፡፡ ነገር ግን ፈላጊውን ትክክለኛ እናድርገው፤ ፈላጊውን እናቀናጅና ከዛ እናስወጣው፤ እናሸጋግረውና የሰብዓዊ ድጋፍ ፈላጊን ቁጥር እንቀንስ፤ በዚህ ውስጥ የተረጂነት አስተሳሰብ ሂደቱን እንዳይጫነው፣ የተረጂነት አስተሳሰብ እንዳያሰናክለው እንከላከል የሚል ነው፡ ፡ ይሄንን በተጠያቂነት መርህ፣ በምርታማነት መርህ እንሻገረው የሚል ነው፡፡

ከዛ ተርፎ የሚመጣ ካለ በራሳችን አቅም ምላሽ ለመስጠት ዝግጅት እናድርግ ነው፡፡ ይሄን የምናደርገው ደግሞ ቀደም ሲል ባነሳኋቸው አግባብ ነው፡፡ የማህበረሰቡ የእርስ በእርስ መተጋገዝ ባሕል ተጠቅመን፤ የስትራቴጂክ ክምችትን አሳድገን፤

ወደ ገጽ 8 ዞሯል

# «ለርዳታ እጁን ዘርግቶ ርዳታ...

ከ7ኛ ገፅ የዞረ

የእለት ደራሹን ይዘን፤ ፈንድ አደራጅተንና ዝግጁ ሆነን ስንጠብቅ ነው፡፡ ይሄን ስናደርግ የሆነ ነገር ሲመጣ አንዋከብም፤ አንበረግግምም፡፡ ምክንያቱም ተዘጋጅትን ነው ያለነው፤ ምን እንደሚመጣም እናውቃለን፡፡ በመሆኑም አቅጣጫው በዛ መንገድ እንሥራ የሚል ነው፡፡

በዚህ ዓይነት መንገድ ስንሰራ ትልሙን እውን ማድረግ እንችላለን፡፡ ምክንያቱም እንደ መንግሥትም የመቻል ታሪክ አለን፡፡ እንደ ሀገርም እኛ በጣም ታላቅ ሀገር ነን፡፡ በዓድዋ ላይ በጦርነት ማጥ ውስጥ ገብተን አሸንፈን የወጣን ሕዝቦች ነን፡፡ ባልተቆራረጠው ሥርዓተ መንግሥታችንም ብዙ የሉዓላዊነት ተንኳሾችን አሳፍረን እና አንገት አስደፍተን መመለስም የቻልን ሀገርና ሕዝብ ነን፡፡ ዛሬም እንደ ዓባይ ግድብ ያሉ ትላልቅ ፕሮጀክቶችን በራሳችን አቅም ሰርተን እየተወጣን ነን፡፡

ታዲያ የተረጂነት እሳቤ ለምን እንደዚህ እጅና እግራችንን ጠላልፎ ሊይዘን ቻለ፣ የሚለውን መመርመርና ሚስጢሩን መፍታት ሲቻል፤ ትክክለኛ መልሱን ማግኘትም፤ ከችግሩ ልቆ መውጣትም ይቻላል፡፡ አሁን ያለው የተረጂነት እሳቤና መንገድ ኢትዮጵያንም፣ ኢትዮጵያውያንንም፣ ኢትዮጵያዊነትንም ስለማይመጥን ከዚህ መውጣት አለብን፡፡

ምክንያቱም፣ ለርዳታ እጁን ዘርግቶ ርዳታ የሚወስድ አካል፣ ሞራል ኖሮት ከሌላው ጋር እኩል መቆምና መገዳደር አይችልም፡፡ ይሄ ደግሞ የኢትዮጵያዊነት ሰብዕና ሊሆን የማይገባው፤ ገጽታችንንም የሚያበላሽ፤ ማንነታችንን የሚያኮላሽ ክብረ ነክ ጉዳይ ስለሆነ፤ ከዚህ እሳቤና ችግር በቻልነው ፍጥነት መውጣት አለብን፡፡

በሂደቱም አንደኛው ዜጋ የበለጠ ጉዳዩ ተቆርቋሪ፣ ሌላኛው ደግሞ ከፊል ተቆርቋሪ ሊሆን አይችልም፡፡ ጉዳዩ ሁሉንም የሚመለከት፤ የሁሉም ድርሻ፣ የሁሉንም ተሳትፎና ኃላፊነት የሚሻ ነው፡፡ በዚህ አግባብ ባለን አቅምና ጉልበት ሁሉ በስፋት ከተረባረብን ደግሞ ፈጣሪም ስለሚያግዘን የማናሳካበት ምክንያት ስለማይኖር፤ ሁላችንም በእኩል ቁጭትና ወኔ በርትተን ልንሰራ ይገባል፡፡

**አዲስ ዘመን፡- በራስ አቅም ምላሽ ከመስጠት ጋር በተያያዘ ለቅጽበታዊ አደጋዎች ምላሽ ከመስጠትም ሆነ፤ የአጋር አካላትን ድጋፍ ተቀብሎ የዘላቂ ልማት አቅም ከማድረግ አኳያ ያለው አካሄድ ምንድን ነው?**

**አምባሳደር ዶክተር ሽፈራው፡-** ከቅጽበታዊ አደጋዎች ጋር በማያያዝ ትልቁ ጉዳይ ቅድመ ዝግጅት እና ቅድመ ማስጠንቀቂያ ነው፡፡ ለምሳሌ፣ አሁን ባለንበት ወቅት ላይ ዝናብ እንደሚበረታ የታወቀው ከስድስት እና ሰባት ወር በፊት ነው፡፡ ዛሬ ስለዘነበ አዲስ ክስተት ነው ማለት አይቻልም፡፡ ለዛ የሚሆን ዝግጅት ቀድሞ ማድረግ፤ ተጋላጭ የሆኑ አካባቢዎች ላይ ያሉ ነገሮች ላይ በትኩረት መሥራት ይገባል፡፡ ሕዝባችንም የመከላከሉም፣ የምላሹም አካል እንዲሆን ማዘጋጀት ያስፈልጋል፡፡ ከዛ ባሻገር አቅም በቻለና በፈቀደ መጠን ሌሎች የሚያግዙ ካሉ፣ ለእነሱም በራችን ዝግ አይደለም፡፡

በራስ አቅም ምላሽ መስጠትን ስናስብም፣ የሆነ ሰው አንድ ነገር ይዞ ቢመጣ፣ አይ ይዘህ ሂድ እያልን አይደለም፡፡ ይልቁንም ሰብዓዊ ድጋፍን በሚመለከት ሰዎች አቅም እንዲኖራቸው በሚያስችል መልኩ መጠቀም የሚገባ መሆኑን መገንዘብ ይገባል፡፡ ይሄ ዓሣን ከምታበላው ዓሣን እንዴት እንደሚይዝ አስተምረው እንደሚባለው ዓይነት ነው፡፡ ሰውን በየቀኑ እመግብሃለሁ ከማለት፤ ምግቡን ራሱ እንዴት እንደሚያመርት በማሳወቅና በማገዝ ላይ የተመሰረተ መደጋገፍ ነው የሚፈለገው። በዚህ ረገድ አቅም አለኝ የሚል ማንኛውም አካል ካለ አሁንም ሊደግፍ የሚችልበት ሰፊ እድል ስላለ ሊሳተፍ ይችላል፡፡

ሰብዓዊ ድጋፉም ላይ አለን የሚሉ ካሉ ይዛችሁ እንዳትመጡ አላልንም፡፡ እያልን ያለነው፣ ዓለም አቀፉ ድጋፍ እየነጠፈ ሄዷል፡፡ እናም በየደረጃው ያለው የመንግሥት አካል ሌላ የማንንም ይሁንታም ይሁን ርዳታና ድጋፍ ሳይጠይቅ፣ ድጋፍን በራሱ ለማድረስ ዝግጁ መሆን አለበት የሚል ነው፡፡ ሆኖም በአቅሙ ሰርቶ ሲያበቃ የሚያቅተው ነገር ካለ የሚቀጥለውን አካል በይፋ ይጠይቃል፡፡ የጠየቀው ነገር ትክክለኛ መሆኑ እየተለየም ድጋፎች ይቀጥላሉ፡፡ ምክንያቱም ዜጋን በተመለከተ የመጀመሪያው ተጠያቂ ራሱ መንግሥት (በየደረጃው ያለው የመንግሥት አካል) ነው፡፡

**አዲስ ዘመን፡- የኮሚሽኑ የሥራ ተሞክሮ የአደጋ ጊዜ ምላሽ ላይ ያተኮረ ነው፡፡ ይሄ ደግሞ እንደ ሀገርም ሆነ እንደ ሕዝብ ከፍ ላለ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ ብሎም ሰብዓዊ ጉዳት የሚዳርግ፤ የኮሚሽኑም የቀጣይ ጉዞ ፈተና መሆኑን ተገንዝቦ ከመፍታት አኳያ ምን ታስቧል?**

**አምባሳደር ዶክተር ሽፈራው፡-** ይሄ ትክክለኛ ችግርም፤ ፈተናም ነው፡፡ ችግርና ፈተናነቱ ከአጋር አካላት ጋር ብቻ ሳይሆን፤ እንደ መንግሥት መዋቅርም ፈተና ነው፡፡ እንደ መንግሥት መዋቅር የቅድመ አደጋ ብለን ስናነሳ እና ወደ ተቋማት ስናመጣው የአደጋ ስጋት የሆኑ ጉዳዮችን በመለየት በእቅዶቻቸው ውስጥ አስገብተው እና በጀት መድበው፣ እንዲሁም የሰው ኃይል አሰማርተው መተግበርን የሚመለከት ነው፡፡

ለምሳሌ፣ ይሄንን ከግብርና አንጻር ብንመለከተው፤ ድርቅ ሊመጣ ሲሆን ሁሌም ቅድመ ትንበያ አለ፡፡ በዚህ አካባቢ ድርቅ

> **ለርዳታ እጁን ዘርግቶ ርዳታ የሚወስድ አካል፣ ሞራል ኖሮት ከሌላው ጋር እኩል መቆምና መገዳደር አይችልም፡፡ ይሄ ደግሞ የኢትዮጵያዊነት ሰብዕና ሊሆን የማይገባው፤ ገጽታችንንም የሚያበላሽ፤ ማንነታችንን የሚያኮላሽ ክብረ ነክ ጉዳይ ስለሆነ፤ ከዚህ እሳቤና ችግር በቻልነው ፍጥነት መውጣት አለብን**

ሊከሰት ነው ሲባል የእንስሳት መኖ ያዘጋጃል፤ የእንስሳትን ቁጥር ይመጥናል፤ በአካባቢው ላይ ሊዘራ የሚገባውን ድርቅን ሊቋቋምና ቶሎ ሊደርስ የሚችል ነገር ካለ በእሱ ላይ ይሰራል። እነዚህን ከሰራ ድርቁ እንኳን ቢከሰት ማስታገሻ ተፈጥሯል ማለት ነው፡፡ ምናልባት በጣም የማይቻል ሁኔታ እንኳን ቢኖር ሰውንም፣ አካባቢውንም፣ እንስሳውንም ወደሚመች አካባቢ የማስጠጋት ነገርን ሁሉ ሊያካትት ይችላል፡፡ ይሄ ማለት የተለያዩ የአዳብቴሽን እና ሚቲጌሽን ወይም ችግሩን የማላመድና ችግሩን የመጋፈጥ ነገሮችን እየፈጠሩ መሄድ ማለት ነው፡፡

በውሃ ዘርፉም በተመሳሳይ ነው፤ ውሃ ሊጠፋ ነው፣ ላይኖር ይችላል ከተባለ፤ መውጫ መንገዶቹንና የመፍትሔ አማራጮቹን በመፈተሽ ይዘጋጃል፡፡ በጤናውም ዘፍር ቢሆን እንደዚሁ የሆነ ችግር ሊፈጠር ነው ከተባለ፤ ስለሚፈጠረው ነገር ቀድሞ መረዳት እና የመፍትሔ መንገድ ማበጀት ይኖርበታል፡፡ ለምሳሌ፣ የተለያዩ ወረርሽኖች ሊከሰቱ ከሆነ፤ የጤና ተቋማት ችግር ሊያጋጥማቸው ከሆነ፤ የመድኃኒት ክምችት የሚያስፈልግ ከሆነ፤ የቅድመ ክትባት ሥራ የሚያስፈልግ ከሆነ፤... ጉዳዮቹን ቀድሞ ተረድቶ እንደ የጉዳዩ ምላሽ መስጠት የሚያስችል አቅም መፍጠርን የሚመለከት ነው፡፡

የአደጋ ስጋት ሥራ አመራር ኮሚሽንም፣ እዚህ አካባቢ የሆነ ነገር ሊፈጠር ነው የሚለውን ሲገነዘብ፤ እንደሚከሰቱት አደጋዎች ባህሪ ቀድሜ የምግብ ክምችት መያዝ አለብኝ፤ ምግብ ነክ ያልሆነ ክምችት መያዝ አለብኝ፤ የያዝኩትንስ የት ነው የማዘጋጀው፤ የሚሉ ሥራዎችን መሥራት ማለት ነው፡፡ አንዱ ፈተናም የሚጀምረው እዚህ ጋ ነው፡፡ ምክንያቱም ለዚህ ሥራ በጀት በትክክል ተመድቦ አይሰራም፡፡ ይሄ የመዋቅራችንም ችግር ነው፡፡

ይሄ በመደበኛነት የእቅድ አካል ቢሆንም፤ ችግሮች በሚፈጠሩባቸው አካባቢዎች ላይ ቀበሌው፣ ወረዳው፣ ዞኑ እና ክልሉ የአደጋ ስጋት ፕሮፋይል (ምን ዓይነት አደጋ አለ፣ ይሄ አደጋ ማንን ተጋላጭ ያደርጋል፣ ይሄንንስ መቋቋም ይቻላል ወይ የሚሉ ጉዳዮች) ሊኖረው ይገባል፡፡ ምክንያቱም የአደጋ ስጋት የከፋ ውጤት የሚባለው የአደጋው መኖር አለመኖር ብቻ ሳይሆን፣ አደጋውን የመቋቋም አቅሙንም ጭምር ስለሚመለከት ነው፡፡ የእነዚህ ሁለቱ ሚዛን ነው የከፋ ጉዳት የማስከተል እና አለማስከተል ውጤት የሚታየው፡፡ ሂሳቡም ይሄ ነው፡፡

ስለዚህ የቅድመ አደጋ ሥራ ላይ ሀብት መድቦ ቀድሞ በመሄድ መሥራት ላይ ያለውን ክፍተት መሻገር በጣም ወሳኝ ነው፡፡ አሁን ላይ የአደጋ ስጋት ምላሽ ፈንድ ብለን እየሰራን ያለነው አንዱ ሥራ ይሄንን ክፍተት እንዲሸፍን ነው፡፡ ይሄ በሚያስፈልግበት ጊዜ በተቻለ መጠን የመንግሥት መዋቅሩ መጀመሪያ በሴክተሮች የሚሰራው ሥራ ይኖራል፤ ከዛም ለአደጋ ስጋት ምላሽ ተብሎ ለኮሚሽኑ የሚመደብ አለ፡፡ በእነዚህ ሁለቱ ያልተሸፈነና የተንጠባጠበ ነገር ሲኖር ደግሞ በአደጋ ስጋት ምላሽ ፈንድ ይመለሳል የሚል ስሌት ይዘን ነው እየሰራን ያለነው፡፡ ይሄው ሥራ በመንግሥት በኩልም ይሁንታ ተገኝቶበት እየተከናወነ ያለ ነው፡፡

ከዚህ ጋር ተያይዞ የሚነሳው የአደጋ ጊዜ ምላሽ ነው፡፡ በአደጋ ወቅት ባለው ምላሽ ላይ ብዙ ጊዜ ሲታይ ይብዛም ይነስ ሀብት ይመደባል፡፡ ለምሳሌ፣ በዚህ ዓመት (በ2016) ከ40 ቢሊዩን ብር በላይ በመመደብ መንግሥት በክልልም፣ በፌዴራልም ያወጣው ወጪ አለ፡፡ በዚህ መልኩ የአደጋ ጊዜ ምላሽ ላይ ያሳረፍነው ሀብት በየደረጃው በቅድመ አደጋ ላይ አውለነውና ተሰርቶበት ቢሆን ኖሮ ብዙ ነገር መታደግ ይቻል ነበር፡፡ ምክንያቱም የቅድመ አደጋ ሥራ ከአደጋ ጊዜ ሥራ በብዙ እጥፍ ያነሰ ወጪ የሚጠይቅ ነው፡፡

ይሄንን በገንዘብ ስሌት ለማየት ብንሞክር፤ ለአደጋ ጊዜ ምላሽ ወይም ለቀውስ አስተዳደር የምናወጣው ሃያ ዶላር ቢሆን፤ በቅድመ አደጋ ላይ ሰርተን ቢሆን ኖሮ በአንድ ዶላር ሊሰራ ይችል ነበር፡፡ እናም አንድ ዶላር ኢንቨስት ማድረግ ተቸግረን፣ ሃያ ዶላር ነው ወጪ እያወጣን ያለነው፡፡ ስለዚህ የቅድመ አደጋ ሥራ እጅግ ተፈላጊም፤ የሚደገፍም፤ ከወጪም አኳያ ተመራጭ ነው፡፡ ሆኖም የአደጋ ስጋት ሥራ አመራራችን ውድ በሆነው መንገድ እየተጓዘ የቆየ ነው፡፡

ሦስተኛው ጉዳይ፣ የድህረ አደጋ ምላሽ ነው፡፡ ምክንያቱም፣ በቅድመ አደጋ የሚሰራው ሥራ አደጋ እንዳይከሰት ሲሆን፤ በድህረ አደጋ የሚሰራው ደግሞ በተሻለ ሁኔታ ለማቋቋም እና ሰው ተመልሶ ወደ አደጋው እንዳይመጣ ለመከላከል ነው። ሆኖም እንደ ቅድመ አደጋ መከላከሉ ሁሉ፣ በድህረ አደጋ ምላሽ ላይም ሀብት አይመደብም፡፡ አጋር አካላትም ቢሆኑ ሀብት አይመድቡም፡፡ ሁሉም የሚያተኩረው ቀውሷ ላይ ነው፡፡ ምክንያቱም ቀውሱ ፊት ለፊት የሚታይ እና የሚንቀሳቀስ ነገር ስላለው፣ ሁሉም እሷው ላይ ለመረባረብ ይሞክራል፡፡ ከዛ በኋላ ግን ማንም ሰው የለም፡፡

ነገር ግን በድህረ አደጋ ላይም የሚሰራው ሥራ በተሟላ መልኩ ተሰርቶ ቢሆን ኖሮ፤ ወይም ሰብዓዊነትን፣ ሰላም ግንባታን እና ልማትን ባማከለ መልኩ አቀናጅቶ መሥራት ቢቻል ኖሮ፤ አሉ የምንላቸውን ችግሮች በሙሉ መድረስ ይቻል ነበር፡፡

በመሆኑም እነዚህን ሦስት ጉዳዮች ወይም የቅድመ አደጋ፣ የአደጋ ወቅት እና የድህረ አደጋ ሥራን ሚዛን አስጠብቆ መጓዝ ፈተና ነው፡፡ ይሄ እንደ አጋር አካላትም ሲታይ ፈተና ነው፤ በራሳችን ከታች ጀምሮ ባለው የመንግሥት መዋቅርም ፈተና ነው፡፡ ስለዚህ መግባባት አለብን ከምንላቸው ጉዳዮች አንዱ ይሄ ነው፡፡ በዚህ ላይ ተግባብተን እና ሀብትን በሚዛናዊነት መድበን፤ አንደኛው ላይ የምንመድበው በሌላኛው ላይ ያለውን ወጪ የሚቆጥብ/የሚቀንስ ነው የሚለውን ይዘን መሥራት ብንችል ጠቃሚ ነው፡፡ ነገር ግን ይሄ ሳይሆን ቀርቶ፣ በከፋ መንገድም ቢሆን ሚዛን ጠብቆ የመሥራትን አስፈላጊነት እየተማርን ነው፡፡

**አዲስ ዘመን፡- በከፋ መልኩም ቢሆን የተገኘውን ትምህርት ይዞ በቀጣይ የተሻለ ሥራን ከማከናወን አንጻር የኮሚሽኑ አቋም እና መልዕክት ምንድን ነው?**

**አምባሳደር ዶክተር ሽፈራው፡-** በከፋ መንገድ መማር ማለት፤ ቅድመ አደጋ ላይ በደንብ ባለመሥራታችን፤ በድህረ አደጋም በትክክል ባለመሥራታችን ምክንያት፤ በአደጋ ወቅት ሥራ ላይ ብቻ አተኩረን እዛው እየሰመጥን ምን እያስከተለ እንደሆነ በተግባር መመልከትና ትምህርት መውሰድ ማለት ነው፡፡ በዚህ መልኩ ባይሆንና ይሄንን ማድረግ እንደሚገባን በመልካም መንገድ ብንማረው ጥሩ ነበር፡፡ ግን ሆነ፡፡ በመሆኑም በችግርም ቢሆን የተገኘውን ትምህርት በመውሰድ ነገን የተሻለ ነገር ለመፈጸም ነው እየሄድን ያለነው፡፡

ሆኖም አሁንም፣ በዚህ ረገድ በኮሚሽናችን በኩል የአደጋ ስጋት ሥራ አመራር ፖሊሲ በዚህ ጥልቀት እንዲያዝ መረዳት እንዲኖር፤ ይሄን መረዳትም ወደ ተግባር እንዲቀየር በማድረግ ሰፊ ሥራ ይጠይቀናል፡፡ ሚዲያዎቻችንንም በዚህ ረገድ በስፋት ማሰማራት ይፈልጋል፡፡ ምክንያቱም፣ ስለ ጉዳዩ አንድ ቀን ተናግሮ ሰው ተገንዝቧል ለማለት አይቻልም፡፡

የምንፈልገው ውጤት እስከሚገኝ ድረስ ደጋግሞ መናገር፤ ደጋግሞ መወያየት፤ ደጋግሞ መፍትሔ መፈለግ፤ መፍትሔውም እንደየአካባቢው እና እንደየነባራዊ ሁኔታው እንዲተገበር ማድረግ ይገባል፡፡ ለዚህም የተለያዩ ፈጠራዎችን፣ በማከል ጭምር መሥራትን የሚፈልግ ነው፡፡ እናም ከተባበርን እናሳካዋለን፤ የምግብ ሉዓላዊነትን ማሳካትም ከእኛ ሩቅ አይደለም፡፡

ለምሳሌ፣ የአደጋ ስጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን ቀደም ሲል በቢሊዩኖች በሚቆጠር ገንዘብ ነው ስንዴ ከውጭ ይገዛ የነበረው፡፡ አሁን እኔ እስከማውቀው ድረስ ባለፉት ሁለት ዓመታት ከእኛ ዶላር አውጥተን ስንዴ አስገብተን አናውቅም። የምንገዛውንም ከራሳችን ከሀገራችን ገበያ ነው፡፡ ከዛም አልፈን ባለፉት ሁለት ዓመታት በመጣንበት ሂደት የተረጂ ቁጥር እየቀነሰ ሄዷል፡፡

ለአብነት፣ ከዛሬ ሁለትና ሦስት ዓመታት በፊት ወደ ሃያ ነጥብ አንድ ሚሊዩን ነበረ፡፡ ይሄ አሃዝ የእለት ደራሽ ድጋፍ ፈላጊ ብቻ ነው፡፡ በመካከል ወደ 15 ነጥብ አራት ሚሊዩን ደርሶ ነበር፡፡ በዚህ ዓመት ወደ አስር ነጥብ አራት ሚሊዩን ነው የነበረው፡፡ በዚህ ሲዝን ላይ ደግሞ ወደ ስድስት ነጥብ ስምንት ሚሊዩን ነው እያስተናገድን ያለው፡፡ ስለዚህ የተረጂነት አስተሳሰብ እየቀነሰ ሄዷል፡፡ በዚህ ሂደት ግን የአየር ንብረት ለውጡ መልካም ነበር፡፡ ይሄ መልካም የአየር ንብረት ባለፈው በልግም፣ እያለፈ ባለው ክረምትም የታየ ነው፡፡

አሁን ላይ እየተሻሻለ የሄደው የተረጂነት አስተሳሰብም በመልካም ጅማሮነት የሚያዝ ነው፡፡ ምክንያቱም፣ አመራሮቻችን ተረጂነት ክፉ ልምምድ ነው በሚለው አጀንዳ ላይ እየተነጋገሩበት ነው፡፡ ከክቡር ጠቅላይ ሚኒስትራችን ጀምሮ በየደረጃው፣ በሀገር ውስጥም ይሁን ከሀገር ውጭ አምርቶ ራሱን የማይመግብ ማህበረሰብ ነፃነቱ የተሟላ አይደለም፤ ልመና ኢትዮጵያን እና ኢትዮጵያዊነትን የሚመጥን አይደለም የሚል ጠንካራ አቋም አለ፡፡

ይሄ ደግሞ የመንግሥት አቋም እንጂ፣ የሆነ ኮሚሽነር ተነስቶ የሚያቀርበው ንግግር ወይም የዜና ፍጆታ ጉዳይ አይደለም፡፡ መንግሥት እንደ መንግሥትም፣ እንደ ፓርቲም ጭምር አቋም የወሰደበት ነው፡፡ ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትራችን፣ ከተረጂነት የመላቀቅ እድል የሉዓላዊነት እና የማንነት ልኬት ማሳያ እንደመሆኑ፤ ለተፈጻሚነቱ ሁሉም የድርሻውን ሊወጣ እንደሚገባ የብልጽግና ፓርቲ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ላይ ያሳሰቡበትን ሁነት መጥቀስ ይቻላል፡፡ በመንግሥት መድረኮችም ይሄው አቋም ነው ያለው፡፡

ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሩ በሚመሩት እና በየደረጃው በነበረን የኢትዮጵያ የአደጋ ስጋት ሥራ አመራር ምክር ቤት መድረክም፣ ይሄው ጉዳይ እንደ አቋም ተወስዷል፡፡ በዚህ ረገድ የፌዴራልም ሆነ የክልል ሥራም ተለይቶ ተቀምጧል፡፡ በየጊዜው በምናደርገው ክትትልም የብልጽግና ፓርቲ የበላይ አመራሮችና ምክትል ፕሬዚዳንቶች በቅርበት ክትትል የሚደረግበት ርዕስ ነው፡፡

እናም አጀንዳው በመንግሥት ተይዟል፤ በገዢው ፓርቲ ተይዟል፤ ሕዝቡም በአስተሳሰብ ደረጃ ከዚህ የተለየ ሃሳብ የለውም፡፡ ስለዚህ መሃል ላይ ሊያጋጥም የሚችል ችግር ካለ ወይ ስንፍና ነው፤ ወይም ብልሸት ነው፡፡ ስንፍናን እና ብልሽትን ደግሞ በመዋቅራችን ውስጥ በመታገል በትኩረት ይሰራል፡፡ በዚህ ረገድ ተጠያቂነትም እንደሚኖር የተረጋገጠ ነው፡፡

በአጋር አካላትና በመሳሰሉት በኩልም ውዥንብር ሊኖር ይችላል፡፡ ውዥንብሩ እኛ አልተፈለግንም የመሳሰለ ነገር ከሆነ፤ እኛ ማንም አንፈልግም አላልንም፡፡ እያልን ያለነው እኛን በሚያሳክከን ቦታ ላይ አግዙን ነው፡፡ ይሄ ደግሞ ከተረጂነት ለመውጣት ሰው የራሱን አቅም አውጥቶ እንዲጠቀም እንዴት እናግዝ፤ እንዴት እንደግፈው የሚል እሳቤን ከመያዝ አኳያ የሚገለጽ ነው፡፡

በመሆኑም በዚህ መልኩ የሚመጣን ነገር በሰብዓዊነት ቋት ውስጥ እንከትታለን፡፡ ምክንያቱም በድጋፍ ስም እጃችንን አስገብተን እንበጠብጣለን የሚል እስከ ሌለ ድረስ ድጋፉ መልካም ነው፡፡ ችግር የሚሆነው ትንሽ ነገር ከትተናልና፣ እኛ ነን የምንወስንላችሁ ሲባል ነው፡፡ ይሄ ከተባለ ዞሮ ዞሮ ሁነቱ ክብረ ነክ ነው፤ ክብረ ነክነቱም ለሀገርም ለዜጋውም ነው፤ ነፃነትንም፣ ሉዓላዊነትንም የሚጎዳ ነው፤ ያልነው ነገር ነው ተመልሶ የሚመጣው፡፡ ይሄ ደግሞ መፈቀድ የሌለበት ነገር ነው፤ አንፈቅድምም፡፡

ነገር ግን ልንደጋገፍ ነው የሚል አካል ከመጣ፤ አይ የእናንተን ድጋፍ አንፈልግም አንልም፡፡ እንደዛም እያልን አይደለም፤ አልተባለምም፡፡ እያልን ያለነው የራስን ሰብዓዊ ፍላጎት በራስ አቅም ማሟላት ይቻላል፡፡ ይሄ ደግሞ የምግብ ሉዓላዊነት ጥያቄ እንደመሆኑ ኢትዮጵያ ማድረግ ትችላለች፡፡ ለዚህ የሚያስፈልገው ሁለት ሚሊዩን ሜትሪክ ቶን ያክል እህል መሰብሰብ ይቻላል፡፡ ምክንያቱም ዓመቱን ሙሉ የሚታረሰውን ወቅትና የመስኖ ተግባራትን ሳይጨምር፣ ከዚህኛዋ ክረምት ብቻ የሚሰበሰበው ከአምስት ሚሊዩን ሜትሪክ ቶን በላይ ነው።

ስለዚህ እያነሳን ያለነው የሚቻለውን ነገር ስለሆነ ሁሉም ሰው ከተረባረበ፣ የአደጋ ስጋት ሥራ አመራር ክንውንን ሚዛኑን ጠብቀን ከተጓዝን፣ እና የተረጂነት እሳቤን ጨከን ብለን ከውስጣችን ብናወጣው፤ እኛ ኢትዮጵያውያን ከዚህ በፊት በዓድዋ ላይ ለአፍሪካውያን ነፃነት ፋና ወጊ እንደሆንን ሁሉ፤ አሁንም በምግብ ሉዓላዊነት ፋና ወጊ መሆን እንችላለን፡፡ ለዚህ ደግሞ አፍሪካ ዓለምን ይመግባል ብቻ ሳይሆን፤ አፍሪካ ዓለምን የሚያጥለቀልቅ ሀብት አላት፡፡

ነገር ግን አፍሪካ በዚህ ዓይነት ሁኔታ ንቅት ብሎ፤ ራስን በራስ መርቶ፤ የራስን ደረጃ አውቆ መንቀሳቀስ ላይ ድክመቶች አሉ፡፡ በመሆኑም መልዕክቴ፣ ቀድሞ የፖለቲካ ቅኝ ግዛት ስንል የነበረውን ሥርዓት በድል እና ነፃነት እንደተካነው ሁሉ፤ አሁንም በኢኮኖሚ ቅኝ ግዛት ውስጥ ከመሆን ወጥተን ራሳችንን እንችላለን፤ ትልቅ ቦታም እንደርሳለን፡፡ በዚህም ሕዝባችንንም፣ ራሳችንንም ነፃ እናወጣለን፤ የሚል ነው፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ለቃለ ምልልሱ ፈቃደኛ ሆነው፣ ለሰጡን ሃሳብና ማብራሪያ አመሰግናለሁ!**

**አምባሳደር ዶክተር ሽፈራው፡-** እኔም ሃሳቤን እንድገልጽ ስለጋበዛችሁኝ አመሰግናለሁ!

# በንግድ ሳምንቱ የተከናወነው ኤግዚቢሽንና ባዛር

**ፍሬሕይወት አወቀ**




የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር ባሳለፍነው ሳምንት "የኢትዮጵያን ይግዙ" በሚል መሪ ሃሳብ ልዩ የንግድ ሳምንት ኤግዚቢሽንና ባዛር ማዘጋጀቱ ይታወሳል።በንግድ ሳምንቱም የተለያዩ ሁነቶች የተከናወኑ ሲሆን፤ በተለይም በመንግሥትና በግሉ ሴክተር ተሳትፎ በሀገሪቱ ለመጀመሪያ ጊዜ የተገነባው የውጭ ምርቶች ማሳያ ቋሚ የኢግዚቢሽን ማዕከል በይፋ ተከፍቷል፡፡ በልዩ የንግድ ሳምንቱ በመንግሥትና በግሉ ዘርፍ መካከል የጋራ ምክክርና ውይይትም ተደርጓል፡፡ ከዚሁ በተጨማሪም ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ የተለያዩ ምርቶች በተመጣጣኝ ዋጋ ለህብረተሰቡ መቅረብ የቻለበትን ምቹ ሁኔታ ፈጥሯል፡፡

በንግድና ቀጠናዊ ትስስር መሥሪያ ቤት ቅጥር ግቢ ውስጥ በተዘጋጀው ኤግዚቢሽንና ባዛር አምራቾችና ጅምላ አከፋፋይ ነጋዴዎች የተለያዩ የምግብ ሸቀጦችን ይዘው ቀርበዋል፡፡ በኤግዚቢሽንና ባዛሩ ከቀረቡ ምርቶች መካከል የግብርና ምርቶችን ጨምሮ የተለያዩ የፋብሪካ ውጤት የሆኑ ምርቶች ለአብነትም ዘይት፣ ሩዝ፣ የሕፃናት ወተት፣ ፓስታ፣ ማካሮኒ፣ ዱቄትና ሌሎች ምርቶችም ቀርበዋል። በኤግዚቢሽንና ባዛሩ ምርቶቻቸውን ይዘው ከቀረቡ አምራች ኢንዱስትሪዎች መካከል የግብርና ምርት የሆኑ የአትክልትና ፍራፍሬ ምርቶችን ጨምሮ ቦይዝ ፓስታና ማካሮኒ፣ ዲኤች ገዳ ዱቄት ፋብሪካ፣ ቱሬ ጤፍና ሌሎችም ይገኙበታል፡፡

የዝግጅት ክፍላችን በኤግዚቢሽንና ባዛሩ ላይ በመገኘት ምርቶቻቸውን ይዘው ከቀረቡ አምራች ኢንዱስትሪዎች መካከል ጥቂቶቹን አነጋግሯል። በኤግዚቢሽንና ባዛሩ ላይ ተሳታፊ መሆናቸው ምን ጠቀሜታ አለው ሲል ላነሳላቸው ጥያቄም የሚከተለውን ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ የፋብሪካ ውጤት የሆነውን የጤፍ ዱቄት ይዞ የቀረበው ቱሬ ወይም ሶርስ ጤፍ አንዱ ነው፡፡ አቶ ከሊፋ አብዱልቃድር የቱሬ ጤፍ ወይም ሶርስ ጤፍ ፋብሪካ ማናጀር ናቸው፡፡

እሳቸው እንዳሉት በኤግዚቢሽንና ባዛሩ ላይ በዓይነቱ ለየት ያለና መቶ በመቶ ጥራት ያለው ንጹህ የጤፍ ዱቄት ለማህበረሰቡ በተመጣጣኝ ዋጋ ይዘው ቀርበዋል፡፡ የጤፍ ዱቄት በፋብሪካ ደረጃ አዘጋጅቶ ለገበያ ማቅረብ ሀገር ውስጥ ብዙም አልተለመደም። ነገር ግን ጤፍ በፋብሪካ ደረጃ በጥራት ማዘጋጀት ይቻላል፡፡ ድርጅቱ ጤፍን በጥራት እያዘጋጀ በማቅረብ ቀዳሚ ሲሆን፤ ለዚህም ዓለም አቀፍ ዕውቅና ካላቸው አይኤስኦ 9001 እና ኤፍኤስሲ 22000 ድርጅቶ ዕውቅና አግኝቷል፡፡ ቱሬ ወይም ሶርስ ጤፍ በሀገር ውስጥና በውጭ ተቆጣጣሪ ድርጅቶች ደንብ የሚተዳደር ፋብሪካ ነው፡፡

ቱሬ ወይም ሶርስ ጤፍ በ2009 ዓ.ም የተጀመረ ሲሆን፤ በአሁን ወቅት ገበያ ውስጥ በስፋት ገብቷል። ባለፉት ጊዜያት ማህበረሰቡ ጤፍን በዚህ መልክ በፋብሪካ ደረጃ አዘጋጅቶ የሚያቀርብ አልነበረም ሂደቱም ቢሆን በአብዛኛው ሰው የተለመደ አልነበረም። ይሁንና አሁን ላይ ግን ማህበረሰቡ እየለመደው በመምጣቱ ሰፊ የገበያ ፍላጎት መኖሩን መገንዘብ እንደቻሉ ተናግረዋል፡፡ ‹‹በተለይም አብዛኛው ሰው ጠዋት ወጥቶ ማታ የሚገባና መኖሪያ ቤቱና ሥራ ቦታው የተራራቀ በመሆኑ ጊዜና ጉልበትን መቆጠብ ችሏል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም በጥራት ተጠቃሚ ሆኗል። ምክንያቱም ቱሬ ወይም ሶርስ ጤፍ መቶ በመቶ የጤፍ የሆነ ዱቄት በጥራት አዘጋጅቶ ያቀርባል። በመሆኑም ተቀባይነቱ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ መጥቷል›› የሚሉት አቶ ከሊፋ፤ ምንም ዓይነት ባዕድ ነገሮች የማይቀላቀልበት እንደሆነ ሲያስረዱም ‹‹ፋብሪካ ውስጥ ጤፍ ብቻ ገብቶ ጤፍ ብቻ ይወጣል›› በማለት ነው፡፡

በኤግዚቢሽንና ባዛሩ ላይም ተሳታፊ መሆናችን ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታዎች ያሉት ሲሆን፤ ዋና ዓላማውም የሀገር ውስጥ ምርትን ለሀገር ውስጥ ዜጋ ወይም ለመላው ማህበረሰብ በጥራት እያቀረቡ እንደሆነ ማስተዋወቅ ነው ይላሉ፡፡ እሳቸው እንዳሉት፤ በኤግዚብሽንና ባዛሩ ላይ ተሳታፊ በመሆናቸው ቱሬ ጤፍን የማያውቁ የማህበረሰብ አካላትን እንዲያውቁት ሆኗል፡፡ የገበያ ትስስር መፍጠር ተችሏል፡፡ ቱሬ ወይም ሶርስ ጤፍ ምርቱን ከሀገር ውስጥ ባለፈ ወደ ውጭ ገበያ የማቅረብ ዕቅድ ያለው በመሆኑ እንዲህ ዓይነት መድረኮች የገበያ ትስስር ለመፍጠር አጋዥ ናቸው፡፡

ስምንት ዓመታትን ያስቆጠረው ቱሬ ወይም ሶርስ ጤፍ አሁን ላይ አቅርቦቱና ተደራሽነቱ ካለው ፍላጎት ጋር ተመጣጣኝ አይደለም ያሉት አቶ ከሊፋ፤ ድርጅቱ በቀጣዮቹ ዓመታት ምርትና ምርታማነቱን በማሳደግ ተደራሽነቱን ለማስፋት አቅዶ እየሰራ መሆኑን አመላክተዋል፡፡ ለዚህም ድርጅቱ የግብርና ሥራውን ጭምር በመሥራት የጤፍ ምርት በማምረት ጭምር የምርት አቅርቦቱን እንዲሁም ተደራሽነቱን ለማስፋት በሚያስችል እንቅስቃሴ ላይ መሆኑን ተናረዋል፡፡

በአሁን ወቅት ቱሬ ወይም ሶርስ ጤፍ አዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ባሉት ሰባት ቅርንጫፎች አማካኝነት በከተማ ውስጥ ለሚገኙ የማህበረሰብ አካላት ማለትም ግለሰቦችን ጨምሮ ሆቴሎች፣ ተቋማትና የተለያዩ ድርጅቶች ይገኙበታል፡፡ በቀጣይም ከከተማ ውጭ ለሚገኙ የማህበረሰብ አካላትም ተደራሽ የመሆን ዕቅድ ያለው ሲሆን፤ በቅርቡ ምርቶቹን ለክልል ከተሞች ተደራሽ ለማድረግ ዝግጅቱን አጠናቅቋል።

ቱሬ ወይም ሶርስ ጤፍ አሁን ላይ በተለያየ ዓይነትና መጠን ለገበያ እየቀረበ መሆኑን ያነሱት አቶ ከሊፋ፤ በዓይነት ነጭና ቀይ ጤፍ መሆኑን ጠቅሰው በመጠን ደግሞ በ10 እና በ25 ኪሎ ግራም ነው ብለዋል፡፡ ይህም ማለት ቀይ ጤፍ ባለ 10 እና ባለ 25 ኪሎ ግራም እና ነጭ ጤፍ ባለ 10 እና ባለ 25 ኪሎ ግራም መጠን ያላቸው ናቸው፡፡

‹‹የጤፍ ዱቄት በተለምዶ ወፍጮ ቤት ሄዶ ይፈጫል›› ያሉት አቶ ከሊፋ የቱሬ ወይም የሶርስ ጤፍ ጥራትና ደህንነቱ የተጠበቀ የጤፍ ዱቄት ማዘጋጀትን ዋና ዓላማ አድርጎ ነው የተነሳው፡፡ በመሆኑም በተለምዶ ወፍጮ ቤት የሚፈጨውን ጤፍ ዘመናዊ በሆነ መንገድ በፋብሪካ ተዘጋጅቶ በጥራት ማቅረብ ለሁሉም ጠቃሚ እንደሆነ አብራርተዋል፡፡ እሳቸው እንዳሉት በአዲስ ግኝት ልዩ በሆነ ሁኔታ ጤፍ ብቻ የሚፈጭ ማሽን ዲዛይን በማስደረግ ከቻይና አስመጥተዋል፡፡ በመሆኑም ማሽኑ አገልግሎት የሚሰጠው ለጤፍ ብቻ ሲሆን፤ ይህም ለጥራትና ደህንነት ትልቅ ግምት መሰጠቱን ያሳያል፡፡

የጤፍ ዱቄት በምን ያህል መጠን መድቀቅ እንዳለበት ጭምር በላቦራቶሪ የተረጋገጠ ሲሆን፤ የተለያዩ ጥናቶች ተሰርተውለት ከባዕድ ነገሮች ነፃ መሆኑም ተረጋግጧል፡፡ አቶ ከሊፋ፤ የፍጭት ቦታውም ጥራቱን በጠበቀ መንገድ የተዘጋጀ ስለመሆኑ ሲያስረዱ የጤፍ ዱቄቱ ደረጃውን በጠበቀ መንገድ የሚዘጋጅ እንደሆነና ገበያ ውስጥም በስፋት እየገቡ እንደሆነ ተናግረዋል፡፡ ‹‹ዋጋውን አስመልክቶም ቱሬ ወይም ሶርስ የጤፍ ዱቄቱ ለሸማቹ እየቀረበ ያለው ተመጣጣኝ በሆነ ዋጋ ነው፡፡›› ያሉት አቶ ከሊፋ፤ ይህን ለማረጋገጥ ከፍተኛ ቁጥር ያለው ደንበኛ አንዱ ሲሆን፤ ሌላው በምግብ ኢንዱስትሪ ውስጥ ጥራት ያለውና ደህንነቱ የተጠበቀ ምርት ማቅረብ በራሱ በተመጣጣኝ ዋጋ እንደ ማቅረብ ነው ብለዋል፡፡

በኤግዚቢሽንና ባዛሩ ከምግብ ሸቀጦች ውጭ የሆኑ የተለያዩ ቁሳቁሶችም ቀርበዋል፡፡ ከእነዚህም መካከል አንዴ ማማ የተባለ የተለያዩ የእጅ ሥራዎችን ከወዳደቁ ቁሶች የሚሰራ አምራች ድርጅት አንዱ ነው፡፡ ሃና ግርማ የአንዴ ማማ ማርኬተር ናት፡፡ እሷ እንዳለችው አንዴ ማማ የወዳደቁ ቁሳቁሶችን መልሶ ጥቅም ላይ ማዋልን ዓላማ አድርጎ የተመሰረተው ድርጅት ነው፡፡ ድርጅቱ ወደ ሥራው ከገባ ሶስት ዓመታትን አስቆጥሯል። የሚያመርታቸው ምርቶች በዋናነት የቤት ውስጥ ቁሳቁሶችና ለመሥሪያ ቤት መገልገያ የሚውሉ ናቸው፡፡

አንዴ ማማ እነዚህን ቁሳቁሶች ለማምረት አነስተኛ ገቢ ያላቸውንና አቅመ ደካማ የሆኑ በመንግሥት መሥሪያ ቤት ውስጥ በጽዳት ሥራ ላይ የተሰማሩ እናቶችን ምርጫው ያደረገ ሲሆን፤ ከሴቶችና ሕፃናት፣ ከክፍለ ከተማና ከወረዳ ጋር በጋራ በመሆን ይሰራል። ለእነዚህ እናቶችም ድርጅቱ በቅድሚያ የተለያዩ ሥልጠናዎችን በመስጠት ወደሥራ እንዲገቡ ያደርጋል። ሥልጠናውን በነፃ በመስጠት እናቶቹ የተለያዩ ቁሳቁሶችን ማምረት የሚያስችላቸውን ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል፡፡

ሥልጠናውን ያገኙት እናቶችም የቤት ውስጥ መገልገያ የሆኑ የተለያዩ ቁሳቁሶችን እና ጌጣጌጦችን ያመርታሉ፡፡ ከቤት ውስጥ ቁሳቁሶች በተጨማሪም ለቢሮ አገልግሎት የሚውሉ ቁሳቁሶችን አምርተው ለገበያ ያቀርባሉ፡፡ ለእነዚህ ምርቶች ታዲያ በዋናነት የሚጠቀሙት ጥሬ ዕቃ ጋዜጣና መጽሔትን ጨምሮ አገልግሎታቸው ያበቃና የተጣሉ ወረቀቶችን ነው፡፡ እነዚህን ወረቀቶች ለማግኘትም ባንኮችን ጨምሮ 500 ከሚደርሱ ተቋማት ጋር በጋራ ይሰራል። ጋዜጦቹን ሊያበላሽ የሚችለው ውሃ ብቻ እንደመሆኑ ወረቀቱ እንዳይበላሽ ወተር ፒሩፍ ይቀባል፡፡

በውሃ እንዳይበላሹ ወተር ፒሩፍ የተቀቡትና በቀጫጭኑ በቲዩብ የተጠቀለሉት ጋዜጦችም ስልጠና የወሰዱ እናቶች እጅ ሲደርሱ የተለያየ የቤት ውስጥ መገልገያ ቁሳቁስ መሆን ይችላሉ፡፡ እናቶቹ በቤታቸው ሆነው ለሚሰሩት ሥራ ከወረቀቶቹ በተጨማሪ ኮላ ይጠቀማሉ፡፡ በአሁን ወቅትም በሰሩት መጠን የሚከፍላቸው 700 እናቶች ስለመኖራቸው ያነሳችው ወጣት ሃና ከወዳደቁ ወረቀቶች የሚመረቱ ቁሳቁሶች ለገበያ እየቀረቡ እንደሆነ ተናግራለች፡፡ እናቶቹ ከሚሰሯቸው የእጅ ሥራዎች መካከልም ቅርጫት፣ ግድግዳ ላይ የሚሰቀሉ የተለያዩ ጌጣጌጦች፣ ቢዝነስ ካርዶች፣ መመገቢያ ሳህን፣ የግድግዳ ሰዓት ይጠቀሳሉ፡፡

ምርቶቹ በአብዛኛው በትዕዛዝ የሚሰሩ ሲሆን፤ እንዲህ ዓይነት ኤግዚብሽንና ባዛሮች ላይ እንደሚሸጡ የገለጸችው ወጣት ሃና፤ ንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር መሥሪያ ቤት ባዘጋጀው ኤግዚቢሽንና ባዛር መሳተፍ መቻላቸው የጎላ አበርክቶው ያለው መሆኑን ነው ያስረዳችው፡፡ በተለይም ከመንግሥት የሥራ ኃላፊዎች ጋር እንዲሁም ከማህበረሰቡ ጋር ፊት ለፊት የመገናኘትና የመተዋወቅ ዕድል ይፈጠራል። ከሚፈጠረው የገበያ ትስስር በባለፊም ሰዎች የተለያዩ የፈጠራ ሥራዎችን በቀላሉ መሥራት እንደሚችሉ ግንዛቤ ለመፍጠር ያግዛል፡፡ በመሆኑም በኢትዮጵያውያን እናቶች የሚሰሩትን የእጅ ሥራዎች ማህበረሰቡ ገዝቶ በመጠቀም እናቶችን ይደግፍ ያበረታታ በሀገሩ ምርት ይኩራ በማለት መልዕክት አስተላልፋለች፡፡

‹‹የኢትዮጵያን ይግዙ›› በሚል መሪ ሃሳብ ለአምስት ቀናት ሲካሄድ በቆየው ልዩ የንግድ ሳምንት በርካታ የምግብ ሸቀጦች በተመጣጣኝ ዋጋ ቀርበው ሸማቹ ሲሸምት ሰነባብቷል፡፡ ከመደበኛው ገበያ በተሻለ ዋጋ በኤግዚቢሽንና ባዛሩ ላይ ከቀረቡ ምርቶች መካከል ለአብነት ዘይት ተጠቃሽ ነው፡፡ በመደበኛው ገበያ ከአንድ ሺ አንድ ብር እስከ አንድ ሺ ሰባ ብር ድረስ የሚሸጠው ባለ አምስት ሊትር ዘይት በአንድ ሺ ብር ተሸጧል፡፡ እንዲሁም በመደበኛው ገበያ ከ80 ብር በላይ የሚሸጠው ፓስታ በ70 ብር ከሃምሳ ሳንቲም፣ ሲሸጥ ቆይቷል፡፡ ለንጽህና አገልግሎት የሚውሉ የተለያዩ ደረቅ እና ዲተርጀንት ሳሙናዎች እንዲሁም ሌሎች ምርቶች በተመጣጣኝ ዋጋ ሲሸጥ እንደነበር መመልከት ችለናል፡፡

በንግድ ሳምንቱ ማጠቃለያ የተገኙት የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስትር ካሣሁን ጎፌ (ዶ/ር) በንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር አዘጋጅነት በሀገር አቀፍ ደረጃ ለመጀመሪያ ጊዜ የተዘጋጀው የንግድ ሳምንት ዋናው ዓላማ የሀገር ውስጥ አምራቾችን ማበረታታት እንደነበር ጠቅሰዋል፡፡ እሳቸው እንዳሉት፤ የሀገር ውስጥ የእጅ ባለሙያዎችን፣ ሥራ ፈጣሪዎችንና ነጋዴዎችን ማበረታታት ለነገዋ ኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ነው፡፡ በመሆኑም መላው ኢትዮጵያውያን የኢትዮጵያን ምርትና አገልግሎት በመግዛትና በመጠቀም ለነገዋ ኢትዮጵያ ኢንቨስት ሊያደርጉ ይገባል፡፡ መንግሥትም በሁሉም ዘርፎች ምርትና ምርታማነትን የማሳደግ ተጨማሪ የንግድ ዕድሎችን የማመቻቸት፣ የንግድ ሥርዓቱን ለማዘመን የሚረዱ የፖሊሲ እና የሕግ ማሻሻያዎችን በማድረግ እንዲሁም የንግዱን ዘርፍ ተዋንያኖች አቅም የማሳደግ ሥራ ይሰራል፡፡

መንግሥት ተወዳዳሪ የንግድ ሥርዓትን ለመገንባት፣ የገቢና የወጪ ንግዱን ለማሳለጥ በርካታ የፖሊሲና የሕግ ማሻሻያዎችን አድርጓል፡፡ መንግሥት ካደረጋቸው ማሻሻያዎች ውስጥ በቅርቡ የተደረገው የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ ተጠቃሽ ሲሆን፤ ይህም የሀገሪቱን የንግድ ሥርዓት ለማዘመን ትልቅ ድርሻ ይኖረዋል፡፡ በመሆኑም መንግሥትና የግሉ ዘርፍ መናበብ፣ መቀናጀትና መወያየት ከቻሉ የምናስባትን ታላቅ ሀገር በአጭር ጊዜ እውን ማድረግ ይቻላል።

መዝናኛ

# ማረፊያ/ትዝብት

## የጋዜጠኝነት ሙያ ራሱን ጣለ ወይስ ሌሎች ጣሉት?

**ዋስልኝ አየለ**

አንድ ባለሦስተኛ ዲግሪ (ፒ. ኤች. ዲ) የሀገራችን ምሑር አንድ የመዝናኛ ፕሮግራም ላይ ቀረቡ፡፡ የመዝናኛ ፕሮግራም አዘጋጁ «አዲስ ዘመን ጋዜጣን፣ ሪፖርተር ጋዜጣን እና አዲስ አድማስ ጋዜጣን አንድ ቦታ ላይ ተዘርግተው ቢያገኟቸው የትኛውን ያነሳሉ?» ብሎ ጠየቃቸው፡፡ ምሑሩ በማጣጣል እና በንቀት ድምጸት «አንዱንም አላነሳም!» ካሉ በኋላ «ምናልባት ለዕቃ መጠቅለያ ከሆነ አዲስ ዘመን ጋዜጣን ላነሳ እችላለሁ» አሉ፡፡ ታዝቧቸው ይሁን አላውቅም ጠያቂው አልሳቀላቸውም፡፡

ምናልባት የእነ «ዋሽንግተን ፖስት» እና «ዘ ጋርዲያን» ደንበኛ የሆኑት እኚህ ኢትዮጵያዊ ምሑር ሃገራቸው እንደ አሜሪካ ወይም እንግሊዝ እንድትሆን ምን ሠርተው ይሆን?

«ለራስ ሲቆርሱ አያሳንሱ» እንዳይሆንና ራስን በራስ መገምገም ልክ ስለማይሆን አዲስ ዘመን ጋዜጣን እንተወው።እውነት ሪፖርተር ጋዜጣ ለዚያ ሰውየ አነሰ? አዲስ አድማስ ጋዜጣ ለዚያ ሰውየ አነሰ?

ሰውየው የሥነ ጽሑፍ ሰው ናቸው፡፡ አዲስ አድማስ ጋዜጣ ደግሞ የሥነ ጽሑፍ ሥራዎች የሚተነትኑበት ነው። ራሳቸው ሰውየውን ጨምሮ ብዙ ደራሲያን እና ሃያሲያን ይጽፉበታል፤ ይከራከሩበታል፡፡ የመጻሕፍት ዳሰሳ እና ሂስ ይሠራበታል፡፡ ይህን ጋዜጣ ነው እንግዲህ የሥነ ጽሑፍ ሰው ነኝ የሚሉት ሰውየ «አላነሳውም» ያሉት፡፡ ሲያነቡት ብቻ ሳይሆን ሲጽፉበት የቆየ ጋዜጣ ነው እኮ! ታዲያ ለምን «አላነሳውም!» አሉ? የሚያስመሰግንና የሚያስወድድ ስለመሰላቸው፡፡ የምሑርነት መገለጫ ስለመሰላቸው፡፡ «አይመጥነውም» እንዲባልላቸው!

ሦስቱም ጋዜጦች የተለያዩ ናቸው፡፡ አዲስ ዘመን ጋዜጣ መንግሥታዊ ጉዳዮችና እንቅስቃሴዎች የሚበዙበት ነው፡፡ ምንም እንኳን ሰውየው ከመንግሥታዊ መድረኮች የማይጠፉ ቢሆኑም «መንግሥትን የሚያወድስ ጋዜጣ አላነብም!» ብለው ነው እንበል፡፡ ሪፖርተር ጋዜጣ ግን በተቃራኒው መንግሥትን የሚነቅፉ ነገሮችን የሚዘግብ ነው፡፡ ታዲያ ሰውየው ምንድነው የሚሻላቸው? ምን ቢሆን ነበር የሚያነቡት? የፖለቲካ ጋዜጦችም፣ የሥነ ጽሑፍ ጋዜጦችም ካልመጠኗቸው እርሳቸውን የሚመጥን ምን ቢጻፍ ነበር?

ሰውየው የቀረቡበት ፕሮግራም የመዝናኛ ፕሮግራም ነው፡፡ በብዛት አርቲስቶች እና በማኅበራዊ መገናኛ ዘዴዎች መነጋገሪያ የሆኑ ወጣቶች የሚቀርቡበት ነው፡፡ ፕሮግራሙ የመዝናኛ ስለሆነ የሚጠየቁት ጥያቄም ሰዎችን ለማዝናናት ነው፡፡ ምሑሩ ከዚያ ፕሮግራም ላይ ነው የቀረቡት። የቀረቡት ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ቀጣናዊ ጉዳዮችን ሊተነትኑ አይደለም፡፡ በወቅቱ መጽሐፍ ጽፈው ስለነበር እና ፕሮግራሙ ብዙ ተመልካች ስላለው መጽሐፋቸውን ለማስተዋወቅ ነው፡፡ ምናልባትም የፕሮግራሙን ባለቤት አቅርበኝ ብለው በአማላጅ ለምነውም ሊሆን ይችላል፡፡

ይቺን አንድ ነጠላ ምሳሌ ያነሳሁት የመንጋ ድጋፍ ፍለጋ ምሑራን ድረስ እንደሄደ ለማሳየት ነው፡፡ ለምሳሌ፤ ከምሑሩ የሚጠበቀው ምሑራዊ በሆነ መንገድ «ይሄኛው ይሄ ችግር አለበት፣ ይሄኛው በዚህ በኩል ቢሻልም ይህን ግን ማስተካከል አለበት....» የሚል ነበር፡፡ እርሳቸው የፈለጉት ግን በማጣጣል እና በመሳደብ የተለየ ብቃት ያለው መስሎ መታየት ነው፡፡ ይህ የብዙዎች ችግር ነው፡፡ ተረጋግተው በትሕትና ማስረዳት አይችሉም፡፡ ምሑራን እንዲህ ከሆኑ ሌላው ምንም ቢል እና ምንም ቢያደርግ አይገርምም ማለት ነው፡፡

የኢትዮጵያ ጋዜጠኝነት አደገኛ ችግሩ ፍረጃ ነው። ብዙዎች በራሳቸው ግምገማ እና በራሳቸው መረዳት ከመወሰን ይልቅ ሲባል በሚሰሙት መሄድን ይመርጣሉ። «እገሌ ጋዜጠኛ እኮ ጎበዝ ነው» ከተባለ ሥራውን ማየት አይጠበቅባቸውም፡፡ ተከትሎ ማድነቅ ነው፡፡ «ሚዲያ ማለት እገሌ ነው...» ከተባለ ምንም አይነት ጥፋት ይሥራ ሁሌም ትክክል ነው፡፡ ሌላ አንድ ምሳሌ ልጥቀስ፡፡

አንድ በብዙዎች ዘንድ ተመራጭ ነው የሚባል የኤፍ ኤም ሬዲዮ አለ፡፡ ብዙዎች ሲሉ እንደምሰማው የሚወደደው ዜና ላይ በሚጠቀማቸው ቃላት ነው፡፡ ቃላቱ ግን የዜና ቃላት አይደሉም፡፡ ለማሳመር ሲባል የሚጠቀማቸው ቃላት ትርጉም ያዛባሉ፡፡ ለምሳሌ፤ የኮቪድ-19 ወረርሽኝ አስፈሪ በነበረበት ወቅት ይህን ዜና ሰማሁ፡፡ «አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎቼን ለመፈተን ኮሮና የሚባለው ነገር አይበግረኝም አለ» ይላል፡፡

በወቅቱ በነበረው አስፈሪነት ይህ ዜና አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲን ሊያስከስስ ሁሉ ይችል ነበር፡፡ ምክንያቱም በወቅቱ ኮሮናን እንዲህ ማጣጣል ጥፋትን ማወጅ ነው፡፡ ደግነቱ ዩኒቨርሲቲው እንደዚያ አላለም፡፡ የዜናው ዝርዝር ሲሰማ፤ ዩኒቨርሲቲው የተናገረው «የአፍና የአፍንጫ መሸፈኛ በመጠቀም፣ እጅን በመታጠብ እና ርቀታቸውን ጠብቀው በመቀመጥ....» የሚል ነው፡፡ በዚህ ጥንቃቄ ደግሞ የትኛውም የሥራ እንቅስቃሴ እየተከናወነ ነበር፡፡ ይህንን ነው እንግዲህ ያ ተወዳጅ ሬዲዮ ጣቢያ «ኮሮና አይበግረኝም!» አለ ያለው፡፡

አንድ ጊዜ ደግሞ ይሄው ጣቢያ በተወሰኑ የተሽከርካሪ አይነቶች ላይ የሰዓት ገደብ ተደርጎ፤ «በአዲስ አበባ ከተማ ዝር እንዳይሉ ተባለ» ብሎ ሲሠራ ሰማሁት፡፡ «ዝር እንዳይሉ!» ማለት እኮ ጭራሹንም እንዳይታዩ ማለት ነው፡፡ እንዲህ አይነት ቃላት ለመደበኛ ዜና (hard news) አይሆኑም፡፡ ግን ችግሩ ጣቢያው የተወደደለት ይሄ ነገሩ ነው፡፡ ምክንያቱም ከሙያዊ ይልቅ ለመንጋ ድጋፍ ትኩረት ይሰጣል፡፡ ስናደንቅም ሆነ ስንደግፍ በጭፍን ነው፡፡ እናደንቀዋለን በምንለው ነገር ላይ ምንም አይነት ህፀፅ አይታየንም፡፡ በጠላነው ነገር ላይ ምንም አይነት በጎ ነገር አይታየንም፡፡ ነገሮችን ሙያዊ ሆኖ ማየት የሚባል ነገር የለም፡፡ ምሑራኑም ሲያደንቁም ሆነ ሲወቅሱ «ይህንን ብናገር» ምን ያህል ሰው ይወደኛል ወይም ይጠላኛል በሚል ታሳቢነት እንጂ ሕሊናቸውን ተከትለው አይደለም፡፡

ይህን ሁሉ ያስታወሰኝ በቅርቡ የተደረገው «ሚዲያ አዋርድ» ነው፡፡ ነገርየውን ማስተዋወቅ ከተጀመረበት ጊዜ ጀምሮ በማኅበራዊ ገጾች የነበረውን እንቅስቃሴ እያስተዋልኩ ነበር፡፡ ራሳቸው ጋዜጠኛ የሚባሉት ሳይቀር ስለጋዜጠኝነት ግንዛቤ አልነበራቸውም ማለት ነው፡፡ ቅስቀሳ ሲያደርጉ የነበረው በጓደኝነት ነበር፡፡ ጓደኞቼ በይሉኝታ መርጠውኝ ምርጥ ጋዜጠኛ ነኝ ለማለት ያስችለኛል ወይ? አንዳንድ የክፍለ ከተማ ወጣቶች «የእኛ ሰፈር ልጅ ስለሆነ የዚህ ሰፈር ሰዎች ምረጡ...» ሲሉ ሁሉ ነበር፡፡ ሙያዊ ነገር እንዴት በትውውቅ ይመረጣል?

ምናልባት «ዕድሉን ስላላገኘህ ቀንተህ ነው» የሚል ይኖር ይሆናል፡፡ የዚህ ውድድር ዕጩ ነበርኩ፡፡ አንድም ሰው ግን «ምረጡኝ» ብየ አላውቅም፡፡ የጓጓሁት «የተመረጠው ሥራዬ በባለሙያዎች ይወደድ ይሆን?» ብዬ ነበር፡፡ ዳሩ ግን የታየው በባለሙያ ሳይሆን በመንጋ ውሳኔ ነበር፡፡ በባለሙያ ቢሆን የእኔ ይመረጥ ነበር እያልኩ አይደለም፤ ሁሉ ነገሩ የተምታታበትና የተደበላለቀበት ስለነበር ባለሙያ እንዳልገባበት ስለሚያስታውቅ ነው፡፡ ከሁኔታው እንደምንረዳው፤ ያደረጉት እንደሚከተለው ነው፡፡

ከእገሌ ሚዲያ ብንመርጥ ሰው ምን ይለናል? እገሌን ባንመርጠው ምን ሊጎዳን ይችላል? እገሌ ታዋቂ ስለሆነ ብንመርጠው ምን ይጠቅመናል? ማን ከባለሀብት እና ከፋይናንስ ተቋማት ጋር ሊያገናኘን ይችላል? በሚል ነው። ነገርየው የቢዝነስ ጉዳይ ስለነበር «ማንን ብንመርጥ ያዋጣናል?» በሚል ነው፡፡ የቢዝነሱ ጉዳይ ይሳካ እንጂ ማንም ቢንጫጫ ምንም አያመጣም በሚል ድምዳሜ ነው፡፡

ለመሆኑ «ምርጥ ዜና አንባቢ ማለት ምን ማለት ነው?» የድምፁ ማማር ከሆነ፤ መወዳደር ያለበት የድምፅ አይዶል ነው፡፡ የአካላዊ ቁመናው ማማር ከሆነ፤ መወዳደር ያለበት የቁንጅና ውድድር ነው፡፡ ያነበበው ዜና ሀሳብ ከሆነ፤ መሸለም ያለበት ዜናውን የሠራው ዘጋቢ ነው፡፡ ብዙ ዜና አንባቢዎች ራሳቸውም ጋዜጠኛ ናቸው፡፡ ስለዚህ ያነበበውን ዜና የሠራው ራሱ ከሆነ መደነቅ ያለበት በሠራው ዜና ነው፡፡ በአንባቢነት ብቻ ከሆነ ግን አንድ የፋና ወይም የኢቲቪ ዜና አንባቢ ከዋልታ ወይም ኤን. ቢ. ሲ ዜና አንባቢ የሚለየው በምንድነው? አቀራረብን በተመለከተ ሁሉም የየራሳቸው «ስታይል» አላቸው፤ ምኑ ከምን ተወዳድሮ ነው «ምርጥ» የሚሆነው? ሙያዊ መለኪያው የተለየ አይሆንም ወይ?

ዜና ወይም አርቲክል ከሆነ ግን «የማኅበረሰብ ችግር ፈቺነቱ፣ መረጃ ሰጪነቱ፣ አስተማሪነቱ፣ ምርመራነቱ....» እየተባለ ሊገለጽ ይችላል፡፡ ስለዚህ ሽልማቱ ትኩረት ያደረገው ሙያዊ ጉዳይ ላይ ሳይሆን ታዋቂነት ላይ ነው፡፡

ይህ ሁሉ ሲሆን ግን ጋዜጠኞችም የሙያው ተቆርቋሪ አልሆኑም፡፡ የኢትዮጵያ የጋዜጠኝነት ሙያ በተደጋጋሚ የሚወቀሰው ባለሙያው ራሱን ስለጣለ ነው፡፡ «እንዴት ሙያውን ያክብር?» የሚለውን በሌላ ክፍል እናየዋለን፡፡

# ዓለም አቀፍ

## ዩናይትድ ኪንግደም አንዳንድ የጦር መሣሪያዎች ለእሥራኤል እንዳይሸጡ አገደች

ዩኬ ለእሥራኤል የምትሸጣቸው አንዳንድ የጦር መሣሪያዎች ዓለም አቀፍ ሕግ የሚጥስ ተግባር ሊፈፀማባቸው ስለሚችል በሚል ሽያጯን መግታቷን አስታውቃለች። የዩኬ ውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ዴቪድ ላሚ ሀገራቸው ወደ እሥራኤል ከምትልካቸው 350 የጦር መሣሪያዎች መካከል 30 የሚሆኑትን አግዳለች ብለዋል።

ወደ እሥራኤል እንዳይላኩ ከታገዱት የጦር መሣሪያዎች መካከል የጦር አውሮፕላኖች፣ ሄሊኮፕተሮች እና ድሮኖች ይገኙበታል። አንድ የእሥራኤል ባለሥልጣን የዩኬ ውሳኔ “የተሳሳተ መልዕክት የሚያስተላልፍ እና የሚያበሳጭ ነው” ሲሉ ተናግረዋል። ሚኒስትር ላሚ፤ እሥራኤል ራሷን የመከላከል መብቷን ዩኬ ትደግፋለች ብለው ይህ ውሳኔ የጦር መሣሪያ ማዕቀብ ተደርጎ መወሰድ እንደሌለበት አሳስበዋል።

የእሥራኤል የዲያስፖራ ጉዳዮች ኃላፊ የሆኑት አሚቻይ ቻክሊ ይህ ውሳኔ እሥራኤል በሐማስ ታግተው የተገደሉባት ስድስት ዜጓችን እየቀበረች ባለች ወቅት መሆኑ “ስሜታዊ” ያደርገዋል ብለዋል። “ከኢስላሚክ ስቴት ግሩፕ፣ ከአል-ቃዒዳ እና ሐማስ ጋር የሚደረገው ጦርነት ተመሳሳይ ነው። ይህ ጦርነት በምዕራባዊ ሥልጣኔ እና በአክራሪ ኢስላም መካከል የሚደረግ ነው” ብለዋል።


የእሥራኤል ውጭ ጉዳይ ሚኒስትር እስራኤል ካትዝ ውሳኔውን ተከትሎ በሰጡት አስተያየት ሀገራቸው ዓለም አቀፍ ሕግን ተከትላ እርምጃ እየወሰደች እንዳለች ተናግረዋል። ሌሎችም በዩናይትድ ኪንግደም ውሳኔ ደስተኛ ያልሆኑ ከፍተኛ የእሥራኤል ባለሥልጣናት በማኅበራዊ ሚዲያ ገፆቻቸው በውሳኔው የተሰማቸውን እያጋሩ ይገኛሉ።

የአምነስቲ ኢንተርናሽናል የዩኬ ኃላፊ የሆኑት ሳሻ ዴሽሙኽ በበኩላቸው ዕገዳው “በጣም ውሱን እና በተለያዩ ክፍተቶች የተሞላ ነው” ሲሉ አጣጥለውታል። ምዕራባውያን መንግሥታት ከእሥራኤል ጋር የሚያደርጉትን የጦር መሣሪያ ንግድ ተከትሎ ወቀሳ እየደረሰባቸው ሲሆን እስራኤል በሐማስ ላይ በከፈተችው ጦርነት ምክንያት በጋዛ ሰርጥ እየፈፀመችው ባለው ተግባር ትችት ይቀርብባታል።

የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ እንዳሉት በርካታ የሕዝብ እንደራሴዎች፣ የሕግ ሰዎች እና ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ብሪታኒያ ወደ እሥራኤል የምትልከውን የጦር መሣሪያ አስመልክቶ ያላቸውን ስጋት አጋርተዋል። አዲሱ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ባለፈው ሐምሌ ወደ ሥልጣን እንደመጡ ብሪታኒያ ወደ እስራኤል የምትልከውን የጦር መሣሪያ መገምገማቸውን ተናግረዋል።

ላሚ፤ ግምገማው “እሥራኤል ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብት ሕግጋትን ጥሳለች ወይ?” የሚለውን አልተመለከተም ብለው “ይህ ነፃ የመሆን አሊያም የወንጀለኝነት ፍርድ አይደለም” ሲሉ የሀገራቸውን ውሳኔ ተከላክለዋል። የዩኬ መንግሥት ውሳኔውን ባሰፈረበት ወቅት እሥራኤል በጋዛ ያለውን እርዳታ እንዴት ታየዋለች እንዲሁም በቁጥጥር ሥር ያሉ ሰዎች እንዴት ትንከባከባለች የሚለውን ከግምት ማስገባቱን አስታውቋል።

ተንታኞች ውሳኔው ከወታደራዊ አንድምታው ይልቅ ፖለቲካዊው ያመዝናል ይላሉ። እሥራኤል አንድ በመቶ የጦር መሣሪያ ብቻ ነው ከዩኬ የምታስገባው። ዩናይትድ ስቴትስ ከፍተኛውን የጦር መሣሪያ ለእሥራኤል የምትልክ ሲሆን እሥራኤል ከምታስመጣቸው የጦር መሣሪያዎች መካከል 69 በመቶ ከአሜሪካ ነው የሚመጡት ሲል ቢቢሲ ዘግቧል።



የዩኬ ውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ዴቪድ ላሚ፣

## የሀውቲ ታጣቂዎች በሁለት ነዳጅ ጫኝ መርከቦች ላይ ጥቃት አደረሱ



የሀውቲ ታጣቂዎች ሁለት ነዳጅ ጫኝ መርከቦችን ማጥቃታቸውን የአሜሪካ ጦር ገለጸ። የአሜሪካ ጦር በኢራን የሚደገፉት የሀውቲ ታጣቂዎች ሁለት ድፍድፍ ነዳጅ የጫኑ መርከቦችን ነሐሴ 27 ቀን 2016 ዓ.ም በቀይ ባሕር ላይ አጥቅተዋል ብሏል።

ጦሩ እንደገለጸው ከሆነ ጥቃት የደረሰባቸው መርከቦች የሳዑዲ ሰንደቅ ዓላማ ስታውለበልብ የነበረችው አምጃድ እና የፓናማ ሰንደቅ ዓላማ ስታውለበለብ የነበረችው ብሉ ላጉን ናቸው። ሀውቲዎች ሰኞ ምሽት ብሉ ላጉንን በበርካታ ድሮኖች እና ሚሳይሎች ማጥቃታቸውን ያመኑ ሲሆን ስለሳዑዲ መርከብ ጉዳይ ግን ምንም ያሉት ነገር የለም።

የአሜሪካ ማዕከላዊ እዝ ሀውቲዎች ሁለቱን መርከቦች በሁለት ሚሳይሎች እና ድሮን ዒላማ ማድረጋቸውን እና መምታታቸውን ገልጿል። ሁለቱም መርከቦች ነዳጅ ጭነው ነበር ያለው የአሜሪካ ጦር መግለጫ ጥቃቱን “ሀውቲዎች የፈጸሙት ኃላፊነት የጎደለው የሽብር ድርጊት” ሲል ገልጾታል። ሮይተርስ ሁለት ምንጮችን ጠቅሶ እንደዘገበው መርከቦቹ በሚመቱበት ወቅት ተቀራርበው ሲጓዙ ነበር። የደረሰው ጥቃት ቀላል በመሆኑ መርከቦቹ ጉዟቸውን መቀጠላቸውም ተገልጿል።

ሁለት ሚሊዮን በርሜል ድፍድፍ ነዳጅ የጫነችው የሳዑዲዋ አምጃድ መርከብ ባለቤት የሆነው ሳዑዲ ናሽናል ሺፒንግ ግሩፕ ባሕሪ ስለጉዳዩ አስተያየት አለመስጠቱን ዘገባው ጠቅሷል። ብሉ ላጉን የሚያስተዳድረው የግሪኩ አስተዳዳሪ ሲ ትሬድ ማሪን ኤስኤ በተመሳሳይ ስለጉዳዩ መልስ አልሰጠም። የሱዝማዝ ታንከሯ የመጨረሻ የመጫን አቅሟ አንድ ሚሊዮን በርሜል ነዳጅ እንደሚሆን ተገልጿል።

የሳዑዲዋ መርከብ በቀጥታ ዒላማ ተደርጋለች ላይሆን እንደሚችል ዘገባው ምንጮችን ጠቅሶ ዘግቧል። የዓለም ትልቋ ነዳጅ አምራች ሳዑዲ ዓረቢያ ሀውቲዎች መርከቦችን ዒላማ ለማድረግ በግዛቷ ላይ ሲተኩሱ በከፍተኛ ጥንቃቄ እየተመለከተቻቸው ነው። ሳዑዲ ዓረቢያ ምስቅልቅል ካስከተለው የየመን ጦርነት ራሷን ለመነጠል እየሞከረችም ነው።

የሀውቲ ታጣቂዎች በቀይ ባሕር እና በኤደን ባሕረ ሰላጤ በሚንቀሳቀሱ መርከቦች ላይ ከባለፈው ኅዳር ወር ጀምረው ጥቃት እያደረሱ ያሉት ከእስራኤል ጋር እየተዋጋ ላለው ሀማስ አጋርነት ለማሳየት ነው ማለታቸው ይታወሳል። ሀውቲዎች እስካሁን በፈጸሟቸው ጥቃቶች የሰጠሙ መርከቦችም አሉ። ሀውቲዎች ይህን ጥቃት የማያቆሙት በጋዛ ተኩስ ሲቆም ነው ብለዋል።

አሜሪካ እና አጋሮቿ ሀውቲዎች እያደረሱት ያለውን ጥቃት ለማስቆም የመን ውስጥ ዘልቀው በመግባት የሀውቲ ይዞታዎች ቢደበድቡም፣ ጥቃቱን ማስቆም አልቻሉም ሲል አል ዐይን ዘግቧል።

# የአቪዬሽን ሕግና የተጓዦች...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

አቀፍ ተቋማትና ግለሰቦች ግን አየር መንገዱን አወድሰውታል።

በተመሳሳይ የኢትዮጵያ አየር መንገድም ሰሞኑን ከክረምቱ ጋር ተያይዞ ባጋጠመ ጭጋጋማ የአየር ሁኔታ ምክንያት በረራዎች እንዲሰረዙና እንዲራዘሙ ምክንያት ሆኖ ነበር። ነሐሴ 16 ቀን ብቻ 42 ዓለም አቀፍ በረራዎች ቦሌ ዓለም አቀፍ የአየር ማረፊያ ማረፍ ባለመቻላቸው አቅራቢያ ወዳሉ አየር መንገዶች ለማረፍ መገደዳቸውንም አየር መንገዱ አስታውቋል።

በዚሁ ቀን ከሰዓት በኋላም ወደ መቀሌ ተጉዘው የነበሩ ሁለት አውሮፕላኖች በጭጋጉ የተነሳ ማረፍ ሳይችሉ ወደ አዲስ አበባ ተመልሰዋል። በዚህም ምክንያት ወደ መቀሌ ለመጓዝ በዝግጅት ላይ የነበረው ሦስተኛ አውሮፕላን የአየር ሁኔታው ለደኅንነት አስጊ በመሆኑ ከአዲስ አበባ ሳይነሳ በረራው እንዲሰረዝ ተደርጓል ሲሉም የአየር መንገዱ የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊ ወይዘሮ ሐና አጥናፉ መግለጻቸው ይታወሳል።

በወቅቱም ከበረራው መቋረጥ ጋር ተያይዞ በማኅበራዊ ሚዲያ የተላለፈ እሰጥ አገባ እንደነበር አይዘነጋም። ይህንንም ተከትሎ የሲቪል አቪዬሽንን ሕግና አሠራር ጥሰዋል የተባሉ ስድስት ተጠርጣሪዎች ፍርድ ቤት ቀርበዋል።

የአየር መንገዱ ዋና ሥራ አስፈፃሚ አቶ መስፍን ጣሰውም የበረራ ደኅንነትን የሚጥሱ ደንበኞች በዓለም አቀፍ የአቪዬሽን ሕግ እንደሚጠየቁ ማሳወቃቸው አይዘነጋም።

በዓለም አቀፉ የአቪዬሽን ደንብ መሠረት አላስፈላጊ ባሕሪ የሚያሳዩ መንገደኞች ሲኖሩ ሕጉ ምን ይላል? ኅብረተሰቡስ ምን አይነት ጥንቃቄ ማድረግ አለበት? በሚሉና በተያያዥ ጉዳዮች ዙሪያ የዘርፉን ኃላፊዎች ሃሳባቸውን ሰጥተዋል።

በኢትዮጵያ ሲቪል አቪዬሽን ባለሥልጣን የአየር ትራፊክ ማኔጅመንት ዳይሬክተር አቶ ዮሐንስ አበራ፤ የነሐሴ አስራ ስድስቱ ክስተት ግንዛቤ በመፍጠሩ ረገድ ያለንን ክፍተት እንድንለይ አድርጎናል ይላሉ።

ምናልባትም ግንዛቤን በአግባቡ ሰጥተን ቢሆን ኖሮ የተፈጠሩት ነገሮች በዚህ መልኩ ላይጓዙ እንደሚችሉም ጠቁመው፤ ሰዎች የአቪዬሽን ሕጉን ባለማወቅ በርካታ ጥፋቶችን እንደሚፈጽሙ ያስረዳሉ።

ተጓዦች በእያንዳንዷ ሰዓት ምን አለማድረግና ማድረግ እንዳለባቸው የሚያግዙ ተከታታይ የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረኮችና መግለጫዎች በቋሚነት እንደሚያስፈልጉ አንተው፤ በመገናኛ ብዙኃንና በተለያዩ የሶሻል ሚዲያ አማራጮች ጠቅላላው ማኅበረሰብ በአየር ትራንስፖርቱ ዙሪያ መብቶቹንም ግዴታዎቹንም እንዲያውቅ የሚደረግበት ስትራቴጂ አስፈላጊ መሆኑን ያብራራሉ።

በአየር ትራንስፖርቱ ኢንዱስትሪ ዙሪያ ግንዛቤ መፍጠር ብዙ ስህተቶች እንዳይደገሙ ያደርጋል የሚሉት ዳይሬክተሩ፤ በተመሳሳይ ብሔራዊ አየር መንገዱ ላይም ሆነ የኢትዮጵያ ኤርፖርቶች ላይ የሚፈጸሙ የስም ማጥፋት ዘመቻዎችንም ለመቀነስ እንደሚረዳም ይገልጻሉ።

ሕግን ባለማወቅ በሚፈጸም ጥፋት ከወንጀለኛነት ነፃ መሆን ባይቻልም ተገቢውን ግንዛቤ የያዘ ሰው ደግሞ ዘሎ ወደጥፋተኝነት የሚገባበትን መንገድ መቀነስ ይቻላል ሲሉ ያስረዳሉ።

በመሆኑም ተገልጋዮችም ሆኑ አገልግሎት ሰጪዎች በየጊዜው የሚወጡ የአቪዬሽን ዘርፍ ደንብና ግዴታዎችን መከታተል ይኖርባቸዋል፤ በተመሳሳይ መገናኛ ብዙኃኑም ሆነ የሚመለከታቸው አካላት ጥልቀት ያላቸውን መረጃዎችን ትንታኔዎች በማቅረብ ሰዎች ያላቸውን የግንዛቤ እጥረት መቅረፍ ይኖርባቸዋል ይላሉ።

በዚህም የአየር ደኅንነት ስጋቶችን በመቀነስ ዜጎች ያለወንጀል የሚጓዙበትን የተመቻቸ ምሕዳር ማስፋት እንደሚቻል ነው የሚጠቁሙት።

የኢትዮጵያ አየር መንገድ ዋና ሥራ አስፈፃሚ አቶ መስፍን ጣሰው ለመገናኛ ብዙኃን በሰጡት ማብራሪያ፤ የበረራ ደኅንነትን የሚጥሱ ደንበኞች በዓለም አቀፍ የአቪዬሽን ሕግ የሚጠየቁበት አግባብ መኖሩን አንስተዋል።

አየር መንገዱ ደንበኛ ንጉሥ ነው ብሎ የሚያምንና ዓለም አቀፍ የአቪዬሽን ሕግን አክብሮ የሚሠራ ተቋም ነው። ከዛ ባሻገር የአገልግሎት ጥራት ደረጃን በማውጣት ደንበኞችን በአገልግሎት አሰጣጥ ለማርካት ይሠራል በዚህ አግባብ ደንበኞችን የአቪዬሽን ሕግን አውቀውና በአግባቡ ተግብረው መገልገል እንዳለባቸው ይናገራሉ።

አየር መንገዱ የአገልግሎት አሰጣጥ ጥራትን በየጊዜው በመገምገም ደንበኞችን ለማርካትም እየሠራ ነው፤ ደንበኞቹም ደግሞ አላስፈላጊ አምባጓሮ ውስጥ ከመግባትና የበረራ ደኅንነትን አደጋ ውስጥ ከመጣል ተቆጥበው በዓለም አቀፍ የአቪዬሽን ሕግ እየተመሩ መሳፈር እንዳለባቸው ነው የሚጠቁሙት።

ደንበኞች ከእኔ ምን ይጠበቃል፤ የአቪዬሽን ተቆጣጣሪዎችን የአየር መንገዱ ሠራተኞች የሚያስተላልፏቸው ትዕዛዞችስ ለበረራ ደኅንነቱ ምን ያክል አስፈላጊ ናቸው የሚለውን ከግምት ውስጥ በማስገባት ተባባሪ መሆን እንደሚገባቸው እሙን ነው ሲሉ ይናገራሉ።

በጉዞ ወቅትም ሆነ በፊት የአየር በረራዎች ላይ እክል የሚፈጥሩ ስህተቶችን ግን እንደማይታገስና ተገልጋዮችን ሕግንና መመሪያን ብቻ አክብረው በመሳፈር የእራሳቸውንም ሆነ የሌሎችን ደኅንነት ማስጠበቅ እንዳለባቸው ይገልጻሉ።

የአቪዬሽን ዘርፉ እንቀሳቃሾች የዘርፉን ሕግ ጠንቅቆ ማወቅና መተግበር ለማንኛውም ዜጋ ቸል ሊባል የማይገባው ጉዳይ መሆኑን አፅንዖት ሰጥተዋል። በሀገር ውስጥም ሆነ በዓለም አቀፍ በረራዎች ላይ በባለሙያዎች የሚተላለፉ መልዕክቶችን መተግበርና አሠራሩን ተከትሎ መገልገል የአቪዬሽን ዘርፍ ደኅንነት ለማስጠበቅ ወሳኝነት አለው።

# የጥናትና ምርምር...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

መምህርና ተመራማሪ ጥሩሰው ተፈራ(ፕ/ር)፤ በጥናትና ምርምር ዘርፍ ቅንጅታዊ አሠራር ባለመፈጠሩ ጥናቶች ተግባራዊ እንዳይሆኑ ማድረጉን ይናገራሉ።

የጥናትና ምርምር ሥራዎች ለሀገር እድገትና ለሁለንተናዊ ልማት ጠቃሚ እንዲሆኑ ለማድረግ በቅንጅት መሥራት ተገቢ ነው የሚሉት ፕሮፌሰሩ፤ በየጊዜው የሚሠሩ ጥናቶች ችግር ፈቺና ለፖሊሲ ግብዓት አለመሆናቸው ብቻ ሳይሆን በትክክል የተሠሩትም ቢሆን መሬት ላይ አውርዶ የሚጠቀምበት ክፍል እንደሌለ ይጠቁማሉ።

በተጨማሪም የበጀት እጥረትና የበጀት ነፃነት አለመኖር፣ ጥናትና ምርምር ከተጨባጭ ሁኔታ ጋር ያልተገናኙ መሆን፣ የኅብረተሰቡ ችግር የሆነውን ቅድሚያ ሰጥቶ አለመሥራትና ለፖሊሲ ግብዓት የሚሆኑ ጥናቶችን አለመሥራት በኢትዮጵያ አብዛኛው የጥናትና የምርምር ሥራዎች ወደ ተግባር እንዳይቀየሩ አድርጓቸዋል ባይ ናቸው።

ኅብረተሰቡን ያማከለና ለፖሊሲ አቅጣጫ የሚያመላክት እንዲሁም ችግር ፈቺ የሆነ ርዕሰ ጉዳይ መምረጥና ጥናቱን የሚሠሩ አካላት ከሚመለከታቸው ጋር በመቀናጀት መሥራት ቢቻል በቀላሉ ወደ ተግባር የሚገቡ ይሆናል የሚሉት ጥሩ ሰው (ፕ/ር)፤ በሀገሪቱ የሚሠሩ ጥናቶች አሁንም በቂ ባለመሆናቸው ከፍተኛ ክፍተት እንዳለ ያስረዳሉ።

ሁኔታው ወደፊትም በተመሳሳይ መልኩ የሚቀጥል ከሆነ የሀገሪቱ ኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊና ፖለቲካዊ ችግሮችን የመፍታት አቅም ይበልጥ እያሽቆለቆለ የሚሄድ መሆኑንም ያክላሉ።

በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሚሠሩ አብዛኛው ጥናቶች የበጀት ነፃነት ስለሌላቸው በፈንድ አቅራቢዎች ፍላጎት ላይ የተመሠረተ እንጂ ብሔራዊ ጥቅም ላይ ትኩረት አያደርግም ያሉ ሲሆን በቀጣይም አግባብነት ያላቸው ጥናትና ምርምር እንዲካሄዱ መንግሥት በጀት በመበጀት ዘርፉን መደገፍ እንዳለበት ያመላክታሉ።

የትምህርት ባለሙያው አማኑኤል ኤሮሞ (ዶ/ር) በበኩላቸው በኢትዮጵያ የሚሠሩ የጥናትና የምርምር ሥራዎች የተወሰነ ክፍተት ኖሮባቸው ወደ ተግባር መግባት ባይችሉም አብዛኛው በትክክል የተሠሩትም ቢሆን ጠይቆ የመጠቀም ፍላጎት ያለው ተቋም አለመኖሩ በተግባራዊነቱ ላይ ፈተና ሆኗል ይላሉ።

ሌሎች ሀገሮች ላይ ጥናት ሲሠራ ተግባር ላይ የሚውል ነው የሚሉት አማኑኤል (ዶ/ር)፤ ኢትዮጵያ ላይ ከጅምሩም ቢሆን በመናበብ የሚሠራ ባለመሆኑ የተሠራው ጥናት ጠረጴዛ ከማሞቅ ውጪ ጥቅም ላይ አይውልም ባይ ናቸው።

እንደ አማኑኤል (ዶ/ር) ገለጻ፤ በዘርፉ ቅንጅታዊ አሠራር በመዘርጋት፣ እውቀትን በትክክል መምራትና ሀብትን በአግባቡ በመጠቀም ችግር ፈቺና አዳዲስ ሃሳቦች ማፍለቅ እንዲሁም የእውቀት አድማስ ሊያሰፉ የሚችሉ ጥናቶች መሥራት ያስፈልጋል። ዩኒቨርስቲዎች የተቋቋሙት ለሀገሪቱ ሁለንተናዊ እድገት እንጂ ተማሪ ብቻ ለማሠልጠን የተቋቋሙ ስላልሆነ የሚሠሩ ጥናቶች ተቋማት መጠቀም አለባቸው።

የተሠሩ ጥናቶች ወደ ተግባር የማይገቡበት ዋነኛ ምክንያት የቅንጅት ክፍተት፣ የበጀት እጥረት፣ ከንድፈ ሃሳብ በዘለለ በተግባር የሚሠሩ ጥናቶች ውስንነት ስላለ እንዲሁም የሀገሪቷ ፍላጎት ሌላ የተሠራው ጥናት ሌላ በመሆኑ ነው ያሉት ደግሞ የትምህርት ባለሙያው ከበደ ሶርሳ (ዶ/ር) ናቸው።

በሀገሪቱ የሚሠሩ የተለያዩ ጥናቶች ወደ ተግባር አለመውረዳቸው በሀገር ላይ ከፍተኛ ኪሳራ የሚያስከትል ስለመሆኑም አልዘነጉም።

እንደ ዶክተር ከበደ ገለጻ፤ የተለያዩ ዩኒቨርስቲዎች ተደጋጋሚ ጥናቶች ያደርጋሉ፤ ይህም ጥናቱ ከቦታ ቦታ ሊለያይ የማይችል ከሆነ ሀብት እውቀትና ጊዜን ከማባከን ውጪ ጥቅም አይኖረውም።

በትምህርት ሚኒስቴር የከፍተኛ ትምህርት ልማት ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ አቶ ኮራ ጠሹኔ በበኩላቸው ሚኒስቴሩ በዘርፉ ከቅንጅት ክፍተት ጋር ያሉ ችግሮች ለመቅረፍ የተለያዩ እቅዶች ነድፎ ወደ ተግባር ገብቷል ይላሉ።

ሀገሪቱ በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ብቻ ለጥናትና ለምርምር በየዓመቱ እስከ ሦስት ቢሊዮን ብር ወጪ ታወጣለች የሚሉት አቶ ኮራ፤ በምታወጣው ወጪ ልክ ተጠቃሚ ሆናለች ወይ የሚለው አሁንም ጥያቄ ውስጥ መሆኑን ይናገራሉ።

በቀጣይም ጥራታቸውን የጠበቁ የጥናትና ምርምር ሥራዎች ለማሠራት ብሎም ወደ ተግባር ለማስገባት የተለያዩ የሪፎርም ሥራዎች ተሠርተዋል ብለዋል።

# ጠንካራ የሥራ ባሕል የታየበት...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

አይዘነጋውም።

የኮሪደር ሥራው ላይ ከመግባቱ በፊት ከኮንትራክተሮች ጋር በካሬ 75 ብር እየተከፈለው ይሠራ እንደነበር አስታውሷል። አሁን ግን በኮሪደር ሥራው በካሬ 120 እና 150 ብር ይከፈለዋል። በዚህም ራሱን ከመቻል አልፎ እናትና አባቱን በመርዳት ማስደሰት እንደቻለ ተናግሯል።

የሐዋሳ የኮሪደር ሥራ የከተማዋን ውበት ከመጨመር ባለፈ የቱሪስት ቁጥርን ይጨምራል። ከዚህም በላይ ለትውልድ ውብ ከተማን ማስተላለፍ ያስችላል ያለው ወጣት ፍቃዱ፤ የአዲስ አበባ የኮሪደር ልማት የሥራ ዕድል የፈጠረ ብቻ ሳይሆን የሥራ ባሕልና አስተሳሰብን የቀየረ መሆኑን ይገልጻል።

የሀዋሳ ከተማም ከአዲስ አበባ ተሞክሮ በመውሰድ አዲስ የሥራ ባሕልን በከተማዋ ነዋሪዎች ላይ ለማስረጽ የኮሪደር ልማት ተጀምሯል ያለው ወጣት ፍቃዱ፤ በዚህም ተጨማሪ ሰዓት በመሥራት የወር ገቢውን ለማሳደግ እየሠራ መሆኑን ተናግሯል።

ሐዋሳን የሚመጥን የልማት ሥራ ላይ መሳተፋቸው በውስጣቸው ልዩ ስሜት እንዲፈጠር ማድረጉን የገለጸው ወጣት ፍቃዱ፤ በልማቱ በሚሠራው የሴራሚክና የቴራዞ ሥራ ላይ ነዋሪዎች ሲመላለሱና ሥራውን ሲያደንቁ ሲሰማ ደስታው እጥፍ ድርብ እንደሚሆን ተናግሯል።

የሲቪል መሐንዲስ ባለሙያ ወጣት ጌታቸው አታራ በበኩሉ፤ የኮሪደር ልማቱ ላይ የተሳተፈው በመደበኛነት ከሚሠራው ሥራ እረፍት በመውጣት መሆኑን ገልጾ፤ የእረፍት ጊዜው እስከሚጠናቀቅ ድረስ ከኮሪደር ልማቱ በርካታ ልምዶችንና ክህሎቶችን እንደሚያገኝ ተናግሯል። ይህም ወደፊት ሙያውን እንደሚያሳድግ አስረድቷል።

ጊዜውን በመዝናናትና ቤት ውስጥ ቁጭ ከማለት ወደኮሪደር ልማት ሥራው መግባቱን ገልጾ፤ በዚህም ተጨማሪ ሰዓት በመሥራት የተሻለ ገቢ እያገኘ መሆኑን ተናግሯል። ጠንክሮ ከተሠራ ከራስ አልፎ የቤተሰብንና የአካባቢን ኑሮ ለመለወጥ ወደሚያበቃ ደረጃ እንደሚሸጋገር ተስፋው መሆኑን አመላክቷል።

እያንዳንዱ የሥራ አይነት ትንሽ ወይም ትልቅ ሳይባል ትኩረት አግኝቶ ከተሠራ ጥሩ የገቢ ምንጭ ሊሆን ይችላል። ዛሬ ትንሽ ነው የሚባል አንድ ሥራ ተገቢውን ትኩረት ካገኘ ነገ የሚሠራውን ሰው ከፍ ወዳለ ደረጃ ሊያደርሰው ይችላል ብሏል።

የኮሪደር ልማቱ ለከተማዋ ገጽታ ከሚያበረክተው ጉልህ ሚና አንፃር ያለደመወዝ ቢሠራ እንኳን ቅር እንደማይሰኝ የገለጸው ወጣት ጌታቸው፤ ከሙያው አንፃር ሲመለከተው ለኮሪደር ልማቱ የተሰጠው ትኩረትና እየቀረቡ ያሉት ግብዓቶች ደረጃቸውንና ጥራታቸውን የጠበቁ መሆናቸውን እንዲሁም ሥራው በብቁ ባለሙያዎች እየተከናወነ መሆኑን ነው የተናገረው።

የምሕንድስና ሳይንስን መሠረት አድርጎ እየተገነባ በመሆኑ በጥራት የሚሠራ የኮሪደር ልማት መሆኑን በልበ ሙሉነት እንደሚናገር ገልጿል።

በሀዋሳ የኮሪደር ልማት በምሽት ሥራውን መሥራታቸው ፕሮጀክቱን በአጠረ ጊዜ እንዲጠናቀቅ እንደሚያደርግ እና ተጨማሪ ገቢ ማግኘት እንዲችሉ ማድረጉን የተናገረው ደግሞ የሴራሚክ ባለሙያው ወጣት ኢሳያስ የቴ ነው። በተፈጠረላቸው የሥራ ዕድል በሚያገኙት ገቢ ቤተሰቦቻቸውንና ራሳቸውን እያስተዳደሩ መሆኑን ገልጿል።

በኮሪደር ልማቱ ተግባራዊ የሆነው የሥራ ባሕል በኮንስትራክሽን ዘርፉ የሚስተዋለውን የጊዜ መዘግየት ችግር እንደሚቀርፍ ተናግሯል። በሌሎች የሥራ ዘርፎች የተሰማሩ ዜጎች ቀንና ሌሊት በመሥራት የሥራ ባሕል ለውጥ ማድረግና ለሀገራቸው ዕድገት መሥራት እንዳለባቸው መልዕክት አስተላልፏል። ትውልዱ ያገኘውን ዘመናዊ ትምህርትና ክህሎት በመጠቀም የሥራ ባሕሉን ማጠናከር እንዳለበትም ተናግሯል።

የሐዋሳ ከተማ ከንቲባ አቶ መኩሪያ መርሻ በበኩላቸው፤ በከተማዋ እየተካሄደ ያለው የኮሪደር ልማት ሙሉ በሙሉ የሥራ ባሕልን የለወጠ፤ ጅምሮ መጨረስን ያስተማረ ፕሮጀክት ነው ብለዋል።

ወቅቱ የከተሞች ትንሳኤ እንደመሆኑ ቀድሞ በቂ ትኩረት ያልተሰጠው የከተሞች ዕድገት አሁን ላይ በመሻሻሉ ዕድገታቸው እየጎለበተ መሆኑን አንስተዋል።

የሐዋሳ ከተማ የኮሪደር ልማት ሥራ ቀን ከሌሊት እየተሠራ መሆኑንና ከተማዋ የቱሪስት መዳረሻነትዋ የበለጠ ሳቢና ማራኪ ይሆናል ብለዋል።

የሐዋሳ ከተማ የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን መምሪያ ኃላፊ ምሕረቱ ገብሬ (ኢ/ር)፤ በበኩላቸው በከተማው የተጀመረው የኮሪደር ልማት በሁለት ዘርፎች ተከፍሎ እየተካሄደ እንደሆነና ይህም በከተማ ውስጥና በማስፋፊያ ቦታዎች ላይ የሚከናወንን መሆኑን አንስተዋል።

በከተማዋ የተጀመረው የኮሪደር ልማት ከአዲስ አበባ ብዙ ልምዶች የተገኙበት መሆኑን ያነሱት ኢንጅነሩ፤ የኮሪደር ልማቱ የእግረኛና የብስክሌት መንገድ፣ ፋውንቴን፣ የማረፊያ ቦታዎች፣ የሕፃናት መጫወቻዎችን አሟልቶ የሚይዝ እንደሆነም ያመላክታሉ።

በሐምሌ ወር የተጀመረው የሐዋሳ ከተማ የአንድ ነጥብ አንድ ኪሎ ሜትር የኮሪደር ልማት ሥራ በአሁኑ ወቅት 50 በመቶ መጠናቀቁን አንስተው፤ ሥራው በአጭር ጊዜ እንደሚጠናቀቅ ተናግረዋል።

በማስፋፊያ ቦታዎች ለሚካሄዱት የኮሪደር ልማት ሥራዎች አንድ ሺህ 145 ተነሺዎች መለየታቸውንና ለተነሺዎች ተገቢውን ካሣ ክፍሎ የልማት ሥራውን ለማስጀመርም አስፈላጊው ቅድመ ዝግጅት መጠናቀቁንም ነው የገለጹት።

ሐዋሳ በፕላን የተሠራች ከተማ በመሆኑዋ አሁን የተጀመረው የኮሪደር ልማት ሥራ ከተማዋን ይበልጥ የቱሪስት መዳረሻ ያደርጋታል ተብሎ እንደሚጠበቅም ኢንጂነር ምሕረቱ ተናግረዋል።

ማህበራዊ

# ባለውለታዎቻችን

## ታላቅ ኢትዮጵያዊ ፈላስፋ

**ክብረአብ በላቸው**

የምሁር ዕውቀት የሰዎችን ኑሮና አኗኗር ወደ ተሻለ ደረጃ ለማሻሻል የራሱን አስተዋጽኦ ማበርከት እንዳለበት ብዙዎች ይስማማሉ፡፡ በእያንዳንዱ የዕውቀት ዘርፍ የሚደረግ ጥናትና ምርምር የሰዎችን ሕይወት በማሻሻል ላይ ማዕከል ያደረገ መሆን እንዳለበትም እንዲሁ፤ ስለዚህ፣ አንድ ሰው በትክክል “ምሁር” ለመባል ብቁ የሚሆነው ዕውቀቱን ከራሱ አልፎ በሌሎች ሕይወት ላይ ለውጥና መሻሻል ለማምጣት የሚጠቀምበት ከሆነ ነው። ምሁርነትም ከዚህ አንፃር ታይቶና ተመዝኖ የሚሰጥ ክብር እንደሆነ ብዙዎች ይናገራሉ።

ስለዚህ ምሁር ማለት በልምድ፣ በትምህርትና በልዩ ልዩ መንገድ ያገኛቸውን ማስተዋሎችና ዕውቀት በሃሳብ መልክ ለኅብረተሰቡ የሚያቀርብ ሰው ነው። ለዚህ ቃል ብቁ ሆነው የተገኙ ጥቂት የሚባል ቁጥር የሌላቸው በዓለም መድረክ ላይ የሀገራቸውን ስም ያስጠሩ ዕንቁ ኢትዮጵያን አሉ፤ ከእነዚህ መካከል ፕሮፌሰር አንድሪያስ እሸቴ አንዱ ናቸው።

አብዛኞች እንደዋዛ ጥለዋት በሚለይዋት ዓለም በተቃራኒው ጥቂቶች ከራሳቸው ለሌሎች የሚተርፍ አስተዋጽኦ አበርክተው ማለፉ ይሳካላቸዋል። በሚያልፍ ዕድሜ የማያልፍ ሥራ ሠርተው ስማቸው ሲወሳ ከሚኖሩ ኢትዮጵያውያን መካከል አንዱ ከቀናት በፊት ከዚህ ዓለም ድካም ያረፉት ፕሮፌሰር እንድሪያስ፣ ባለዕውቀት፣ ብስለት ከጥበብ ጋር ከሰመረላቸው ለኢትዮጵያ ሀገረ መንግሥት ግንባታ ከሰሩ ኢትዮጵያውያን መካከል እንደሆኑ ብዙዎች ይመሰክሩላቸዋል።

ፕሮፌሰር አንድሪያስ እሸቴ፣ ከወላጅ እናታቸው መንበረ ገብረማርያም እና ከወላጅ አባታቸው ከእሸቴ ተሰማ ተወልደው በመሀል አዲስ አበባ አራት ኪሎ ልጅነታቸውን አሳልፈዋል፡፡

ከእናት እና አባታቸው በመቀጠል ያሳደጓቸው አጎታቸው ጀማነው አላብሰው ወጣትነታቸውን ደግሞ በፓንክረስት ቤተሰቦች ውስጥ እንደ ልጅ በመሆን ትምህርታቸውን እየተከታተሉ በእንክብካቤና በንባብ ራሳቸውን በእውቀትና በልምድ ማጎልበት ችለዋል፡፡

በሀገራችን ኢትዮጵያ የዘመናዊ ትምህርት ቤት ፋና ወጊ በመሆን በሚጠቀሰው ዳግማዊ ምኒልክ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የትምህርት ሕይወታቸውን ‘ሀ’ ብለው የጀመሩት የያኔው አንድሪያስ እሸቴ፣ በዊልያምስ ኮሌጅ ትምህርታቸውን ተከታትለው ከየል ዩኒቨርሲቲ የዶክትሬት ዲግሪያቸውን እስካገኙበት ጊዜ ድረስ ሰፊ የንባብ ልምድና የፍልስፍና ሕይወት ውስጥ ያለፉ ናቸው፤ ከሀገር ውጭ በተለያዩ ቦታዎች ከሰሩና በበርካታ ዩኒቨርሲቲ ውስጥ ካስተማሩ በኋላ ወደ ሀገር ውስጥ በመመለስ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በመምህርነት እንዲሁም የዩኒቨርሲቲው ፕሬዚዳንት በመሆን አገልግለዋል።

ከዚህ በመቀጠል በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ለቀድሞ ጠቅላይ ሚኒስትር አቶ መለስ ዜናዊ አማካሪ በመሆን አገልግለዋል፡፡ በ1987 ዓ.ም የኢትዮጵያ ሕገ መንግሥት ሲረቀቅም በአባልነት የራሳቸውን ሚና አበርክተዋል፡፡

ፕሮፌሰሩ፣ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት በነበሩበት ወቅት በርካታ ለትውልድ የሚሻገሩ ሥራዎችን የሰሩ ሲሆን፣ በፕሬዚዳንትነት ጊዜያቸው ካበረከቷቸው አስተዋፅኦዎች መካከል በፖሊሲ ደረጃ ውሳኔን በማሳለፍ ዓይነስውራን በያሬድ ሙዚቃ ትምህርት ቤት ገብተው ትምህርታቸውን መከታተል እንዲችሉ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያበረከቱ ምሁር እንደሆኑ ይጠቀሳል፡፡ በጋይዳንስ እና ካውንሲሊንግ ስር የነበረውን ለብቻው በማውጣትና ቦታ ሰጥቶ ሕንፃ በማሰራት የመጀመሪያውን የአካል ጉዳተኞች ተማሪዎች ማዕከል ወይም (የልዩ ፍላጎት ድጋፍ ማዕከል) ያቋቋሙት ፕሮፌሰሩ ናቸው፡፡

ለብቻው ሞደርን አርት ሙዚየም በመባል የገብረ ክርስቶስ ሥራዎች አሁን ባሉበት መልኩ ተለይተው እንዲቀመጡና እንዲጎበኙ፤ ተያይዞም ጥናትና ምርምር እንዲሰራባቸው አስደርገዋል፡፡ እንዲሁም ከሰባ ዓመታት በላይ ባስቆጠረው የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲው ታሪክ ውስጥ የመጀመሪያዋ ሴት ምክትል ፕሬዚዳንት የዛሬዋ ፕሮፌሰር ሂሩት ወልደማርያም የተሾመችው በዚሁ ጊዜ ነው፡፡ በርካታ በፒ.ኤች.ዲ ደረጃ አዳዲስ የትምህርት ዘርፎች እንዲከፈቱ ያደረጉት አበርክቶ ይጠቀሳል፡፡



ፕሮፌሰር አንድሪያስ እሸቴ

**ከፍልስፍና እስከ ሥነ-ምግባር፣ ከሃይማኖት እስከ ሥነ-ውበት፣ ከወንድማማችነት እስከ ነፃነት በርካታ ፍልስፍናዎችን ማጋራት ችለዋል**

ኢትዮጵያ የመጀመሪያዋን የሴት ፕሮፌሰር፣ ፕሮፌሰር የዓለምፀሐይ መኮንን ማዕረጉን ያገኙት በዚሁ በፕሮፌሰሩ የፕሬዚዳንትነት ጊዜ ነበር። በዕለቱም በሽልማት ሁሉ በማበረታታት በደስታ ብዛት ዕንባ ተናንቋቸው እንደነበር በዕለቱ በመድረኩ የታደሙ ታዳሚዎች ይመሰክራሉ፡፡

ፕሮፌሰሩ ሴቶችን ከማብቃት ጋር ስማቸው በተደጋጋሚ ተያይዞ ይነሳል፡፡ በተጨማሪም በፕሬዚ ዳንትነት ዘመናቸው ከሰሯቸው ሥራዎች ሌላው ከትምህርት ክፍሉ ወጥተው ሙዚቃ፣ ቴአትርና ስዕል አንድ ላይ በመሆን ራሳቸውን ችለው እንደ ኮሌጅ ቢቋቋሙ በማለት የተለያዩ ምሁራንን በመጋበዝ ኮሌጁን በእግሩ እንዲቆም አድርገዋል፤ በተጨማሪም ለቴአትር ትምህርት ቤት ታላቁን አዘጋጅ አባተ መኩሪያን ወደ ዩኒቨርሲቲው በማምጣት አዲሱ ትውልድ ልምዱን እና እውቀቱን እንዲቀስም ያደረጉት እኚሁ ፕሮፌሰር አንድሪያስ እሸቴ ናቸው ይላል ታሪካቸው፡፡

ፕሮፌሰር አንድሪያስን፣ ሌሎች የሀገራችን ምሁራን ሲገልጿቸው፤ በተለያዩ የትምህርት ዘርፎች በዋነኝነት በሕግ ፍልስፍና ዙሪያ ከፍተኛ አስተዋፅኦ በማድረግ በርካታ የሕትመት ውጤቶችን ከማሳተም ባለፈ ሕግና አዋጅ በማርቀቅና የፖሊሲ ማሻሻያ በማድረግ ለሀገርም ሆነ ለአፍሪካ የራሳቸውን ከፍተኛ አስተዋፅኦ ማድረግ የቻሉ ፈላስፋ ናቸው ይሏቸዋል፡፡

አንድሪያስ፣ ገና በወጣትነታቸው በመጀመሪያ ባሳተሙትና ሪቻርድ ፓንክረስት በሚያሳትሙት “Ethiopia observer” የተሰኘው መፅሔት ላይ ለዓለም አቀፉ ማህበረሰብ ብዙም ያልተወራለት የኢትዮጵያ የመረዳጃ ሀብቶች ስለሆኑት ስለ እድር፤ እቁብ እና ማህበራት ዙሪያ ከሪቻርድ ፓንክረስት ጋር በመሆን “self-help in Ethiopia” በሚል ርዕሰ አርቲክል በመፃፍ ባሕላችን ከሌላው ዓለም ጋርም ምን ዓይነት መስተጋብር እንዳለው በመዳሰስ እና በመዘርዘር በተጨማሪም ሀገር በቀል እውቀትና ባሕልን አጉልቶ በማሳየት ከፍተኛ አስተዋፅኦ ነበራቸው፡፡

ፕሮፌሰር አንድሪያስ በሥራ ዘመናቸው በሀገር ውስጥ ብቻ ሳይሆን በዓለም አቀፍ የሥራ ተሞክሯቸው በዩኔስኮ የሰብዓዊ መብት፣ የሰላም እና የዴሞክራሲ ሊቀ-መንበር በመሆን አገልግለዋል፡፡

በአሜሪካን ሀገር በነበሩበት ወቅት በሰብዓዊ መብቶች ንቅናቄ ላይ ንቁ ተሳታፊ ነበሩና በብላክ ፓንተር ፓርቲ ውስጥም ተሳትፎ የነበራቸው ምሁር ነበሩ፡፡ በሞራል እና ፖለቲካዊ ፍልስፍናዎች እንዲሁም ሥነ-ምግባር ላይ ያተኮሩ የድርሰት ውጤቶችን በበርካታ መንገዶች ለሕትመት አብቅተዋል፡፡ ከፍልስፍና ባሻገር ስለ ኢትዮጵያ አጫጭርም ሆነ ረጃጅም አርቲክሎችን በተለያየ ወቅት አስነብበዋል።

ፕሮፌሰሩ፣ በሙሉ ጊዜያቸው ተምረዋል፤ አስተምረዋል፤ ተፈላስፈዋል፡፡ በአስተማሪነት ከአገለገሉበቸው ዩኒቨርሲቲዎች ውስጥ በአሜሪካን ሀገር በሚገኘው ብራውን ዩኒቨርሲቲ፣ ዩሲኤልኤ፣ በርክሊን፣ ፔንሲልቬንያ ዩኒቨርሲቲ ከሀገር ውጭ ያስተማሩባቸው ቦታዎች ሲሆኑ፣ በርካታ ተማሪዎችም ማፍራት ችለዋል።

የተለያዩ ቦታዎች ማስተማር ብቻ ሳይሆን የተለያዩ የትምህርት ዓይነቶችንም በማስተማር ይታወቁ ነበር። ከፍልስፍና እስከ ሥነ-ምግባር፣ ከሃይማኖት እስከ ሥነ-ውበት፣ ከወንድማማችነት እስከ ነፃነት በርካታ ፍልስፍናዎችን ማጋራት ችለዋል፡፡ በዓለም አቀፍ ደረጃ እውቅናን ካተረፉ ዝነኞች ውስጥ በአሜሪካ ከዋነኞቹ የፖለቲካ ፈላስፋ መሀል ጆሴፍ ኮን እንዲሁም የሂውማን ራይትስ ዎች ፕሬዚዳንት ኬኔት ሮፍ ከፕሮፌሰሩ ተማሪዎች ውስጥ ለአብነት የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

ፕሮፌሰሩ፣ ገና በወጣትነታቸው በኢትዮጵያ ተማሪዎች ንቅናቄ ወቅት ታዋቂ ምሁር ከነበሩት ውስጥ አንዱ ነበሩ። በብዕር ተጋድሎአቸው፣ ከጥቂሮች መብት ጋር ባላቸው አቋም፣ በአንባቢነታቸው፣ በምሁርነታቸው ብቻ አልነበረም የሚታወቁት፤ ይልቁንም በመላው ኢትዮጵያ ሶሻሊስት ንቅናቄ (መኢሶን) ፓርቲ ውስጥ በመታቀፍ አባል ሆነው ለሀገራቸው ያበረከቱት ፖለቲካዊ አስተዋፅኦ አብሮ ይነሳል፡፡

ፕሮፌሰር አንድሪያስ፣ ከታላላቆቹ ፈላስፎች ውስጥ የፕሌቶ፣ የማርክስ እና ሄግልስ አድናቂ ሲሆኑ፣ ከሀገር ውስጥ ምሁራን እነ ነጋድራስ ተሰማ እሸቴ እና መንግሥቱ ለማ ሥራዎችን ማንበባቸውን እና መውደዳቸውን ሳይሸሽጉ ለሥነ-ጽሑፍም ከፍተኛ ፍቅርና ክብር እንዳላቸው ሲናገሩ ተደምጠዋል፡፡

ከማስተማር እና ከዩኒቨርሲቲ ሕይወት ባሻገር በተለያዩ ዘመናት በጦርነት ሰበብ በርካታ የሀገር ቅርሶች፣ የቤተክርስትያን እና የሀገር መዛግብት፣ መስቀል እንዲሁም የብራና መጻሕፍቶችን ወደ ሀገር ውስጥ ለመመለስ ታስቦ በተቋቋመው የተወሰዱ እና የተዘረፉ የኢትዮጵያ ቅርሶችን ወደ ሀገር ውስጥ በማስመለስ በነበረው ኮሚቴ ከዓለም አቀፉ ማህበረሰብ ጋር ከፍተኛ ሙግት በመግጠም እና በማሳመን የተወሰኑትን ሀብቶች በጊዜው ማስመለስ ከቻሉ የኮሚቴ አባላት ውስጥ አንዱ ፕሮፌሰር አንድሪያስ እሸቴ ናቸው፡፡

ፕሮፌሰር እንድሪያስ፣ የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ በ1995 ሕገ-መንግሥት በሚሻሻልበትና በሚረቀቅበት ወቅት የሕገ-መንግሥት እና አስተዳደር ጉዳዮች አስተባባሪ አባል በመሆን አገልግለዋል፡፡ በቦርዱም ውስጥ ከፍተኛ የሆነ አስተዋፅኦ እንደነበራቸው ይነገርላቸዋል፡፡

የአፍሪካ ህብረት የሰብዓዊ መብቶች መታሰቢያ ፕሮጀክት ጊዜያዊ ቦርድ ሊቀ-መንበር እና አባል በመሆን ፓን አፍሪካነትን በፅኑ ከሚያቀነቅኑ ምሁር ውስጥ በቀዳሚነት ይጠቀሳሉ፡፡ እንዲሁም የጣና ፎረም ከፍተኛ ደረጃ መድረክ ሊቀ-መንበር በመሆን እና የፌዴሬሽን መድረክ ቦርድ አባል በመሆን አገልግለዋል።

ፕሮፌሰሩ፣ ከጽሑፎቻቸው መካከል ስለ “ወንድማማችነት” የጻፉት ጽሑፍ በኢትዮጵያ የሀገረ መንግሥት ግንባታ ውስጥ ትልቅ ሚና ተጫውቷል ይባልላቸዋል። ከሦስቱ አስተሳሰቦች፣ “ነፃነት፣ እኩልነት እና ወንድማማችነት” ውስጥ የምዕራቡ ዓለም የፖለቲካ ፈላስፋዎች “ነፃነት እና እኩልነት” ላይ ያተኮሩ እና “ወንድማማችነትን” ችላ ብለዋል የሚሉት ፕሮፌሰር አንድሪያስ፤ በኢትዮጵያ የብሔር ፌዴራሊዝም አውድ ውስጥ “ወንድማማችነት” የሚለውን ሃሳብ የጋራ ቋንቋ እና ባሕል ላላቸው ብሔረሰቦች መተግበር አስተማማኝ ስለመሆኑ ይናገሩ ነበር።

ፕሮፌሰሩን ከሥራ ሕይወታቸው ባሻገር የቅርብ ወዳጆቻቸው ሲገልጧቸው ‘አንባቢና ሙሉ ፈላስፋ ነው’ ይሏቸዋል፡፡ ‘የምትተማመኑበት ጓደኛ፣ አዋቂ እና ተጫዋች ነው፡፡ ስስ የሆነ ነፍስ አለው፤ የተጎዳ ሰው ካየ በዕንባ ሀዘኑን ይገልፃል፡፡ ደግና ለሴቶች መብት አብዝቶ የሚጨነቅ ሰው ነው፡፡’ ብለው ይገልጿቸዋል። በኢትዮጵያ ቁልፍ የታሪክ ሁነቶች ውስጥ ታዛቢ ብቻ ሳይሆኑ ቁልፍ ተሳታፊም ነበሩ፡፡

ፕሮፌሰር አንድሪያስ እሸቴ፣ የአዲስ አበባ ዩኒቨር ሲቲ ፕሬዚዳንት በነበሩበት ወቅት በዩኒቨርሲቲው ውስጥ አካል ጉዳተኛ ተማሪዎች እውቅና እንዲያገኙና ምቹ ሁኔታ እንዲፈጠርላቸው ለሚደረገው ጥረት ድጋፍ በማድረግ በሀገራችን የከፍተኛ ትምህርት ተቋም ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ግቢ ውስጥ የአካል ጉዳተኞች ማዕከል ተቋቁሟል፤ በርካታ አገልግሎቶችን በመስጠት ላይም ይገኛል።

በዚህ ሳይቆም የኢትዮጵያ መስማት የተሳናቸው ብሔራዊ ማኅበር መሠረታዊ የኢትዮጵያ ምልክት ቋንቋ ስልጠና በዩኒቨርሲቲው ሥነ ልሳን ክፍል በኩል ጥያቄ አቅርቦ ለጥያቄው መልካምና ቀና ምላሽ በመስጠቱ መስማት የተሳናቸው የብሔራዊ ማኅበር አባላት በየሳምንቱ መጨረሻ ለአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ማኅበረሰብ መሠረታዊ የምልክት ቋንቋ ስልጠና ለረጅም ጊዚያት ሲሰጥ ቆይቷል።

በዚህም ለኢትዮጵያ ምልክት ቋንቋ እና መስማት የተሳናቸው ባሕል ትምህርት በመጀመሪያና በሁለተኛ ዲግሪ ደረጃ እንዲሰጥ ተደርጓል። ፕሮፌሰር አንድሪያስ እሸቴ፣ መስማት የተሳናቸው የማኅበረሰብ ክፍሎች ቋንቋና ባሕል በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ እዚህ ደረጃ መድረስና የበርካታ መስማት የተሳናቸው የከፍተኛ ትምህርት እድል መከፈት መሠረት የጣሉ ባለውለታ ነበሩ።

ፕሮፌሰር አንድሪያስ፣ ከወለዱት ልጃቸው አሉላ አንድሪያስ በተጨማሪ የአባት ፍቅር እየሰጡ ያሳደጓቸው የቀድሞ ባለቤታቸው የእሙዬ አስፋው ሁለት ልጆችን ታጠቅ እና አደይን ጨምሮ የሶስት ልጆች አባት ነበሩ። እኛም እኚህን ጉምቱ የሀገር ባለውለታ ምሁር በዚህ መልኩ ያስታወስናቸው ሲሆን፣ ለወዳጅ ዘመዶቻቸው መፅናናትን እየተመኘን ነው፡፡

The Ethiopian Herald
አዲስ ዘመን
BARIISAA
العلم
ወጋሕታ
BAKKALCHO
የህትመት ውጤቶቻችንን ለማንበብ ድረገጻችንንና ፌስቡክ ገጻችንን ይጎብኙ!
የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት
ዌብሳይት፡- www.press.et
ፌስቡክ፡- Ehiopian Press Agency

አዲስ ዘመን
ረቡዕ ስፖርት

ይህ ቦታ
ለማስታወቂያ ክፍት ነው!

# ታሪክ ሠሪው የኢትዮጵያ ፓራሊምፒክ ቡድን

**ቦጋለ አበበ**

ወጣቱ ኢትዮጵያዊ የፓራሊምፒክ ኮከብ አትሌት ይታያል ስለሺ በፓሪስ 2024 የፓራሊምፒክ ጨዋታዎች በዓይነስውራን ሙሉ በሙሉ(T 11) ምድብ በመካከለኛ ርቀት 1500 ሜትር አትሌቲክስ ውድድር የብር ሜዳሊያ አሸናፊ ሆኗል።

ትናንት ረፋድ በተካሄደውና ጠንካራ ፉክክር በታየበት ውድድር አትሌት ይታያል ከአሯሯጩ እሱባለው በቀለ ጋር በመሆን ከብራዚላውያን አትሌቶች ጋር ብርቱ ፉክክር አድርጎ 4:03:21 በሆነ ሰዓት ሁለተኛ ሆኖ አጠናቋል። በወጣቱ የፓራሊምፒክ ኮከብ ይታያል ስለሺ በምዕራብ ጎጃም ዞን ደንበጫ ከተማ የተወለደ ሲሆን እድሜው ገና 19 ነው፡፡

በኢትዮጵያ ፓራሊምፒክ ታሪክ በእድሜ ትንሹ የዓለም ፓራ አትሌቲክስ ሻምፒዮና የሜዳሊያ ባለቤትም ነው። ከደብረ ብርሃን ዩኒቨርሲቲ ክለብ የተገኘው ይህ አትሌት ወደስፖርቱ የገባው ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ሲሆን፣ በዘንድሮው ዓመት ዱባይ ላይ በተካሄደው የዓለም ፓራሻምፒዮና ሚኒማውን አማልቶ ሜይ 2024 ኮቤ ጃፓን ላይ በ1500 ሜትር ዓይነስውራን ሙሉ በሙሉ ምድብ 4:03:20 በመሮጥ የብር ሜዳሊያ ማጥለቅ ችሏል። በዚህም ለፓሪስ የፓራሊምፒክ ውድድር የቀጥታ ተሳትፎ ዕድልን ማሳካት ችሏል።

በቶኪዮ 2020 ፓራሊምፒክ ከሦስት ዓመት በፊት



**የኢትዮጵያ ፓራሊምፒክ ቡድን ከዓለም 27ኛ ከአፍሪካ ደግሞ 2ኛ ደረጃን በመያዝ አጠናቋል፣**

የርቀቱ የወርቅ ሜዳሊያ አሸናፊ የነበረው ብራዚላዊ ጃክኩዊስ ሄልትሲን የአሸናፊነት ግምት ከተሰጣቸው አትሌቶች አንዱ የነበረ ሲሆን፣ ፓሪስ ላይም በድንቅ ብቃት የወርቅ ሜዳሊያ አሸናፊ ሆኗል።3፡55፡82 ውድድሩን ያጠናቀቀበት ሰዓት ሲሆን የርቀቱ አዲስ የዓለም ክብረወሰን ሆኖም ተመዝግቧል፡፡

በጃፓን ኮቤ የዓለም ሻምፒዮና የወርቅ ሜዳሊያ ያሸነፈው ሌላኛው ብራዚላዊ ኤግሪፒኖ ዶስ ሳንቶስ ጁሊዮ ሴዛር ትልቅ የአሸናፊነት ግምት ያገኘ አትሌት ቢሆንም መጨረሻ ላይ በወጣቱ ኢትዮጵያዊ ተቀድሞ በ4፡04፡03 ሰዓት ሦስተኛ ሆኖ በማጠናቀቅ የነሐስ ሜዳሊያው አሸናፊ ሆኗል፡፡ ይህ ብራዚላዊ በዚሁ የፓሪስ ፓራሊምፒክ ከቀናት በፊት በ5000 ሜትር የወርቅ ሜዳሊያ አሸናፊ ነበር።

እንደ ኦሊምፒክ ትኩረት እየተሰጠው በማይገኘው የፓራሊምፒክ ጨዋታዎች ኢትዮጵያ እስከ ትናንት ድረስ ሁለት የወርቅና አንድ የብር ሜዳሊያ ማስመዝገብ ችላለች። ባለፈው ቅዳሜ ምሽት በአትሌት ትዕግስት ገዛኸኝ አማካኝነት ፓሪስ ላይ የወርቅ ሜዳሊያ ማስመዝገቧ ይታወቃል። ከትናንት በስቲያ ደግሞ በሴቶች 1500 ሜትር T11 ሙሉ በሙሉ ዓይነ ሥውራን አትሌት ያየሽ ጌቴ ከአሯሯጯ ክንዱ ሲሳይ ጋር በመሆን በራሷ የተያዘውን የዓለም ክብረ ወሠን በመስበር ጭምር የወርቅ ሜዳሊያ ማሸነፉ ይታወሳል፡፡ በወንዶች T46 የእጅ ጉዳት የ1500 ውድድር ደግሞ አትሌት ገመቹ አመኑ 7ኛ ሆኖ ያጠናቀቀ ሲሆን የዲፕሎማ ባለቤት ሆኗል።

የፓራሊምፒክ ቡድኑ ድል በሚዲያም ይሁን በመንግሥት በኩል በሚገባው ልክ አልተወራለትም። ያም ሆኖ የኢትዮጵያ ፓራሊምፒክ ቡድን ፓሪስ ላይ በአጠቃላይ በ4 ውድድሮች ላይ ተሳትፎ 2 ወርቅ፣ አንድ የብር ሜዳሊያ እና 1 ዲፕሎማ በማስመዝገብ ትልቅ ታሪክ በመሥራት ከዓለም 27ኛ ከአፍሪካ ደግሞ 2ኛ ደረጃን በመያዝ አጠናቋል፡፡ ይህም በኢትዮጵያ ፓራሊምፒክ ተሳትፎ ለመጀመሪያ ጊዜ ትልቅ ውጤት የተመዘገበበትና ታሪክ የተሠራበት ያደርገዋል፡፡ ኢትዮጵያ በ4ቱ ውድድሮች ላይ 6 አትሌቶችን አሳትፋለች። ከእነዚህ ውስጥ ሁለቱ አሯሯጮች ናቸው።

## ከኢትዮጵያ ኢንተርፕራይዝ ልማት ጋር በመተባበር በየ15 ቀኑ የሚታተም

# አምራች ኢንተርፕራይዞች በመስክ ምልከታ ሲዳሰሱ

የኢትዮጵያ ኢንተርፕራይዝ ልማት ከሀገራዊ ለውጡ ጋር ተያይዞ መንግሥት የሀገር ውስጥ አነስተኛና መካከለኛ አምራቾችን በማበራከትና በማሳደግ ለኢንዱስትሪው ልማት አስተማማኝና ሰፊ መሠረት ያለው እንዲሁም በሀገሪቱ ኢኮኖሚ የላቀ ድርሻ የሚወጣ የአምራች ኢንተርፕራይዝ ልማትን ዕውን ለማድረግና የዘርፉን የሪፎርም ሃሳብ ለማሳካት በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 526/2015 መሠረት በአዲስ መልክ ያደራጀው መንግሥታዊ ተቋም ነው።

ተቋሙ በአዲስ መልክ ሲደራጅ በዋናነት የተሰጠው ተልዕኮ አነስተኛና መካከለኛ አምራች ኢንተርፕራይዞችን መደገፍና ማብቃት ነው። በዚህም ኢንተርፕራይዞቹ የማምረቻና የመሸጫ ቦታ፣ የፋይናንስ፣ የግብዓት፣ የስልጠና፣ የቴክኖሎጂ፣ የገበያ ትስስርና መሰል ድጋፎችን አግኝተው ውጤታማ እንዲሆኑ፤ ለሀገራዊ ኢኮኖሚው የድርሻቸውን እንዲወጡ፤ ሰፊ የሥራ ዕድል ለዜጎች እንዲፈጥሩ እንዲሁም ጥራት ያላቸው ምርቶችን እንዲያመርቱና የተወዳዳሪነት አቅማቸው እንዲጎለብት፤ ይህንን ተከትሎ በሀገር ውስጥም ሆነ በውጭ ባሉ የገበያ ዕድሎች ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማስቻል ከዘርፉ ባለድርሻ አካላትና ድጋፍ ሰጪ ተቋማት ጋር በቅንጅት በርካታ ተግባራትን አከናውኗል፤ እያከናወነም ይገኛል።

መሥሪያ ቤቱም ለኢንተርፕራይዞች የሚሰጠውን ድጋፍና ክትትል ይበልጥ በተቀናጀና በተጠና መልኩ ለማድረስ እንዲሁም ኢንተርፕራይዞችን በአካል ጭምር በመገኘት ምልከታ በማድረግ የሚያጋጥሟቸውን ችግሮቻቸውን ለመለየት እና የመፍትሔ አማራጮችን ለማስቀመጥ ይረዳው ዘንድ የመስክ ምልከታ ያከናውናል።

ከዚህ አኳያ የተቋሙ የበላይ አመራሮችና ባለሙያዎች ከሰሞኑ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደርና በኦሮሚያ ክልል ሸገር ከተማ የሚገኙ ከሁሉም የአምራች ዘርፎች የተመረጡ ሞዴል አነስተኛ እና መካከለኛ አምራች ኢንተርፕራይዞችን በአካል በመገኘት የመስክ ምልከታ አድርገዋል፡፡ የመስክ ጉብኝቱ በሶስት ቡድን የተካሄደ ሲሆን፤ 18 ኢንተርፕራይዞች ተጎብኝተዋል።

በተለይ በአዲስ አበባና በኦሮሚያ ክልል ሸገር ከተማ ያሉ አነስተኛና መካከለኛ አምራች ኢንተርፕራይዞች ተኪ እና ወጪ ምርቶችን በማምረት ለሀገሪቱ ኢኮኖሚ ከፍተኛ አስተዋጽኦ በማበርከት የልማት ሞተር ሆነው እያገለገሉ ይገኛሉ። ሆኖም ኢንተርፕራይዞቹ ከዚህ በላይ ለሀገር ኢኮኖሚ የበኩላቸውን ሚና እንዳይጫወቱ እንዲሁም እድገታቸውን እና ዘላቂነታቸውን የሚያደናቅፉ በርካታ ተግዳሮቶች ያጋጥሟቸዋል።

በመሆኑም የመስክ ምልከታው ዋና ዓላማ በነዚህ አካባቢዎች የሚገኙ አነስተኛና መካከለኛ አምራች ኢንተርፕራይዞች ውስጥ ያሉ ምርጥ ተሞክሮዎችን (በአስተዳደር፣ በምርት ሂደት፣ በማምረት አቅም፣ በገበያ ትስስር፣ በቴክኖሎጂ አጠቃቀም እና በፈጠራ… ወዘተ) መለየት እንዲሁም በአካል ተገኝቶ ምልከታ በማድረግ ያጋጠሟቸውን ችግሮች ለመፍታት የሚያስችሉ የመፍትሔ አማራጮችን ለማስቀመጥ ነው። ስለዚህ በመስክ ምልከታው የተገኙ ውጤቶችን፣ የታዩ ጠንካራና ደካማ ጎኖችን እንዲሁም በቀጣይ ትኩረት የሚሹ ጉዳዮችን እንደሚከተለው ይዘን ቀርበናል።

### 1.የተገኙ ውጤቶች

- አነስተኛና መካከለኛ አምራች ኢንተርፕራይዞች ያሉባቸውን ችግሮች በአካል ተገኝቶ በመለየት ችግሩን ለመፍታት የሚያግዝ የመፍትሔ ሃሳብ ቀርቧል፤
- ኢንተርፕራይዞችን በአካል በመገኘት በፋይናንስ አቅርቦት፣ በመሥሪያ ቦታ፣ በገበያ ስትራቴጂዎች፣ በምርታማነት እና በጥሬ ዕቃ አቅርቦት ላይ የማማከር ሥራ ተሠርቷል፤
- በመስክ ምልከታው የኢንተርፕራይዞች ያሏቸውን ምርጥ ተሞክሮዎች መለየት ተችሏል፤
- በምልከታ ወቅት የታዩ ተግዳሮቶች ለንግድ ልማት አገልግሎት (BDS) አማካሪ እንደ ግብዓት ለማቅረብ ተግዳሮቶቹ ተለይተዋል፤
- በተለዩ ችግሮች ላይ ትክክለኛውን ድጋፍና ክትትል ለማካሄድ የድርጊት መርሃ ግብር መቀመጡ በመስክ ምልከታው የተገኙ ዋና ዋና ውጤቶች ናቸው።

### 2. ከባለድርሻ አካላት እና ኢንዱስትሪ/ኢንተርፕራይዝ ቢሮዎች አንፃር የታዩ ጠንካራና ደካማ ጎኖች ጥንካሬ

- ለአብዛኞቹ ኢንተርፕራይዞች የመሥሪያ ቦታዎች መሰጠቱ፤
- የክትትል እና ድጋፍ ሥርዓት በመዘርጋት መሠራቱ፤
- የማሽነሪ ሊዝ እና የሥራ ማስኬጂያ ፋይናንስ መቅረቡ ወዘተ በጠንካራ ጎን የሚነሱ ናቸው።

**ድክመት**

- አምራች ኢንተርፕራይዞች የማምረት አቅማቸው ሲጨምር፣ ምርታቸውን ለማስፋፋት የተለያዩ ማሽኖችን ወደ ሀገር ውስጥ ቢያስገቡም የማስፋፊያ ቦታዎች እና የመሥሪያ ሼዶች አለመሰጠታቸው፤
- የማኑፋክቸሪንግ ኢንተርፕራይዞች ከሌሎች በተለየ ሁኔታ በስፋት ቢኖርም፤ የወለድ ምጣኔው የአምራች ዘርፉን ያገናዘበ አለመሆኑ፤
- የሚደረጉ ክትትል እና ድጋፎች ያሉትን ችግሮች ከመለየት ባለፈ ተከታትሎ እና እቅድ በማውጣት ችግሮችን ከመፍታት አንጻር ክፍተቶች መኖራቸው፤
- ማሽኖችን ወደ ሥራ ለማስገባት ጊዜ የሚወሰድ ቢሆንም ከፋይናንስ ተቋማት በቂ የእፎይታ ጊዜ አለመሰጠት፤
- ኢንተርፕራይዞች ከሼድ እንዲወጡ ሲደረግ ቅድመ ዝግጅት እንዲያደረጉ አለመደረጉና ምትክ የመሥሪያ ቦታ አለመዘጋጀቱ ወዘተ በድክመት የታዩ ናቸው።

### 3.ከልማት መሥሪያ ቤቱ አኳያ የታዩ ጠንካራና ደካማ ጎኖች

**ጥንካሬ**

- አብዛኛው ኢንተርፕራይዞች ቢዝነስ ለመጀመር እና ለማጠናከር የሚያገዙ የአቅም ግንባታ (ቴክኒካል ሥልጠናዎች) በአነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዝ ፋይናንስ ፕሮጀክት ድጋፍ በመሰጠቱ አብዛኛው ኢንተርፕራይዞች ወደ ዘርፍ እንዲገቡ እና ቢዝነሳቸው እንዲጠናከር መደረጉ፤
- ሞዴል ኢንተርፕራይዞችን በመለየት ክትትል እና ድጋፍ መድረጉ፤
- ኢንተርፕራይዞች የምርት ሰርተፍኬሽን እንዲያገኙ ጅምር ሥራዎች መኖራቸው፤
- የፋይናንስ አቅርቦት ላይ የተሠሩ አበረታች ሥራዎች (ማሽነሪ ሊዝ እና የሥራ ማስኬጂያ) ወዘተ በጥንካሬ የሚጠቀሱ ናቸው።

**ድክመት**

- ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት መሠረተ ልማቶች እንዲሟሉ ከማድረግ አኳያ ክፍተት መኖሩ፤
- የመሥሪያ ቦታ ጥያቄዎችን ከአዲስ አበባ ኢንዱስትሪ ቢሮ እና ከባለድርሻ አካላት ጋር ተቀናጅቶ መሥራት ላይ ክፍተት መኖሩ፤
- የሥራ ማስኬጃ ብድር ላይ ከአምራች ኢንተርፕራይዞች አንጻር በልዩ ሁኔታ ተጠቃሚ የሚሆኑባቸው መመሪያዎችና አሠራሮች እንዲወጡና እንዲተገበሩ በትኩረት አለመሥራት ዋና ዋና የታዩ ክፍተቶች ናቸው።

### 4.በቀጣይ ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች

- የኢትዮጵያ ኢንተርፕራይዝ ልማት ከክልሎች ጋር በመተባበር በተሰጠው ሥልጣን እና ኃላፊነት መሠረት የኢንተርፕራይዞችን የመሥሪያ ቦታ ችግር ለመቅረፍ የክላስተር ልማት ጥናቶችን ወደ ተግባር እንዲገቡ ማድረግ፤
- ከሼድ እንዲወጡ የሚደረጉ ኢንተርፕራይዞች በኢንቨስትመንት የመሥሪያ ቦታ እንዲሰጣቸው ማድረግ፤
- የሥራ ማስኬጃ ብድር ላይ የወለድ ምጣኔ እና የብድር ዋስትና (ኮላተራን) ከአምራች ኢንተርፕራይዞች አንጻር በልዩ ሁኔታ ተጠቃሚ የሚሆኑባቸው ሁኔታዎች መፍጠር፤
- ኤክስፖርት እና ተኪ ምርት አምራች ኢንተርፕራይዞችን በልዩ ሁኔታ በኢንተርፕራይዝ ደረጃ ዕቅድ በመያዝ የክትትል እና ድጋፍ ሥርዓት መዘርጋት፤
- ከኢንተርፕራይዞች ክፍተት እና ፍላጎት በመነሳት የኢንዱስትሪ ኤክስቴሽን አገልግሎት ተደራሽ ማድረግ፤
- የኢንተርፕራይዞችን የግብዓት ፍላጎት በማጥናት ከኢንዱስትሪዎች፣ አስመጭዎች … ጋር ትስስር እንዲፈጠር ማድረግ በቀጣይ ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች ናቸው።